ያየነው የይሖዋ ምስክሮች በውጭ የተነሣባቸውን ችግር ቢሆንም እንኳ፣ ውስጣዊ አለመግባባቶችም ተፈጥረውባቸው ነበር:: በአንዳንድ ቤተ ክርስቲያናት የነበረው የጴንጤቆስጤ ልምምድ ወደ አጥቢያ የይሖዋ ምስክሮች ጉባኤም ደርሶ ነበር:: ስለዚህም አንዳንድ የይሖዋ ምስክሮች ሰማያዊ ተስፋ ተቀብለናል ማለት ጀመሩ[22]::

ናይሮቢ ከሚገኘው ቢሮ ዊልያም ኒስበት (William Nisbet) የተባለው ሚስዮናዊ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ችግሩን ለመፍታት ቢሞክርም፣ አንዳንድ የይሖዋ ምስክሮች በአቋማቸው ስለጸኑ ከድርጅቱ ተባረዋል::

የይሖዋ ምስክሮች ያጋጠማቸው ሌላው ስደት፣ ከማርክሲስታዊው መንግሥት ነው:: ከ1980ዓ.ም እስከ 1980ዓ.ም በዓመታዊ መጽሐፋቸውም ሆነ፣ «መጠበቂያ ግንብ» በተባለው መጽሔታቸው ምንም ዐይነት ስታቲስቲካዊ ዘገባ ያለመቅረቡ የዚህ ውጤት ነው:: እንደ 1992ዓ.ም ዓመታዊ መጽሐፍ፣ ብዙ የይሖዋ ምስክሮች በእምነታቸው የተነሣ ተገድለዋል::

ማጠቃለያ

ለይሖዋ ምስክሮች ዕድገት እንደ ምክንያት ከሚቈጠሩት መካከል፣ በስደት ጊዜ ጸንተው መቆማቸው፣ ሊስቡ የሚችሉና በወቅታዊ ርእሶች ላይ የሚዘጋጁ ጽሑፎቻቸው፣ እያንዳንዱ የይሖዋ ምስክር መሠረተ እምነቱን ማወቁ፣ አባላቱ እምነታቸውን ለሌላ ሰው ለማስተማር ያላቸው ከፍተኛ ፍላጎት እንደ ምክንያት ከሚቈጠሩት ውስጥ ዋንኞቹ ናቸው::

[22] እንደ መጠበቂያ ግንብ አስተምህሮ ሰማያዊ ተስፋ የተቀበሉት፣«ቅቡዓን» ብቻ ናቸው::

ክፍል ስምንት

ትምህርተ ሥላሴ የተቀዳው ከቃለ እግዚአብሔር ወይስ ከአረማውያን መድበለ አማልክት?

ሀ. የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮተ ሥላሴ

የይሖዋ ምስክሮች በትምህርተ ሥላሴ አያምኑም:: የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር በመባል የሚታወቀው ድርጅታቸው፣ «ሰዎች ስለ ሥላሴ በቅድሚያ የሚያውቁት ነገር ሳይኖር፣ መጽሐፍ ቅዱስን ከዳር እስከ ዳር ቢያነቡት፣ ካነበቡት ነገር የሥላሴን ፅንሰ ሐሳብ ሊያገኙ ይችላሉን? በፍጹም አይችሉም»[1] ይላል:: እንዲሁም «ሌት ጎድ ቢ ትሩ» የሚባለው የድርጅቱ መጽሐፍ፣ «ይህ እንግዳ የሆነና የተወሳሰበ አደናጋሪ አስተምህሮ በክርስቶስ ኢየሱስ ምንምትኵረት አልተሰጠውም፣ አላብራራውም፣ አላስተማረውም» ይላል[2]:: እንዲሁም «ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር» የሚለው መጽሐፋቸው ደግሞ፣ «የሥላሴ ትምህርትም ሆነ ስለ አምላክ ያላቸው ፅንሰ ሐሳብ [የሥላሴ አማኞች] ከአረማውያን ምንጮች

[1] ሥላሴ ማመን ይገባሃልን? (ብሮክሊን፡ የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክር ማኅበር፡ 1993) ገጽ 2
[2] " Let God Be True" (Brooklyn : Watchtower Bible and Tract Society, 1952) ገጽ 200

የተቀዳና መጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ ካለቀ ከአያሌ መቶ ዘመናት በኋላ፣ የአሁኑን ቅርጽ እንዲይዝ የተደረገ ነው»[3]ይላል::

የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት የሥላሴን አስተምህሮ ላለመቀበልና ትምህርቱም ከአረማውያን መድበለ አማልክት እሳቤ የተቀዳ ነው ብሎ ለመደምደም፣ ከቃለ እግዚአብሔር የሚጠቅሳቸውን «ማስረጃዎች» በማቅረብ[4]፣ ትምህርቱን ከእግዚአብሔር ቃል ጋር እናስተያየዋለን::

የይሖዋ ምስክሮችና ትምህርተ ሥላሴ

የይሖዋ ምስክሮች ምን ይላሉ:- የሥላሴ ትምህርት ያቈጠቈጠውና በስፋት ይታመንበት የጀመረው፣ ከሐዋርያት ዘመን በኋላ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ፣ «ሥላሴ» ወይም «ሦስት አካላት አንድ መለኮት» የሚሉትን ቃላት አይጠቀምም:: የብዙ ሊቃውንት ሥራ የሚያረጋግጠው፣ የሥላሴ ትምህርት የመነጨው ወይም መሠረታዊ እሳቤው መንጸባረቅ የጀመረው በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደሆነ ነው::

መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል:- የሥላሴ ትምህርት የተቀዳው የእግዚአብሔር ሥልጣናዊ ቃል ከሆነው ከመጽሐፍ ቅዱስ ነው:: እንደ ማንኛውም የክርስቲያን አስተምህሮ የሥላሴ ትምህርት ሥርዐት ባለው መልኩ የተተነተነው የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አብ፣ ወልድና፣ መንፈስ ቅዱስን በተመለከተ ለተነሣው የመናፍቃን እንቅስቃሴ መልስ ለመስጠት በሞከረችበት ወቅት ነው:: የምሁራን ማስረጃ የሚያረጋ

[3] በሥላሴ ማመን ይገባሃልን? (ብሮክሊን፤ የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር፤ 1993) ገጽ 204-205 በቅንፍ ያለውን እይጨምርም::

[4] በግርጌ ማስታወሻ ካለተመለከተ በስተቀር የድርጅቱ ትምህረቶች የተወሰዱት በሥላሴ ማመን ይገባሃልን? (1993) እንዲሁም ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር ገጽ 197-198፤212-218፤ 405-426 ላይ ነው::

ግጠውም ይህንን እውነት እንጂ፣ የሥላሴ አስተምህሮ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አለመሆኑን አይደለም[5]::

የይሖዋ ምስክሮች ምን ይላሉ:- መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሥላሴ የሚያስተምረው ምንም ነገር የለም:: እንደ ማቴ 28÷19 ያሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የሥላሴን ትምህርት ለማስተማር ብቁ አይደሉም:: ክፍሉ የሚያስተምረን አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የተወሰነ ኅብረት እንዳላቸው እንጂ፣ በግጻዌ መለኮት ውስጥ ሦስት እኩል የሆኑ አካላት [ትክክል ዕሪና ያላቸው ሦስት አካላት] ስለመኖራቸው አይደለም::

መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል:- መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሥላሴ ሰፊ ትምህርት አለው:: የሥላሴ ትምህርት የተመሠረተው በማቴ 28÷19 ላይ ብቻ አይደለም:: የበሰለ የሥላሴ አማኝ የሥላሴ ትምህርት ያረፈው በዚህ ክፍል ላይ ብቻ ነው አይልም:: ማቴ 28÷19 አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ህልውና እንዳላቸው ጥርት አድርጎ ያሳያል[ቀውማኑ አካል እንደ ሆኑና ትክክል ዕሪና እንዳላቸው ያስተምራል]:: አብና ወልድ አካላዊ ህልውና ካላቸው ከእነርሱ ጋር እኩል የተጠቀሰው መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ህልውና የለውም የተባለበት ምክንያት ምንድን ነው? እንደ ክፍሉ ትምህርት በሦስቱም ስም መጠመቃችን ራሳችንን ሙሉ በሙሉ ለሦስቱም ሥልጣን ማስገዛታችንን የሚያሳይ ነው:: ይህም እኩል የሆነ ሥልጣን እንዳላቸው ያሳያል:: መጽሐፍ ቅዱስ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ፍጥረታትን የመፍጠር፣ የዘላለምን ሕይወት የመስጠት ወዘተ የመሳሰሉ አምላካዊ ሥራዎችን ማከናወናቸው የሥላሴን አስተምህሮ ቀዳማይ አመንጪ ራሱ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሆነ የሚገልጽ ነው::

[5] ተስፋዬ ሮበሌ በሥላሴ ማመን አይገባህምን? በሚል ርእስ ያዘጋጀውን መጽሐፍ ያመለክቷል

የይሖዋ ምስክሮች ምን ይላሉ፡- ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉን ቻይ አምላክ አይደለም። ፍጥረታት፣ «አማልክት» [" gods"] ተብለዋል። ዕብራውያን 2÷7 የተጠቀሰው ከመዝ. 8÷5 ላይ ሲሆን፣ «መልአክ» የሚለው ቃል ከዕብራይስጡ፣ «ኤሎሂም» ከሚለው ቃል የተመለሰ ነው። ስለዚህ በመዝሙር 8÷5 ላይ የሚገኘው፣ «ኤሌሂም» የሚለው ቃል፣ «አማልክት» ወይም « እግዚአብሔር መሰል» [NWT: " godlike ones"] ተብሎ መተርጐም አለበት። መዝሙር 82÷1፡6፤ ዮሐ 10÷34 የእስራኤል ፈራጆች፣ «አማልክት» ተብለዋል። በዚህ ክፍል ላይ፣ «አማልክት» የሚለው ቃል የገባው እግዚአብሔርን በሚወክል መልኩ ነው። ምክንያቱም ፈራጆቹ የእግዚአብሔር ወኪሎች ናቸው። ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ለማስረዳት የቀረበው መከላከያ ጥቅስ መዝ 82÷6 ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል፡- ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ነው። የእግዚአብሔርንና የአማልክትን (gods) የትርጒም አጠቃቀም በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የሚለውን ነጠላ ቃል የሚጠቀመው ያህዌን ለማመልከት ነው። ለምሳሌ፡- እግዚአብሔር [በግሪኩ «ቴዎስ»] የሚለው ነጠላ ቃል በአዲስ ኪዳን 1400 ጊዜ ተጠቅሶአል። ሐሰተኛ አማልክትን ወይም ጣዖታትን ለማሳየት ቃሉ ጥቅም ላይ የዋለው ስድስት ጊዜ ብቻ ነው። ቃሉ ለሐሰተኛ አማልክት ስለመዋሉ ዐውዱ ያስተምረናል (ሐሥ 7÷43፤ 12÷22፤ 28÷6፤ 2ቆሮ 4÷4፤ ፊል 3÷19፤ 2ተሰ 2÷7)። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የሚለውን ቃል በነጠላ ቍጥር ከተጠቀመ [በዕብራይስጥ፣ «ኤል» ወይም ኤሎሂም። በግሪክ፣ «ቴዎስ»] የሚያመለክተው ሁሉን ቻይ የሆነውን አምላክ ነው። ስለዚህ ይህ ወጥነት ያለውና አንድ ዐይነት የቃል አጠቃቀም በግልጽ የሚያሳየን፣ ሁሉም የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ቃሉን የተጠቀሙበት እውነተኛውን አምላክ እንዲያመለክት ብለው ነው። መጽሐፍ ቅዱስ አንድ እውነተኛ አምላክ ብቻ እንዳለ ይናገራል (ለምሳሌ ኢሳ 43÷10፤

44÷6-8፤ ኤር 10÷10፤ ዮሐ 17÷3፤ 1ጢሞ 2÷5፤ ያዕ 2÷19፤ 1ዮሐ 5÷20)። በአንጻሩም አማልክት [gods] ተብለው የተጠሩት ሁሉ ሐሰተኛ አማልክት ናቸው (1ቆሮ 8÷5፤ ዘጸ 32÷21፤ መዝ 96÷5፤ ኢሳ 41÷23-24) ። እንግዲህ እውነቱ ይህ ከሆነ የይሖዋ ምስክሮች በዮሐ 1÷1 እና 20÷28 ላይ ቴዎስ የሚለው ነጠላ ቃል ለክርስቶስ ለምን እንደተሰጠ መልስ ሊሰጡበት ይችላሉ? በመዝ 82÷1 ላይ ሰዎች አማልክት (gods) ተብለዋል፤ ይህም በውክልና ደረጃ ብቻ ነው። ቃሉንም የሚጠቀምበት በምፀት መልክ [ironical] ነው። በክፍሉ ላይ፣ «አማልክት» እያለ የሚጠራቸው አድሎአዊ ፍርድ የሚበይኑትን ሐሰተኛ ፈራጆች ነው። ምክንያቱም ራሳቸውን እንደ አማልክት አድርገው ስለሚቈጥሩ ነው። ነገር ግን ዘማሪው አሳፍ እንደ ሰው ትሞታላችሁ ይላቸዋል (ቍ 6:7)፤ ጌታ ይህን ጥቅስ ወስዶ እያስተማረ ያለው (ዮሐ 10÷34) «የእግዚአብሔር ቃል አይሻርም» ለእነርሱ በምፀት የመጣው ቃል ለእኔ በቀጥታ መዋል አለበት የሚል ነው። ምክንያቱም ኢየሱስ ከአባቱ ጋር እኩል ነውና (ቍ 27-30:36)።

የይሖዋ ምስክሮች ምን ይላሉ፡- ኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር የሚያንስ አምላክ (a god) ነው እንጂ፣ «ሁሉን ቻይ አምላክ» አይደለም። በኢሳ 9÷6 ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ «ኀያል አምላክ» ተባለ እንጂ፣ «ሁሉን ቻይ አምላክ» አልተባለም።

መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል፡- በኢሳ 9÷6 መሲሑ፣ «ኀያል አምላክ» እንደ ተባለ ሁሉ፣ በዚያው ዐውድ የያዕቆብ አምላክ፣ «ኀያል አምላክ» ተብሎአል (ኢሳ 10÷21)። ይህ ክፍል፣ «ኀያል አምላክ» የሚለውን ቃል ለአብ እንደሰጠ ሁሉ ለወልድም መስጠቱ የወልድን አምላክነት የሚያረጋግጥ ነው።

የይሖዋ ምስክሮች ምን ይላሉ፡- ዮሐንስ 1÷1፤ እግዚአብሔር ከሚለው የግሪክ ቃል ፊት የተወሰነ መስተአምር [The] ካለ፣ ቃሉ

በአብዛኛው መተርጐም ያለበት እግዚአብሔር [God] ተብሎ ነው:: ነገር ግን ቃሉ አብዛኛውን ጊዜ እንደሚገኝበት ዐውድ ስለሚወሰን፣ የቃሉን ፍቺ የሚወስኑት ተርጓሚዎቹ ናቸው:: በዚህ ክፍል ግን « ቃል » የተባለው ክርስቶስ፣ «በእግዚአብሔር ዘንድ» ስለነበር፣ እርሱ ራሱ

እግዚአብሔር [God] ሊሆን አይችልም:: ይህም ዐውዱ ራሱ ግልጽ ያደርገዋል:: ምክንያቱም ማንም ከራሱ ጋር [«ዘንድ»] አብሮ ሊሆን አይችልም:: ስለዚህ የዮሐ 1÷1 ትክክለኛ ትርጒም [a god] የሚለው ነው::

መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል፡- ዮሐንስ 1÷1 ቴዎስ [እግዚአብሔር] የሚለው የግሪኩ ቃል አብዛኛውን ጊዜ፣ እግዚአብሔር ወይም አምላክ [God] ተብሎ ይተረጐማል:: ቃሉ በዚህ መልኩ የሚተረጐመው ከቃሉ ፊት የተወሰነ መስተአምር ሲኖርም ሳይኖርም ነው:: በግሪክ፣ በእንግሊዝኛም ሆነ በሌሎች ቋንቋዎች የተወሰነ መስተአምር [the] መኖርም ሆነ አለመኖር በስም [noun] ላይ መሠረታዊ ለውጥ አያመጣም:: በተለይ ቴዎስ የሚለውን የግሪክ ቃል አስመልክቶ ያለው የተወሰነ መስተአምር ጒዳይ፣ በአዲስ ኪዳኑ የግሪክ ትርጒም ላይ ለውጥ አያስከትልም:: ለምሳሌ፡- ሰይጣን፣ «የዚህ ዓለም አምላክ» (2ቆሮ 4÷4) ተብሎአል:: ነገር ግን ቴዎስ [አምላክ] ከሚለው ቃል ፊት የተወሰነ መስተአምር መኖሩ፣ ቃሉ እውነተኛውን አምላክ እንዲያሳይ አላደረገውም:: በአጠቃላይ ቴዎስ ከሚለው ነጠላ ቃል ፊት የተወሰነ መስተአምር ቢኖርም ባይኖርም ቃሉ እግዚአብሔር ወይም አምላክ [God] ተብሎ መተርጐም ይኖርበታል:: ነገር ግን ዐውዱ እውነተኛውን አምላክ የማያመለክት ከሆነ በእንግሊዝኛው [god] ተብሎ ይተረጐማል:: በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ አንድ ላይ ቴዎስ የሚለው ቃል የተወሰነ

መስተአምር ሳይኖረው እግዚአብሔር [God] ተብሎ ነው የተተረጐመው (ዮሐ 1÷1፡12፡13፡18):: በዮሐ 1÷1 ላይ «ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር» እግዚአብሔር (ቴዎስ) ከሚለው ቃል ፊት የተወሰነ መስተአምር አለ:: የትርጒም ይዘቱን ሳይቀይር ቴዎስ የሚለው ቃል የተወሰነ መስተአምር ሳይኖረው በሚቀጥለው ሐረግ ውስጥ ተጠቅሶአል፣ «ቃልም እግዚአብሔር ነበር » የተወሰነ መስተአምር ከቴዎስ ፊት መኖርም ሆነ አለመኖር የትርጒም ለውጥ እንደማያመጣ የሚከተሉትን ጥቅሶች በአዲሲቱ ዓለም ትርጒም እንኳን ማየት ይቻላል (ዮሐ 3÷2፤ 13÷3፤ ሮሜ 1÷21፤ 1ተሰ 1÷9፤ ዕብ9÷14፤ 1ጴጥ 4÷11-12)[6]::

«ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር» የሚለው ዐረፍተ ነገር የሚያሳየን ቃል የተባለው ክርስቶስ ከእግዚአብሔር አብ ጋር አብሮ እንዳለና [«ዘንድ»] ቃል የተባለው ወልድ ከእግዚአብሔር አብ የተለየ ህልውና (አካል) [Personality] እንዳለው የሚያስተምረን ነው:: በዚህ ትምህርት የይሖዋ ምስክሮች ራሳቸው ይስማማሉ:: [ነገር ግን፣ «የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን» አብና ወልድ አንድ ህላዌ (አንድ አካል) አላቸው ከሚለው ትምህርታቸው ጋር ይህን ጥቅስ እንዴት ያስታርቁት ይሆን?]:: ቀጣዩ ዐረፍተ ነገር፣ «ቃልም እግዚአብሔር ነበር» ሲል ቃል የእግዚአብሔር ባሕርይ [Nature] እንዳለው የሚያሳይ ነው እንጂ፣ የይሖዋ ምስክሮች እንደሚሉት እግዚአብሔር የሚለው ቃል ከሁሉን ቻዩ እግዚአብሔር ወደ ኀያሉ እግዚአብሔር መለወጡን ለማሳየት ተፈልጎ አይደለም:: በአጠቃላይ በዮሐ 1÷1 ላይ ለማለት የተፈለገው ቃል በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ነበር ነው:: እንዲሁም ቃል ራሱ የእግዚአብሔር ባሕር [Nature] እንዳለው ነው:: ዮሐንስ እግዚአብሔር (ቴዎስ) ከሚለው ቃል ፊት የተወሰነ መስተአምር («ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር») በማኖር እግዚአብሔር አብን ለማመልከት

---

[6] የበለጠ መረጃ የሚፈልጉ ከሆነ Robert M. Bowman Jr. Jehovah Witnesses, Jesus Christ and the Gospel of John. እንዲሁም Murray J. Harris, Jesus as God: The New Testament Use of Theos in Reference to Jesus (Grand Rapids Baker, 1992) ይመለከቷል::

እንደፈለገ ሁሉ ለወልድም ፣ [«ቃልም እግዚአብሔር ነበር»] የተወሰነ መስተአምር ቢጠቀም ኖሮ፣ «ቃል» የተባለው ክርስቶስ ራሱ እግዚአብሔር አብ ነው የሚል ትርጉም ይኖረው ነበር:: ዮሐንስ የክርስቶስን ፍጹም አምላክነትና ክርስቶስ ከአብ የተለየ ህላዌ እንዳለው ያሳየው ዐረፍተ ነገሩን ያለ መስተአምር በማዋቀር ነው::

የይሖዋ ምስክሮች ምን ይላሉ:- እንደ ሥላሴ አማኞች ትምህርት በዮሐ 5÷18 ላይ ሐዋርያው ዮሐንስ እየተናገረ ያለው ኢየሱስ ክርስቶስ፣ «ከእግዚአብሔር ጋር እኩል» እንደ ሆነ ነው:: ነገር ግን ዮሐንስ የዘገበልን ዕብራውያኑ የኢየሱስ አነጋገር የገባቸው ኢየሱስ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር እንዳስተካከለ ነው:: ስለዚህ ሰንበትን ሽረሃል የሚለው የዕብራውያኑ አነጋገር ሐሰት እንደሆነ ሁሉ፣ ራስህን ከእግዚ አብሔር ጋር አስተካክለሃል የሚለውም ሐሰት ነው::

መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል:- በዮሐንስ 5÷18 ላይ ዮሐንስ፣ ሰዎቹ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ ጋር እኩል ነኝ ማለቱ ነው ብለው መረዳታቸውን መዘገቡ እውነት ነው:: እንዲሁም ሰንበትን ሽረሃል የሚለው የሰዎቹ ክስ ትክክል ያለመሆኑ እውነት ነው:: ነገር ግን ይህ ጒዳይ የይሖዋ ምስክሮች ኢየሱስ እኔ ከአብ ጋር እኩል ነኝ አላለም የሚለውን ትምህርታቸውን አያመለክትም:: በሌላ ዐውድ ኢየሱስ ዕብራውያንን የሰንበትን መንፈስ በመሻራቸው ሲቃወማቸው እናያለን (ማቴ 12÷9-14) :: ነገር ግን በዚህ ክፍል ላይ ኢየሱስ የሰንበት ጌታ መሆኑን እያስተማረ ነው:: በዮሐ 5÷17 ላይ ኢየሱስ ሰንበትን እየተቸ ሳይሆን ሕጉ እርሱን እንደማያካትት፣ በሰብአውያን ላይ ብቻ ተግባራዊ እንደሚሆን እያስተማረ ነው:: ስለዚህ ዕብራውያን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ማድረጉ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር ማስተካከሉ ነው በማለታቸው አልተሳሳቱም:: ጌታ በሚቀጥሉት ጥቅሶች የሚለው እግዚአብሔር መሆኑን እየካደ ሳይሆን፣ የልጁ ሥልጣን በአባቱ ላይ የተመሠረተ መሆኑን እያስረገጠ ነው::

የይሖዋ ምስክሮች ምን ይላሉ:- በዮሐንስ 20÷28 ቶማስ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ «አምላኩ» [God] መሆኑን ማመኑ ኢየሱስ ከእርሱ በላይ ኀያል መሆኑን መቀበሉን የሚያመለክት ነው:: ወይም ኢየሱስ ክርስቶስን ሕያው ሆኖ በማየቱ ተደንቆ ወደ እግዚአብሔር አምላክ በመደነቅ መጮኹን የሚያሳይ ነው:: ይህ ክፍል ቶማስ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ሁሉን ቻይ አምላክ አድርጎት ማመኑን የሚያስተምር አይደለም:: ከዮሐ 20÷17 የምንማረው እግዚአብሔር የኢየሱስ ስቶየበላይ መሆኑን ነው:: እንዲሁም ዮሐ 20÷31 የሚያሳየን ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ወልድ እንደሆነ ሳይሆን የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ነው::

መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል:- በዮሐንስ 20÷28 ኢየሱስ ሕያው ሆኖ ከሙታን በመነሣቱ ቶማስ በመደነቅ ወደ እግዚአብሔር፣ «አምላኬ ሆይ!» ብሎ መጮኹ ነው:: የሚለው የይሖዋ ምስክሮች ትምህርት ከክፍሉ ዐውድ ጋር ብቻ ሳይሆን፣ ከታሪካዊ ዳራውም ጋር አብሮ የሚሄድ አይደለም:: በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የነበሩ አይሁዶች የእግዚአብሔርን ስም እንዲህ በንዝህላልነት መልኩ አይጠሩም ነበር:: ከክፍሉ የምንመለከተው ነገር ቶማስ በቀጥታ ለኢየሱስ መልስ መስጠቱን ነው:- «ቶማስም ጌታዬ አምላኬ ብሎ መለሰለት»:: «መለሰለት» የሚለው ቃል ወደ አብ መጮኹን ሳይሆን፣ በቀጥታ ኢየሱስን «ጌታዬ አምላኬ» ብሎ ማመኑን የሚገልጽ ነው::

የይሖዋ ምስክሮች ምን ይላሉ:- ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጡር ነው:: ምሳ 8÷22 «እግዚአብሔር የመንገዱ መጀመሪያ አደረገኝ በቀድሞ ሥራው መጀመሪያ» ይላል፤ ክፍሉ ስለ ጥበብ የሚናገር ነው:: ይህ ማለት ግን እግዚአብሔር እርሱ ራሱ ስላለው ጥበብ አይደለም፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር የራሱን ጥበብ ሊፈጥር አይችልም:: ስለዚህ ክፍሉ ስለ ሌላ ጥበብ የሚያወራ ነው:: በ1ቆሮ 1÷24 ክርስቶስ ጥበብ ክርስ ተብሎአል፤ ስለዚህ ምሳ 8 የሚናገረው ስለ ክርስቶስ ነው:: ይህም ክርስቶስ እንደተፈጠረ የሚያስተምር ነው::

መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል፡- የይሖዋ ምስክሮች ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጡር ነው ለማለት ከቃለ እግዚአብሔር የሚጠቅሱአቸው ጥቅሶች ትምህርታቸውን የሚደግፉላቸው ሳይሆኑ፣ ድርጅቱ ስለ እግዚአብሔር ቃል ያለው ዕውቀት ደካማ መሆኑን አለያም ቃለ እግዚአብሔር ትምህርቱን እንዲደግፍለት ሲል ሆን ብሎ እንደሚያጣምመው ያስረዳል::

ምሳ 8÷22 በመጽሐፈ ምሳሌ ከምዕራፍ 1-9 ባሉት ክፍሎች ሁሉ ጥበብ በሰውኛ አነጋገር ጥቅም ላይ ውሎአል:: ስለዚህ ምሳ 8÷22-31 ስለ ክርስቶስ ይናገራል ማለት ትክክል አይደለም:: የምሳሌ መጽሐፍ ቅርጽ ፍጹም ቅኔያዊ በመሆኑ፣ ከ1ቆሮ 1÷24-30 ጋር በማያያዝም ክፍሉ ስለ ክርስቶስ ይናገራል ማለት አግባብ አይደለም:: ጳውሎስ የቆሮንቶስን መልእክት ከመጻፉ በፊት የነበሩት አይሁድ፣ ክፍሉን እንዴት ይረዱት ነበር? መጽሐፈ ምሳሌ የቅኔ መጽሐፍ ነው፤ ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጹም ቅኔያዊ ነው:: በምሳ1-9 ባሉት ክፍሎች ጥበብ በሰውኛ [Personification] አገላለጽ ነው የተጠቀሰችው፤ ዳዊት፣ «በገና ሆይ ተነሣ፤ መሰንቆም፤ እኔም ማልጄ እነሣለሁ» (መዝ 108÷2) እንደሚለው ማለት ነው:: ለዚህም ነው መጽሐፉ ጥበብን በአንስታይ ጾታ (ቊጥር 1:2:3:11) የሚጠራት:: ኧረ ለመሆኑ ክርስቶስ በየትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው «አንቺ» (She) የተባለው? ክርስቶስ «የእግዚአብሔር ኀይልና ጥበብ» ከሆነ እግዚአብሔር ክርስቶስን ከመፍጠሩ በፊት ኀይልና ጥበብ የለውም ነበር ማለት ነው:: በአጠቃላይ የምሳሌ መጽሐፍ የጥበብን አስፈላጊነት እንጂ ስለ ክርስቶስ የሚናገር አይደለም::

የይሖዋ ምስክሮች ምን ይላሉ፡- በቈላ 1÷15 «ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኵር ነው» ይላል:: በኵር የሚለው ቃል የሚያሳየን ኢየሱስ ክርስቶስ በመወለድ ሂደት ውስጥ የመጀመሪያ መሆኑን ነው:: ይህም ኢየሱስ ክርስቶስ በይሖዋ አምላክ መፈጠሩን ያስተምረናል::

መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል፡- «በኵር» የሚለው ቃል በመወለድ ሕግ ቀደም ተከተል መሠረት የመጀመሪያ ማለት ሳይሆን፣ ክርስቶስ የፍጥረታት ሁሉ ወራሽና ባለቤት መሆኑን የሚያስተምር ነው:: «በኵር» ተብሎ የተተረጐመው የግሪክ ቃል [ፕሮቶቶከስ] የሚያመለክተው፣ በጊዜ ቀደም ተከተል የመጀመሪያ መሆንን ሳይሆን፣ ታላቅነትንና ክብርን የሚያሳይ ቃል ነው:: [የይሖዋ ምስክሮች እንደሚሉት ኢየሱስ ፍጡር ከሆነ፣ እንዴት በኵር መባል ይችላል? ምክንያቱም በኵር የሚለው ቃል መፈጠርን ሳይሆን መወለድን የሚያመለክት ነውና]:: ክፍሉ ኢየሱስ የተፈጠሩት ነገሮች ለእርሱ፣ በእርሱና ከእርሱ ስለ ተፈጠሩ የፍጥረታቱ ሁሉ ባለቤትና ገዥ መሆኑን ያመለክታል:: ንጉሥ ዳዊት የእሴይ የመጨረሻ ልጅ ነው:: በንግሥና ከሄድን ከዳዊት በፊት ንጉሥ ሳኦል 40 ዓመት ነግሦአል:: ነገር ግን እግዚአብሔር ዳዊትን በኵሬ ይለዋል መዝ 89÷27:: ይህ የዳዊትን ታላቅ ክብር እንጂ፣ የጊዜን ቀደም ተከተል የሚያመለክት አይደለም:: የዮሴፍ የመጀመሪያ ልጅ ምናሴ ሆኖ ሳለ (ዘፍ 41÷50-51) ኤፍሬም፣ «በኵር» ተብሎአል (ኤር 31÷9) :: ያዕቆብ የኤሳውን ብኵርና ወስዶአል ስንል <u>ክብሩን</u> ወሰደ ማለታችንም አይደል? የመውለድ ቀደም ተከተል ብኵርናውንማ (ቀዳሚነቱንማ) ማን ነክቶበት? ጳውሎስ በቈላ 1÷15 ላይ የኢየሱስን ፍጡር መሆን ለማመልከት ቢፈልግ ኖሮ፣ «ፕሮቶቶከስ» ከሚለው የግሪክ ቃል ያስገባ ይልቅ፣ «ፕሮቶኪቲሲስ» የሚለውን ቃል ያስገባ ነበር[7]:: በአዲስ ኪዳን ግሪክ፣ «ፕሮቶኪሲስ» የሚለው ቃል አንድም ጊዜ ክርስቶስን ለማሳየት ጥቅም ላይ አልዋለም»[8]:: የይሖዋ ምስክሮች በቈላ 1÷15 ላይ አራት ጊዜ ሌሎች (other) የሚለውን ቃል በአዲሲቱ ዓለም ትርጒም ላይ ጨምረዋል:: ነገር ግን የግሪክ አዲስ ኪዳን ሌሎች (አሌሎን) የሚል ቃል የለውም:: ያለምንም ቃለ እግዚአብሔር ማስረጃ በክፍሉ ውስጥ አራት ጊዜ

[7] F.F. Bruce, <u>Inerrancy</u> ed. Norman L. Geiseler (Grand Rapids: Zondervan, 1979)

[8] J.B.Light Foot, <u>Paul's Epistles to the Colossians and to Philemon</u>. (Grand Rapids: Zondervan, 1979) ገጽ 147

መጨመራቸው ኢየሱስ ፍጡር ነው ለማለት ምን ያህል እንደተጠቀሙበት፣ ከአዲሲቱ ዓለም ትርጉም (NWT) ላይ ይመልከቱ።

*የይሖዋ ምስክሮች ምን ይላሉ፡-*ኢየሱስ ክርስቶስ ከእርሱ በላይ የሆነ አምላክ አለው። ኢየሱስ አባቱን እግዚአብሔር ብሎአል። ኢየሱስ ይህንን ያለው ከትንሣኤው በኋላ ሰማያዊ በሆነው ክብሩ ሳለ ነው (ዮሐ 20÷17፤ ራእ 3÷12) ። ኢየሱስ ከእርሱ በላይ የሆነ አምላክ ካለው ሁሉን ቻይ አምላክ ሊሆን አይችልም። ኢየሱስ ክርስቶስ አሁን እንኳ በሰማይ ከእግዚአብሔር በታች ሆኖ ነው ያለው። መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስ በሰማይ ለእግዚአብሔር እየተገዛ እንዳለ ያስተምረናል። ይህም በምድር በነበረበት ጊዜ እንደተገዛው ማለት ነው (ዮሐ 14÷28 1ቆሮ 11÷3፤ 15÷28)።

መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል፡- ኢየሱስ ክርስቶስ አባቱን አምላኬ ብሎአል። ምክንያቱም ኢየሱስ የፍጡሩን ቦታ ለእኛ ለኀጢአተኞች ሲል ስለ ወሰደ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ለአብ በሰማይም ተገዝቶለት ነው ያለው። ነገር ግን ይህ ማለት ኢየሱስ ከአብ ያንሳል ማለት አይደለም። ኢየሱስ ክርስቶስ እስከ አሁን ድረስ ሰው ሆኖ ነው ያለው (ሐሥ 17÷31፤ 1ጢሞ 2÷5)፤ ስለዚህ የክርስቶስ መገዛት በምድር በነበረበት ጊዜ ብቻ አይደለም።

የይሖዋ ምስክሮች ምን ይላሉ፡- ኢየሱስ ክርስቶስ ማለት ሊቀ መላእክት ሚካኤል ማለት ነው፤ በዳንኤል 10÷13 ላይ ሚካኤል፣ «ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ» ነው። በዳን 12÷1 ላይ፣ «በዚያን ዘመን ስለ ሕዝብህ ልጆች የሚቆመው ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሣል. . .» የሚለው ትንቢት የተፈጸመው ኢየሱስ ክርስቶስ (ሚካኤል) በሰማይ እንደ ንጉሥ ሆኖ በ1914 በነገሠበት ጊዜ ነው[9]። ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ

[9] " Your Will Be Done On Earth" (Brooklyn Watchtower Bible and Tract Society, 1994) ገጽ 259።

ማስረጃ የሚያሳየን ኢየሱስ ክርስቶስ በቅድመ ሥጋዌም ሆነ በድኅረ ሥጋዌ ጊዜ ሚካኤል እንደሆነ ነው[10]።

መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል፡- ኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ መልአኩ ሚካኤል አይደለም። ትንቢተ ዳንኤልን ጨምሮ ብዙ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ሚካኤል፣ እስራኤላውያንን የሚጠብቃቸው መልአክ እንደሆነ ይገልጻሉ። ነገር ግን አንድም የብሉይም ሆነ የአዲስ ኪዳን ንባባት፣ ኢየሱስ ሚካኤል ነው የሚል ትምህርት የላቸውም። እንደ መጠበቂያ ግንብ ኢየሱስ በቅድመ ሥጋዌ ጊዜ ፍጹም ሰው ብቻ ነበር የሚል አቋም አለው። እንግዲያው ኢየሱስ ሰው ሲሆን ሚካኤል የት ሄደ? 1ተሰ 4÷16 «ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና» ይላል። ይህ ክፍል ኢየሱስ በዳግም ምጽአቱ ጊዜ የመላእክት አለቃ በሆነው በሚካኤል ድምፅ ታጅቦ እንደሚመጣ እንጂ፣ ኢየሱስ ሚካኤል ነው አይለንም።

የይሖዋ ምስክሮች ምን ይላሉ፡- መንፈስ ቅዱስ የራሱ አካል (Personality) የለውም። መጽሐፍ ቅዱስ፣ መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ህልውና እንደሌለው ያስተምራል። በማር 1÷10 መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ነው የታየው። በማቴ 3÷11፤ ሉቃ 3÷16 መንፈስ ቅዱስ ከእሳት ጋር ተነጻጽሮአል። በኤፌ 5÷18 መንፈስ ቅዱስን መሞላት በወይን ጠጅ ከመሞላት ጋር ተነጻጽሮአል። አካላዊ ህልውና ባለው ነገር መሞላት ሞኝነት ነው። መንፈስ ቅዱስ በሰውኛ አገላለጽ ቀርቦአል። ስለዚህ አካላዊ ህልውና ሊኖረው አይችልም። አንዳንዴ መጽሐፍ ቅዱስ አካላዊ ህልውና የሌላቸውንም ነገሮች በሰውኛ አገላለጽ ያቀርባቸዋል። ለምሳሌ ጥበብ ልጅ እንዳለው (ሉቃ 7÷35)፣ ኀጢአትና ሞት እንደ ንጉሥ እንደነገሡ (ሮሜ 5÷14:21)፣ ውሃና ደም ከመንፈሱ ጋር እንደሚመሰክሩ (1ዮሐ 5÷8) ተነግሮአል።

10 Aid to Bible Understanding (Brooklyn : Watchtower Bible and Tract Society, 1971) ገጽ 1152።

መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል፡- መንፈስ ቅዱስ የራሱ አካል (Personality) አለው [ቅውመ አካል ነው]:: ብዙውን ጊዜ አካላዊ ህልውና ማለት መጨበጥ፣ መታየት ወዘተ ማለት የሚመስላቸው ሰዎች አሉ:: ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ የአካል አለው ሲባል ይታያል፣ ይጨበጣል ወዘተ ማለት ሳይሆን፣ የአካል (Personality) ባሕርያት የሆኑት ማለትም ስሜት፣ ፈቃድና ዕውቀት አለው ማለት ነው:: የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት መንፈስ ቅዱስ የራሱ አካል እንደሌለው ያመለክታል የሚለው ትምህርት ስሕተት ነው:: በማር 1÷10፤ ሉቃ 3÷16ላይ መንፈስ ቅዱስ በርግብና በእሳት ተመስሎ መቅረቡ፣ የራሱ አካል የለውም እንድንል አያደርገንም:: አብ ራሱ በቁጥቋጦ እንደሚነድ እሳት ሆኖ ነው ሙሴን የተገናኘው (ዘፀ 3÷2-4) :: መጽሐፍ ቅዱስ በተምሳሌታዊ አገላለጽ እግዚአብሔር እሳት ነው ይለናል (ዘዳ 4÷24፤ 9÷3 ዕብ 12÷29):: ይህ ማለት ግን እግዚአብሔር አብ የራሱ አካል የለውም ማለት አይደለም:: ኤፌ 5÷18 በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ የሚለው የመልእክት ክፍል በእግዚአብሔርም (3÷19) እንዲሁም በክርስቶስ (4÷10) ተሞሉ ይለናል:: አብና ወልድ የየራሳቸው አካል እያላቸው የሚሞሉ ከሆነ መንፈስ ቅዱስ ቢሞላ የራሱ አካል የለውም የሚያሰኘው አንዳች ነገር የለም::

ለ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሥላሴ ምን ያስተምራል?

የሥላሴ ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው:: አንድ እግዚአብሔር ብቻ አለ (ኢሳ 43÷10፤ 44÷6-8፤ ኤር 10÷10፤ ዮሐ 17÷3፤ 1ጢሞ 2÷5፤ ያዕ2÷19፤ 1ዮሐ5÷20):: አብ እግዚአብሔር ነው (ዮሐ 17÷3፤ 1ቆሮ 8÷6) :: ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ነው (ኢሳ 9÷6፤ ዮሐ 1÷1፤ 20÷28፤ ሮሜ 9÷5፤ ቲቶ 2÷13፤ ዕብ1÷8፤ 2ጴጥ 1÷1):: መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ነው (ዮሐ 5÷3-4፤ 2ቆሮ 3÷17)::

ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉን ቻይ አምላክ ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ወይም አምላክ ተብሎአል (ኢሳ 9÷6፤ ዮሐ 1÷1፤ 20÷28፤ ሮሜ 9÷5፤ ቲቶ 2÷13፤ ዕብ 1÷8፤ 2ጴጥ1÷1):: ኢየሱስ ክርስቶስ ያህዌ ተብሎአል (ሮሜ 10÷9-13፤ ፊል 2÷9-11፤ ዕብ 1÷10-12፤ 1ጴጥ 2÷3፤ 3÷15):: ኢየሱስ ክርስቶስ፣ የእግዚአብሔር ብቻ የሆኑ ባሕርያት ሁሉ አሉት (ቈላ 1÷15፤ 2÷9 ዕብ 1÷3) :: ይኸውም አይለወጥም (ዕብ1÷11-12፤ 13÷8):: ዘላለማዊ ነው(ዮሐ 1÷1-2፤ 8÷58፤ 17÷5፤ ቈላ 1÷17፤ ዕብ 1÷2፡12) :: የኀይል ሁሉ ባለቤት ነው (ማቴ 28÷8፤ ኤፌ 1÷21) :: ሁሉን ያውቃል (ዮሐ 16÷30):: በሁሉ ቦታ ይገኛል (ማቴ 18÷20፤ 28÷30፤ ኤፌ 1÷23፤ ኤፌ 4÷10፤ ቈላ 3÷11):: ጥንት አነዋወኑን ማንም ሊያውቅ አይችልም [ከሰዎች ግምት ባላይ ነው] (ማቴ 11÷27፤ የተፈራ የተከበረ ነው ኤፌ 5÷21):: ከምንም፣ ከማንም በላይ በፍጹምነት ተፈቅሮአል (ማቴ10÷37):: በፍጹም ልብ የሚታመንበት ነው [ይኸውም እግዚአብሔርን እንደምናምነው ማለት ነው] (ዮሐ 3÷16፤ 14÷1):: ስግደትን ተቀብሎአል ወይም ተመልኮአል (ማቴ 28÷17፤ ዕብ 1÷6፤

ራእ 22÷3):: የሰዎችን ጸሎት ይሰማል (ዮሐ 14÷14፤ ሮሜ 10÷12-13፣ 1ቆሮ 1÷2) ::

መንፈስ ቅዱስ ፍጹም አምላክ ነው:: መንፈስ ቅዱስ የራሱ አካል አለው:: [ቅውመ አካል ነው]:: የእግዚአብሔር መንፈስ ተብሎአል [ርኩሳን መናፍስት መንፈስ እንደ ተባሉት ማለት ነው]:: መንፈስ ቅዱስ የራሱ ስም አለው (ማቴ 28÷19) :: አጽናኝ ይባላል (ዮሐ 14÷16) [ቃሉ በአዲስ ኪዳን ውስጥ (በግሪኩ ቅጅ ላይ የራሱ አካል ላለው፣ እኔ ብሎ ራሱን አካል ለሚጠራ ብቻ የሚሰጥ ስም ነው)]:: በኢየሱስ ክርስቶስ ተልኮአል፤ ይኸውም ለማስተማር፣ ለመመስከር ወዘተ:: ትምህርቱም ከራሱ ሳይሆን ከኢየሱስ ክርስቶስ የተወሰደ ነው (ዮሐ 14÷26፤ 15÷26፤ 16÷7፡ 13-14):: ከርኩሳን መናፍስት ጋር ተነጻጽሮአል (ማር 3÷28-30፤ 1ጢሞ 4÷1፤ 1ዮሐ 3÷24-4÷6):: ፈቃዱን ለደቀ መዛሙርት ነግሮአቸው፤ ወደ አገልግሎትም መርቶአቸዋል (ሐሥ 8÷29፤ 10÷9-20፤ 16÷7) :: ሰዎችን ለልዩ ልዩ አገልግሎት ጠርቶአቸዋል (ሐሥ 13÷2፤ 20÷28):: እርሱ ራሱ እንደሚፈቅድ ለክርስቲያኖች ስጦታን ይሰጣል (1ቆሮ 12÷11):: በቅዱሳን መጻሕፍት ተናግሮአል (ሐሥ 1÷16፤ 28÷25፤ ዕብ 3÷7):: ሰዎች ሊዋሹት ይችላሉ [እርሱ ግን አምላክ ስለሆነ ሁሉን ያውቃል ሐሥ 5÷3] ::

መንፈስ ቅዱስ ራሱ እግዚአብሔር ነው:: ያህዌ ተብሎአል (ዘፀ 34÷34)፤ [ይህን ጥቅስ ከ2ቆሮ 3÷17-18 ጋር ያነጻጽሩ] :: እግዚአብሔር ተብሎአል (ሐሥ 5÷3-4) :: የእግዚአብሔር ባሕርያት የእርሱም ገንዘቦች ናቸው:: ዘላለማዊ ነው (ዕብ 9÷14) :: ሁሉን ነገር ያውቃል (1ቆሮ 2÷10) :: በሁሉ ቦታ ይገኛል (መዝ 139÷7) ::

ክፍል ዘጠኝ

ትንሣኤ የአካል ወይስ የመንፈስ?

ሀ. የይሖዋ ምስክሮችና የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ

የይሖዋ ምስክሮችና የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር በመባል የሚታወቀው ድርጅታቸው፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን የተነሣው መንፈሳዊ ፍጥረት ሆኖ ነው[1]:: ክርስቶስ በአካል ሥጋ ከሙታን አልተነሣም[2]:: ነገር ግን የክርስቶስ ሰብአዊ አካል ወደ ጋዝነት ተለውጦአል ወይም ወደ አለመኖር ደረጃ ሄዷል የሚል አስተምህሮ አለው[3]::

ድርጅቱም ሆነ የድርጅቱ ተከታዮች ይህን አቋም እንዲይዙ ምክንያት ሆነውናል የሚሏቸውን ማስረጃዎች፣ ከራሱ ከድርጅቱ ጽሑፎች እየጠቀስን ከቃለ እግዚአብሔር ጋር እናነጻጽረዋለን::

የይሖዋ ምስክሮች ምን ይላሉ፡- ኢየሱስ ክርስቶስ አካሉን ከሙታን ካስነሣው ለኀጢአት የከፈለውን ዕዳ መልሶ ወስዶታል ማለት ነው (ማቴ 20÷28)::

መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል፡- መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወቱን ለኀጢአታችን ክፍያ እንዳዋለው ማስተማሩ እውነት ነው::

---

[1]. <u>Let God Be True</u>, (1946) ገጽ 22::
[2] <u>The Kingdom is at Hand</u> ገጽ 258::
[3] <u>Studies in the Scripture</u> ገጽ 129 ቅጽ 2::

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ የኢየሱስ አካለ ሥጋ ከሙታን ሊነሣ አይችልም አላለም::

የይሖዋ ምስክሮች ምን ይላሉ፡- መጽሐፍ ቅዱስ፣ ኢየሱስን ክርስቶስ መንፈስ ሆኖ እንደ ተነሣ ይናገራል:: ጳውሎስ በ1ቆሮ 15÷45 ላይ ኢየሱስ መንፈስ ሆኖ እንደተነሣ ያስተምራል:: በ1ጴጥ 3÷18 ላይ፣ «በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ» ማለት መንፈስ ሆኖ ተነሣ ማለት ነው::

መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል፡- እርግጥ [1ቆሮ15÷45] ኢየሱስን መንፈስ ነው ይለዋል:: ነገር ግን ይህ ማለት ኢየሱስ መንፈስ ብቻ ነበር ማለት አይደለም:: ይህን ክፍል ኢየሱስ መንፈስ ብቻ ነበር ብለን የምንወስደው ከሆነ፣ አዳምም፣ «ሕያው ነፍስ» ብቻ የሆነ፣ ቁሳዊ አካል የሌለው ነበር ማለት ነው:: ክፍሉ አዳምን ነፍስ፣ ኢየሱስን ደግሞ መንፈስ አድርጎ ማነጻጸሩ፣ አዳም ሰው ኢየሱስ መንፈስ ነው ለማለት ፈልጎ አይደለም:: ነገር ግን ጳውሎስ የሚያነጻጽረው፣ የአዳም ሕይወት ምድራዊና ተፈጥሮአዊ ነበር፤ የክርስቶስ የትንሣኤው ሕይወት ግን መንፈሳዊና ሰማያዊ ነበር:: አዳም ሕይወት ያገኘው የሕይወት እስትንፋስ እፍ በተባለበት ጊዜ ነው፤ ኢየሱስ ግን እርሱ ራሱ ሕይወት ሰጪ ነው፤ ስለዚህም የሕይወትን መንፈስ እፍ አለብን:: ጳውሎስ ይህንን ነው በንጽጽር ሊያሳየን የፈለገው::

በአንደኛ ጴጥሮስ 3÷18 ላይ፣ «በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ» ማለት የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት እንደሚለው መንፈስ ሆኖ የተነሣ ማለት አይደለም:: «በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ» ማለት በሥጋ ቢሞትም መንፈስ ቅዱስ ግን አስነሣው ለማለት ነው [NIV " Made alive by the Spirit"]:: ስለዚህ ክፍሉ ኢየሱስ መንፈስ ሆኖ ተነሣ ሳይሆን ያለው፣ ከሙታን ያስነሣው መንፈስ ቅዱስ ነው ማለቱ ነው (ሮሜ 8÷11 ይመለከቷል)::

ስመ ጥር የሆኑ የልሳነ ጽርዕ [የግሪክ ቋንቋ] ሊቃውንት ክፍሉ ኢየሱስ በሞተበት በዕለተ ዐርብና በትንሣኤ በተነሣበት በዕለተ እሑድ መካከል ስለነበረው ጊዜ የሚተርክ እንጂ፣ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ የሚናገር አይደለም የሚል አቋም አላቸው:: በአጠቃላይ ክፍሉ ስለ ትንሣኤ አይናገርም:: ነገር ግን በሞቱና በትንሣኤው መካከል የነበረውን ጊዜ የሚያመለክት ነው:: ይህ ትንተና ከክፍሉ ዐውድ ጋር የሚስማማ ነው:: ቀጣዩ ቁጥር (ቁ19)፣ «እርሱም ደግሞ ሄዶ በወህኒ ለነበሩ ነፍሳት ሰበከላቸው» ይህም በሞቱ ድል መንሣቱን ለማወጅ ነው:: ድል የነሣው ርኩሳን መናፍስትንና በኖኅ ዘመን የነበሩትን ኀጢአተኞች ነው (ቁጥር 20፤ ዘፍ 6÷1-4፤ 2ጴጥ 2÷4-5፤ ይሁዳ 5-6፤ ቈላ 2÷15):: ይህ ትንተና ከዐውዱ ጋር መስማማቱ ብቻ ሳይሆን የክፍሉን የሐሳብ ፍሰት የተከተለ ነው:: ቁጥር 18 ስለ ክርስቶስ ሞት፤ ቁጥር 19 እና 20 በሞቱና በትንሣኤው መካከል ስለነበረው ጊዜ፤ ቁጥር 21 ትንሣኤውን፤ ቁጥር 22 ዕርገቱን የሚመለከት ነውና::

በአጠቃላይ ምሁራን ክፍሉን በተመለከተ የተለያየ አቋም ይኑራቸው እንጂ፣ «በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ» ማለት መንፈስ ሆኖ ከሙታን ተነሣ የሚለውን ትንተና ከክፍሉ ትምህርት እጅግ የራቀ ስለሆነ አይቀበሉትም:: ስለዚህ ትክክለኛ የሆነው የክፍሉ ትምህርት (1) በሥጋ ቢሞትም መንፈስ ቅዱስ አስነሣው (ሕያው አደረገው)፤ (2) ክፍሉ ጌታ በተሰቀለበትና ከሙታን በተነሣበት ጊዜ መካከል ስላለው ሁኔታ (ጊዜ) የሚተርክ ብቻ ነው::

የይሖዋ ምስክሮች ምን ይላሉ፡- ኢየሱስ ክርስቶስ መለኮት ቀመስ ባሕርይ ክብር ስላለው ከሙታን የተነሣው ከሰብአውያን በላይ ሆኖ ነው:: የኢየሱስ አምላክ ቀመስ ባሕርይው፣ እግዚአብሔርን እንዲወክል አድርጎታል (ቈላ 2÷9፤ ዕብ 1÷3):: ስለዚህም መንፈስ መሆን የግድ ያስፈልገዋል (ዮሐ 42÷4)::

መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል፦ የእግዚአብሔር ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው እንደሆነ ያስተምረናል። የይሖዋ ምስክሮች፣ «ኢየሱስ መለኮት ቀመስ » ትምህርታቸው ምን ማለት ነው? ኢየሱስ አባቱን ድሮ በነበረኝ ክብር አክብረኝ (ዮሐ 17÷5) ማለቱ፣ ወደ ቀድሞ ክብሩ እንዲመለስ እንጂ፣ ሰዋዊነቱን ለመተው መፈለጉን አያሳይም። የኢየሱስ የትንሣኤ አካል እኛ ከለበስነው (ካለን) ሥጋና ደም የሚለየው፣ የኢየሱስ የትንሣኤ አካል የማይሞት፣ የማይበሰብስ፣ እጅግ የከበረ፣ ወዘተ መሆኑ ብቻ ነው (1ቆሮ 15÷50)።

የይሖዋ ምስክሮች ምን ይላሉ፦ ኢየሱስ ከትንሣኤው በኋላ ያለመታየቱ መንፈስ ሆኖ መነሣቱን ያረጋግጣል። ዓለም ኢየሱስን በፍጹም አያይም (ዮሐ 14÷19)። ከሙታን የተነሣውን ኢየሱስ ማንም አላየውም፤ ሊያየውም አይችልም (1ጢሞ 6÷16)።

መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል፦ በእርግጥ ዓለም ኢየሱስን ዳግም አያየውም (ዮሐ14÷19)፤ *ነገር ግን ይህ ማለት ኢየሱስ መንፈስ ሆኖ* ነው የተነሣው ማለት አይደለም። ከትንሣኤው በፊት እንደሚያደርገው በሕዝብ ፊት አይመላለስም ለማለት ነበር እንጂ፣ መንፈስ ሆኖ ስለ ተነሣ መታየት አይቻልም አይለንም። እግዚአብሔር፣ ኢየሱስን እንዲያዩ የፈቀደላቸው ደቀ መዛሙርቱና ሌሎች ሰዎች ኢየሱስን በርግጥ አይተውታል (ሐሥ 10÷39-41)። አንደኛ ጢሞ 6÷16 ሰው፣ ኢየሱስን በመለኮታዊ ክብሩ ፍጹም ማየት እንደማይቻል ያስተምራል። ነገር ግን ጳውሎስና ሌሎች ጥቂት ሰዎች በክብሩም እንኳ ቢሆን አይተውታል።

የይሖዋ ምስክሮች ምን ይላሉ፦ ደቀ መዛሙርት ከትንሣኤው በኋላ ኢየሱስን ያወቁት በአካል ሳይሆን በምግባሩ ብቻ መሆኑ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርት የታያቸው በተለየ አካል መሆኑን ያሳየናል። የኤማሁስ መንገደኞች ኢየሱስን ያወቁት ዳቦውን ቈርሶ፣ ባርኮ

ሲሰጣቸው ነው (ሉቃ 24÷13-31)። ማርያም ኢየሱስን ያወቀችው ስሟን ከጠራ በኋላ ነው (ዮሐ 20÷10-17)። ዮሐንስ ኢየሱስን ያወቀው ሌሎች ዓሣ እያጠመዱ ነው (ዮሐ 21÷1-7)።

መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል፦ ደቀ መዛሙርት ኢየሱስን ያላወቁት (ሉቃ 24÷13-31) «እንዳያውቁት ዐይናቸው ተይዞ ነበር» (ቊጥር 16) ስለሚል ነው። እግዚአብሔር ግን ዐይናቸውን ሲከፍትላቸው (ቊጥር 31) ዐወቁት። ደቀ መዛሙርት ኢየሱስን ዘግይተው ማወቃቸው ኢየሱስ መንፈስ ስለሆነ ሳይሆን፣ «ዐይናቸው ስለተያዘ» ነው። በዮሐ 20÷10-17 ላይ ማርያም ኢየሱስን በመጀመሪያ ያላወቀችው (1) ጨለማ ስለ ነበር (ቊጥር 1)፣ (2) ብዙ አልቅሳ ስለ ነበር ዐይኗ በእንባ ስለተሞላ (ቊጥር 11:13:15)፣ (3) ኢየሱስ እስከጠራት ጊዜ ድረስ ወደ እርሱ ስላልዞረች ነበር (ቊጥር 16) እንጂ፣ ኢየሱስ መንፈስ ሆኖ ስለተነሣ አይደለም። በዮሐ 21÷1-7 ደቀ መዛሙርት ኢየሱስን ያላወቁት አንደኛ ጊዜው «ንጋት» ላይ ስለ ነበር (ቊጥር 4)። ሁለተኛ ታንኳዪቱ ኢየሱስ ከነበረበት ስፍራ፣ «ሁለት መቶ ክንድ» [(Hundred Yards) የእግር ኳስ መጫወቻ ሜዳን የሚያህል ቦታ ነው] (ቊጥር 8) ያህል ርቃ ስለነበር እንጂ፣ ኢየሱስ መንፈስ ሆኖ ከሙታን ስለተነሣ አልነበረም።

የይሖዋ ምስክሮች ምን ይላሉ፦ ኢየሱስ በተዘጋ ቤት ውስጥ መግባቱ (ዮሐ 20÷19፤ 26)፣ በድንገት መታየቱም ሆነ ከዐይናቸው መሰወሩ (ሉቃ 24÷30-36) መንፈስ መሆኑን የሚያመለክት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል፦ ልክ ነው ኢየሱስ በተዘጋ ቤት ውስጥ ገብቶአል (ዮሐ 20÷19፤ 26)። በርግጥ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲፈልግ በድንገት መታየትም ሆነ መሰወር ይችል ነበር (ሉቃ 24÷30-36)። ነገር ግን ይህ ማለት ኢየሱስ ከሙታን የተነሣው መንፈስ ሆኖ ነው

ማለት አይደለም:: እግዚአብሔር በፊሊጶስ ተመሳሳይ ነገር አድርጓል (ሐሥ 8÷36-40):: ነገር ግን ፊሊጶስ መንፈስ አልነበረም:: ኢየሱስ ከትንሣኤው በፊት በውሃ ላይ የሄደው (ማቴ 14÷25-27፤ ማር 6÷42-50፤ ሐሥ 6÷6-20) በአካለ ሥጋ ከሆነ ከትንሣኤው በኋላ በተዘጋ ቤት ውስጥ መግባቱም ሆነ ከዐይናቸው መሰወሩ መንፈስ ነው እንዴት ያሰኘዋል?

ለ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ምን ይላል?

የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ የክርስትና እምነት ያረፈበት፣ ጸንቶ የቆመበት ታሪካዊ መሠረት ነው:: ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን አስተምህሮ አስመልክቶ፣ «ክርስቶስ ካለተነሣ እንግዲያስ ስብከታችን ከንቱ ነው፤ እምነታችሁም ደግሞ ከንቱ ናት» ይላል:: በተጨማሪም ጳውሎስ፣ «ክርስቶስም ካልተነሣ እምነታችሁ ከንቱ ናት እስከ አሁን ድረስ በኀጢአታችሁ አላችሁ» (1ቆሮ 15÷14-17):: የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ በቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፈ፣ የታወቀና የታመነ ነገር በመሆኑ፣ የአንድን ሰው ዘላለማዊ ሕይወት ጉዳይ ይወስናል፣ «ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር፣ እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህ» (ሮሜ 10÷9) ::

1. ትንሣኤ የሚለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል ቁሳዊ የሆነ አካልን ብቻ የሚያሳይ ነው[1]

መጽሐፍ ቅዱስ ትንሣኤ የሚለውን ቃል የሚጠቀመው ቁሳዊ አካልን በሚያመለክት መልኩ ብቻ ነው:: አይሁድ በተለይ ፈሪሳውያን የጻድቃንን የወደፊት ሁኔታ በተመለከተ የተለያየ አመለካከት ቢኖራቸውም፣ ሁሉም ግን ትንሣኤን ቁሳዊ አካል በጊዜያዊነትም ሆነ በቋሚነት ከመነሣት ጋር ብቻ ነበር የሚያይዙት[2]::

ምንም እንኳ ኢየሱስ ክርስቶስ በፈሪሳውያን ግብዝነት ባይደሰትም፣ ምንም እንኳን ሰዱቃውያን የሙታን ትንሣኤን ባለመቀበላቸው

---

[1] ይህ ክፍል የተወሰደው ተስፋዬ ሮበሌ የደራዋ ምስክሮችና አስተምህሮአቸው ቢቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን ገጽ 96-13 ላይ ነው::

[2] Norman L. Geiser, The Battel for the Resurrection (Nashville Thomas Nelson 1990)ገጽ 179-181::

ቢነቅፋቸውም፣ ትንሣኤ በሚለው የቃል ፍቺ ላይ ግን ተመሳሳይ አቋም ነበራቸው (ማቴ 22÷23-32)።

ጳውሎስ ቀድሞውኑ ፈሪሳዊ ስለነበር፣ ሥቃይ የደረሰበኝ ትንሣኤ ሙታን መኖሩን በማመኔ ነው ብሎ ነበር (ሐሥ 23÷6-8)።

በአጠቃላይ ትንሣኤ የሚለው ቃል ያለው ትርጕም የሞተ ሰው አካል በቋሚነትም ሆነ በጊዜያዊነት ሕይወት ማግኘት ማለት ነው።

2. ኢየሱስ እስከ አሁን ድረስ ሰው ሆኖ ነው ያለው

በአብ ቀኝ የተቀመጠው የእግዚአብሔር ልጅ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ አሁንም በክበበ ትስብእቱ እንዳለ አለ [አሁን ድረስ ሰው ሆኖ ነው ያለው] (ሐሥ 17÷31፤ 1ቆሮ 15÷47፤ 1ጢሞ 2÷5)።

በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 17 ላይ ጳውሎስ ስለ ሙታን ትንሣኤ እያስተማረ (ቍጥር 32)፣ ኢየሱስ ክርስቶስ አሁን እንኳ በክበበ ትስብእቱ [ሰው ሆኖ] እንዳለ ይናገር ነበር (ቍጥር 31)። በአንደኛ ቆሮ 15÷47 ጳውሎስ ስለ ሁለት ሰዎች እየተናገረ ነው ያለው። የአንደኛው ሕይወት ሰማያዊ ነው፤ የሌላው ደግሞ ምድራዊ ነው። ይህ የሚያመለክተን ኢየሱስ አሁንም በክበበ ትስብእቱ እንዳለ [ሰው ሆኖ እንዳለ] ጸንቶ የሚኖር እንጂ፣ ይህን ከአንድ ወቅት በኋላ የተወ ማለት አይደለም። 1ጢሞ 2÷5 በዚህ ክፍል ኢየሱስ በአሁኑ ጊዜ እንኳ በክበበ ትስብእቱ ባይኖር [ሰው ባይሆን] ኖሮ፣ «ሰው የሆነ» ማለት ባላስፈለገው ነበር። ኢየሱስን አማላጅ እንዲሆን ያደረገው የእኛን ሥጋና ደም ገንዘብ ማድረጉ ነበር። ኢየሱስ የእኛን ሥጋና ደም ትቶ መንፈስ ከሆነማ አማላጅነቱ እምኑ ላይ ነው?

3. ኢየሱስ ራሱ እኔ መንፈስ አይደለሁም ብሎአል

በሉቃ 24÷39 ኢየሱስ መንፈስ እንዳልሆነ ለማስረገጥ የእጁንና የእግሩን ዕትራት [የቍስሉ ምልክቶች] በማሳየት እኔው ራሴ ነኝ ብሎአል። የይሖዋ ምስክሮች እንደሚሉት ኢየሱስ ሥጋና ደም አለኝ ብሎ ለደቀ መዛሙርቱ ዳስሱኝ ያለው፣ የደቀ መዛሙርቱን እምነት በማገዝ፣ መነሣቱን እንዲያምኑ ነበር የሚለው ትንትና ፍጹም ከእውነት የወጣ ነው። እንዴት ደቀ መዛሙርቱን እያታለለ እምነታቸውን ያጠናክራል?

4. ወንጌላት የኢየሱስ አካለ ሥጋ ሕያው እንደሆነ ይናገራሉ

መላእክት የኢየሱስ ሥጋ በመቃብሩ ስፍራ ያለመገኘቱን ማብሠራቸው፣ ኢየሱስ በአካለ ሥጋ መነሣቱን ያሳያል (ማቴ 28÷6፤ ማር 16÷6)።

ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን የተነሣ በኋላም የተቸነከሩት የትንሣኤ አካል በስቅላቱ ጊዜ እጆቹ፣ እግሮቹና በጦር የተወጋው የጐኑ ዕትራት [የቍስሉ ምልክቶች] እንዳሉ ነበሩ (ሉቃ 24÷39-40፤ ዮሐ 20÷20፤ 25÷27)።

ኢየሱስ ከትንሣኤው በኋላ ምግብ በልቶአል (ሉቃ 24÷41-43፤ ሐሥ 1÷4፤ ዮሐ 21÷12-15)።

5. ኢየሱስ የአካለ ሥጋ ሕይወቱን በትንሣኤ መልሶአል

ኢየሱስ የአካለ ሥጋ ሕይወቱን የሰጠው (ያኖረው) ለዘላለም ሊተወው ሳይሆን በከበረ ሁኔታ ዳግም ሊያስነሣው ነው (ዮሐ 10÷17-18)። «ነፍሴን ደግሞ እነሣት ዘንድ አኖራለሁና» (ቁጥር17) የሚለው ገለጻ የሚያመለክተን ነፍሱን የሚያኖርበት ምክንያት ለማስነሣት ነውና (በዚህ ክፍል፣ «ሒና» የሚለው የግሪክ ቃል ምክንያትን የሚያሳይ ነው)።

የሐዋርያት ሥራ 2÷24-32 «እግዚአብሔር ግን የሞትን ጣር አጥፍቶ አስነሣው፤ ሞት ይይዘው ዘንድ አልቻለምና» (ቁጥር 24) ይላል እንጂ፣ እግዚአብሔር ኢየሱስን እንደገና መንፈስ አድርጎ ሠራው አይልም። «ሞት ይይዘው ዘንድ» ካልቻለ የይሖዋ ምስክሮች ለምን ሞቶ ቀረ ይሉናል።

ጴጥሮስ በመዝ 16÷8-11 የተጻፈውን ቃል ከክርስቶስ ጋር ያያይዘዋል (ሐሥ 2÷25፡ 29-30) «. . . ደግሞ ሥጋዬ በተስፋ ያድራል፤ ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና. . .» (ቁጥር 26÷27)። የሞተው የክርስቶስ አካለ ሥጋ በሲኦል እንደማይቀር፣ «ተስፋ» ያደርጋል። በዚህ ቦታ፣ «ነፍስ» የሚለው ቃል ሰብአዊ የሆነውን ሕይወቱን የሚያሳይ ነው። የሚከተሉትን ጥቅሶች ይመልከቱ (ማቴ 20÷28፤ ማር 10÷45፤ ዮሐ 10÷17-18)። በእነዚህ ክፍሎች ላይ ነፍስ [በግሪኩ ሱቼ] የሚለው ቃል የክርስቶስን ሥጋዊ ሕይወት የሚያሳይ ነው።

6. የሞተው አካል ነው ከሙታን የተነሣው

ኢየሱስ ክርስቶስ የሚሞተውን አካለ ሥጋውን ከሙታን እንደሚያስነሣ በዮሐ 2÷19-22 ላይ አስቀድሞ ተናግሮ ነበር። ቁጥር 19 ላይ «ይህን» የሚለው አመልካች ቃል የሚያሳየው ኢየሱስ፣ « ቤተ መቅደስ» ብሎ ስለ ሚጠራው ስለ አካለ ሥጋው ነው። ይህም በሚናገርበት ጊዜ የነበረውን፣ ኢየሱስ፣ «አፍርሱት» (ቁጥር 19) ያለውን ነው ያስነሣው። የፈረሰው መንፈሳዊ አካል ወይም ቤተ ክርስቲያን አይደለም። ነገር ግን አካለ ሥጋውን ነበር እንጂ [የይሖዋ ምስክሮች ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ስለሆነች አስነሣለሁ ያለው ቤተ ክርስቲያንን ነው የሚሉት ነገር አላቸው። ነገር ግን ኢየሱስ አስነሣለሁ ያለው የፈረሰውን፣ በሦስተኛውም ቀን የተነሣውን አካለ ሥጋውን ነው]።

ኢየሱስ፣ «በሦስት ቀን» ያስነሣው አካለ ሥጋውን ነበር እንጂ፣ ቤተ ክርስቲያንን አልነበረም። «ቤተ መቅደስ» የእግዚአብሔር ክብር የሚገለጥበት ምድራዊ ሕንጻ ነው።

7. በአንደኛ ቆሮንቶስ 15 ላይ ጳውሎስ ስለ አካል ትንሣኤ በስፋት አስተምሮአል

አንደኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 15 ስለ ክርስቶስም ሆነ ስለ አማኞች ያለውን የአካለ ሥጋውን ትንሣኤ በስፋት የሚያስተምር ስለሆነ ትኩረት ሰጥተን ልናጠናው ይገባል።

ሀ. « . . . ከእናንተ አንዳንዶቹ ትንሣኤ ሙታን የለም እንዴት ይላሉ? » (ቁጥር 12)

ጳውሎስ ይህን መልእክት የጻፈው ከአቴና ጥቂት ኪሎ ሜትር ርቃ ለምትገኘው ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ነው። በጥንታውያኑ

የቆሮንቶስ ሰዎች ዘንድ የሞቱ ሰዎች ዳግም ሕይወት ያገኛሉ የሚለው ትምህርት እንደ ተረት የሚቆጠር ነበር (ሐሥ 17÷32) ። አንድ ግሪካዊ ወደፊት ሕይወት ለወደፊትም በመንፈሳዊው ዓለም ይቀጥላል የሚለውን ትምህርት የሚቀበለው እንጂ፣ የሚሰናከልበት ጉዳይ አይደለም፤ ግሪካውያንን የሚያሰናክላቸው የአካለ ሥጋ ትንሣኤ ወይም በዚሁ አካል ዳግም ሕይወት ይገኛል የሚለው ትምህርት ነው[3]።

ለ. «. . . የምትዘራው የሚሆነውን አካል አይደለም. . .»

የዘር ፍሬ ከቡቃያው [ከሚበቅለው] ፍሬ እንደሚለይ የትንሣኤም አካል ከሚሞተው አካል የተለየ ነው። ነገር ግን በተዘራው (በሞተው) ዘርና በበቀለው ዘር መካከል በክፍል-ሕዋስ ወይም በመሠረታዊው ተፈጥሮአቸውም ሆነ በታሪካቸው ልዩነት እንደሌላቸው ሁሉ ከሙታን የተነሣው አካልም ከሞተው አካል ጋር ያለው አንድነት እንደዚሁ ነው።

ሐ. « የሙታን ትንሣኤ ደግሞ እንዲሁ ነው። በመበስበስ
ይዘራል፣ ባለመበስበስ ይነሣል፤ በውርደት ይዘራል፣
በክብር ይነሣል፤ በድካም ይዘራል፣ በኀይል ይነሣል፤
ፍ⌒ረታዊ አካል ካለ መንፈሳዊ አካል ደግሞ አለ»
(ቊጥር 42-44)

በዚህ ክፍሉ ውስጥ አራት ጥንድ ነገሮች ተነጻጽረዋል። በመበስበስ፣ ባለመበስበስ፤ በውርደት፣ በክብር፤ በድካም፣ በኀይል፤ ፍጥረታዊ፣ መንፈሳዊ። የመጀመሪያዎቹ ሦስቱ ጥንዶች ስለሚሞተው አካል የተሰጡ አሉታዊ ገለጻዎች ናቸው። መበስበስ፣ ውርደት፣ ድካም ከመጀመሪያው አዳም የተወረሱ የኀጢአት ውጤቶች

---
[3] F.F Bruce. The Acts of the Apostles. The Greek Text with Introduction& Commentary zd ed. (Grand Rapids : Eerdmans, 1952)ገጽ 340 (on Acts 17:32)

ናቸው። በመጀመሪያዎቹ ሦስት ጥንዶች ውስጥ ስለ ትንሣኤ አካል የቀረቡት ገለጻዎች የሚያሳዩት፣ አሉታዊ የሆኑት የውድቀት ውጤቶች እንደሚለወጡ ነው። በክፍሉ ላይ የቀረቡት የጳውሎስ ማስረጃዎች የሐሳብ ፍሰታቸው ወጥነት ያለው ነው። አራተኛውም ጥንድ እንደ ላይኞቹ አብረው የተነጻጸሩ ናቸው፤ ይኸውም ለውድቀት መንሥኤ ስለ ሆነው አካልና ከውድቀት ለመነሣት ምክንያት ስለ ሆነው አካል ነው። «ፍጥረታዊ አካል» የተባለው የኀጢአት አሉታዊ ውጤት የሆነው ነው። በኦሪት ዘፍጥረት መጽሐፍ ላይ እግዚአብሔር አምላክ አዳምን ከምድር ዐፈር እንዳበጀው፣ ይህንንም አካል፣ «መልካም ነው» እንዳለው እንመለከታለን (ዘፍ 1÷26-31)።

አንደኛ ቆሮንቶስ 2÷14-15 ስለ፣ «መንፈሳዊ ሰው» ይናገራል። «መንፈሳዊ ሰው» ማለት ግን ቁስአዊ አካል የሌለው የማይታይ፣ የማይዳሰስ ረቂቅ አካል (መንፈስ) ብቻ የሆነ ማለት አይደለም። ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ ቊጥጥር ሥር ያለ ማለት ነው።

በአጠቃላይ፣ «ፍጥረታዊ አካል» በእግዚአብሔር ቢፈጠርም እንኳ፣ እግዚአብሔር በመጀመሪያ፣ «መልካም ነው» ቢለውም እንኳ፣ ይህ አካል በኀጢአት ምክንያት ተበላሽቶአል።

መ. « እንዲሁ ደግሞ ፊተኛው ሰው አዳም ሕያው ነፍስ ሆነ
ተብሎ ተጽፎአል፤ ኋለኛው አዳም ሕይወትን የሚሰጥ
መንፈስ ሆነ» (ቊጥር 45)

በዚህ ክፍል ላይ የተነጻጸሩት ነፍስ (በግሪክ፡- ሱቺ) እና መንፈስ (በግሪኩ፡- ኒውማ) መፈታት ያለባቸው ከቊጥር 44 አንጻር ነው። ስለዚህ በቊጥር 44 ላይ ያለው ንጽጽር በሚሞተውም አካል [ለኀጢአትና ለውጤቱ ስለባ (ተጠቂ) ተጽዕኖ ውጪ የሆነው] መካከል ነው። በቊጥር 45 ላይም የምናገኘው ንጽጽር ይህንኑ ነው።

አዳም በተፈጠረበት ጊዜ ኀጢአተኛ ስላልነበር የኀጢአት ጥቃት አልደረሰበትም:: ነገር ግን በኀጢአት በመውደቁ ተበላሸ፣ ረከሰ፣ ደከመ፣ ሙት ሆነ::

ሠ. «የፊተኛው ሰው ከመሬት መሬታዊ ነው፤ ሁለተኛው ሰው ከሰማይ ነው» (ቊጥር 47)

ይህ ክፍል ኢየሱስን ሰው ይለዋል:: ለኀጢአት ክፍያ ኢየሱስ ሰው መሆኑ ቀርቶአል ከሚለው ከይሖዋ ምስክሮች ትምህርት ጋር በቀጥታ ይጣረሳል::

የትንሣኤ አካል ዐፈር ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን ለሕይወት ብቁ እንዲሆን የተለወጠ ነው (ቊጥር 48)::

ረ. «. . . ሥጋና ደም የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊወርሱ አይችሉም፤ የሚበሰብሰውም የማይበሰብሰውን አይወርስም» (ቊጥር 50)

የይሖዋ ምስክሮች አብዛኛውን ጊዜ የመጀመሪያውን ዐረፍተ ነገር መጥቀስ ይወዳሉ:: ይሁን እንጂ ተከታዩ ዐረፍተ ነገር ነገሩን ግልጽ ያደርገዋል:: የሚሞተው አካላችን ችግሩ ቊሳዊ አካል መሆኑ ሳይሆን ፈራሽ፣ በስባሽ መሆኑ ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ፣ «ሥጋና ደም» የሚለውን አገላለጽ በምድር ብቻ የተወሰነ መሆንን፣ ድካምን የሚገልጽ ሥዕላዊ ቋንቋ ነው (ማቴ 16÷17፤ ገላ 1÷16፤ ኤፌ 6÷12፤ ዕብ 2÷14)

«የእግዚአብሔርን መንግሥት» ያለመውረሳችን ምክንያት ከሥነ ምግባር ውድቀት የተነሣ ነው (1ቆሮ 6÷9-10፤ ገላ 5÷21)፤ ስለዚህ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ ቊሳዊ አካልን መተው ሳይሆን (1ቆሮ15÷50)፣ የተበላሸውን ሁኔታችንን የሚያድስና የሚያስተካክል የመንፈስ ቅዱስን ሰማያዊ ሕይወት ማግኘት ነው(1ጴጥ 1÷4)::

ሰ. «. . . ሙታንም የማይበሰብሱ ሆነው ይነሣሉ፤ እኛም እንለወጣለን:: ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሊለብስ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን ሊለብስ ይገባዋል» (ቊጥር 52-53)

ጳውሎስ በዚህ ክፍል እያጠናከረ ያለው ትምህርት ሥጋና ደም የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ የግድ መለወጥ እንደሚያስፈልገው ነው:: እርሱን በማጥፋት መንፈሳዊ በሆነው አካል (ኢቊሳዊ አካል) በመቀየር አስፈላጊ አይደለም:: ይህ የተበላሸውና ሟች የሆነው ሥጋዊ አካል የማይሞተውንና የማይበሰብሰውን መልበስ ያስፈልገዋል:: ይህ አሁን ያለው አካላችን ቀጣይነት ይኖረዋል፤ ነገር ግን የሚፈርሰው የሚበሰብሰው ክፍል ሊለወጥ ይገባዋል::

ሸ. «. . . በዚያን ጊዜ ሞት ድል በመነሣት ተዋጠ ተብሎ የተጻፈው ቃል ይፈጸማል» (ቊጥር 54)::

ትንሣኤ፣ ሞትን ድል የሚያደርገው የሚሞተው አካል በሕይወት ሲታደስ ነው::

ክፍል ዐሥር

ደኅንነት በሥራ ወይስ በጸጋ?

ሀ. ደኅንነት እንደ ይሖዋ ምስክሮች አስተምህሮ?

የይሖዋ ምስክሮች ደኅንነት የሚገኘው በሥራ መሆኑን ያምናሉ:: ደኅንነት ክርስቶስን በማመን፣ በጸጋ ይገኛል ለሚለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት የሚሰጡት የከንፈር አገልግሎት ብቻ ነው:: ደኅንነት ለይሖዋ ምስክሮች፣ ለመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ሙሉ ለሙሉ ከመገዛትና በሚያወጣቸውም ፕሮግራሞች ተካፋይ ከመሆን ውጪ የሚታሰብ አይደለም:: ከመጠበቂያ ግንብ ማኅበር ጽሑፎች ጥቂቶቹን[1] እንመልከት:- «ደኅንነት ለማግኘት ወደ ይሖዋ ድርጅት ይምጡ»[2]:: «እግዚአብሔር የግንኙነት ድልድይ አድርጎ ከሚጠቀምበት [የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት] ጋር ግንኙነት ከሌለን የቱንም ያህል መጽሐፍ ቅዱስን ብናነብ በሕይወት ጐዳና ልናድግ አንችልም»[3]:: «የዘላለምን ሕይወት ለመሸለም ጠንክረን መሥራት አለብን»[4]:: «አንድ ሰው በሕይወት መጽሐፍ ላይ ስሙ እንዲጻፍለት በሥራው ሊደገፍ ይገባዋል»[5]::

እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ የመጠበቂያ ግንብ ጽሑፎች በማንበብ የይሖዋ ምስክሮች እንዴት የእግዚአብሔርን ጸጋ ሊረዱ ይችላሉ? እንደ መጠበቂያ ግንብ ጽሑፎች ጸጋ ማለት ደኅንነትን

---

[1] ሰፊ ማብራሪያ ከፈለጉ ተስፋዬ ሮበሌ የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮአቸው በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን ገጽ 104-122 ይመለቷል::
[2] The Watchtower, 15 November 1981 ገጽ 21 በቅንፍ ያለውን አይጨምርም::
[3] The Watchtower, 1 December 1981 ገጽ 1981 ገጽ 27 በቅንፍ ያለውን አይጨምርም::
[4] The Watchtower 15 August 1972 ገጽ 491::
[5] The Watchtower, 1 April 1947 ገጽ 204::

ለመሥራት የሥራ ዕድል ማግኘት ማለት እንጂ፣ ጸጋ የደኅንነት ነጻ ስጦታ ማለት አይደለም::

የይሖዋ ምስክሮች ለመዳን የጸጋን አስፈላጊነትና በክርስቶስ የማመንን አንገብጋቢነት ይናገራሉ:: ደኅንነትም «ነጻ ስጦታ» ነው ይላሉ:: ነገር ግን እንደ መጠበቂያ ግንብ ጽሑፎች ጸጋና እምነት በራሳቸው በቂ አይደሉም:: ደኅንነትም በእምነት ብቻ የሚገኝ ነጻ ስጦታ አይደለም::

እንደ መጠበቂያ ግንብ ትምህርት የይሖዋ ምስክሮች በዚህ ሕይወት ደኅንነት ይኑራቸው ወይም አይኑራቸው በፍጹም እርግጠኞች አይደሉም[6]::

የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር የደኅንነት አስተምህሮ፣ ክርስቲያኖችን በሁለት ጐራ ይከፍላቸዋል:: እነዚህንም «ቅቡዓን» እና «ታላቁ መንጋ» በማለት ይለዩአቸዋል:: «ቅቡዓን» የእግዚአብሔር የመንፈስ ልጅ ሆነው ወደ ሰማይ ይሄዳሉ:: እነዚህንም ሰዎች በሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩና ከ1935 ዓ.ም. በፊት ድርጅቱን የተቀላቀሉ ናቸው «የታላቁ መንጋ» አባላት ትንሣኤን ካገኙ በኋላ በምድር ላይ ለዘላለም ይኖራሉ:: «ታላቁ መንጋ» በ1935 ዓ.ም የሰማይ ቤት ከሞላ በኋላ ድርጅቱን የተቀላቀሉ ሲሆኑ፣ እስከ አሁን ድረስ በምድር ላይ ያሉ ናቸው:: «ቅቡዓን» ሆነው ዛሬ በምድር ላይ የሚገኙት «ቅሬታዎች» በመባል ይታወቃሉ:: ደኅንነት የሚገኘው በክርስቶስ በማመንና ተግቶ በመሥራት ነው:: እንደ መጠበቂያ ግንብ ትምህርት ደኅንነት የሚገኘው ሕይወትን በመቀየር ለአምላክም መንግሥት ብቁ መሆንን በማረጋገጥ ነው::

[6] Life Everlasting- In-April 1947 ገጽ 204::

እንደ ድርጅቱ አስተምህሮ ዳግም ልደት የሚያስፈልጋቸውና ዳግም ልደት ያገኙትም፣ «ቅቡዓኑ» ብቻ ናቸው:: የእነርሱም ቍጥር 144 ሺህ ነው:: «ቅቡዓን» ዳግም ልደት ያስፈለጋቸው ምክንያት፣ በሰማይ መንፈስ ሆነው ለመኖር እንዲያግዛቸው ነው::

ድርጅቱ ይህን ትምህርት ለማስተማር ፈቅደውልኛል የሚላቸውን የቃለ እግዚአብሔርም ንባባት፣ ከራሱ ከድርጅቱ ጽሑፎች እየጠቀስን በመጽሐፍ ቅዱስ እንመዝናቸዋለን::

የይሖዋ ምስክሮች ምን ይላሉ:- ክርስቲያኖች በሁለት ጐራ (ቡድን) ይከፈላሉ[7]:: በራእ 7÷2-8 መሠረት፣ «ቅቡዓን» ወይም 144 ሺዎቹ በአንደኛው ጐራ ሲሆኑ፣ በራእ 7÷9-17 ላይ ደግሞ፣ «ታላቁ መንጋ» ወይም «በግ» የሚባሉት ደግሞ የሚገኙበት ሁለተኛው ጐራ ነው[8]:: 144ሺዎቹ ከሰማያዊ ተስፋ ጋር መንፈሳዊ እስራኤሎች ናቸው:: የሚኖሩትም በጽዮን ተራራ ላይ ነው (ራእ 14÷1):: ይህም የሰማይ ምሳሌ ነው (ዕብ 12÷22):: «ቅቡዓን» ከምድር ወደ ሰማይ ይሄዳሉ (ራእ 14÷3):: ወደፊት «ቅቡዓን» ሆኖ በምድር ላይ የሚኖር የለም:: 144 ሺዎቹ ሁሉ የእስራኤል ዘሥጋ [በሥጋ የእስራኤል] ወገን መሆን የለባቸውም:: አዲሱንም ዝማሬ የሚዘምሩት የእስራኤል ወገን ክርስቲያኖች ብቻ የሚሆኑበት ምንም ዐይነት ምክንያት የለም:: ነገር ግን የአሕዛብ ክርስተያኖችም ጭምር ናቸው:: ስለዚህ 144 ሺዎቹ እስራኤል ዘነፍስ [መንፈሳዊ እስራኤል] ናቸው::

መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል: - ሁለት ዐይነት ክርስቲያኖች አሉ የሚለው የይሖዋ ምስክሮች ትምህርት ሙሉ በሙሉ የተመሠረተው፣ ከአዲስ ኪዳን መጻሕፍት መካከል በጣም አከራካሪና ለመረዳትም እጅግ አስቸጋሪ በሆነው በራእይ መጽሐፍ ላይ ነው (ራእ 7 እና 14÷1-5)::

[7] በምድር ላይ በገነት ለዘላለም መኖር ትችላለህ፤ ገጽ 120-126::
[8] "Great Crowed" In Sight on the Scriptures, 1 ገጽ 995-97

144 ሺዎቹና በራእ 7 ላይ ያለው ታላቁ መንጋ የተለያዩ ክፍሎች ናቸው፣ የሚለው የመጠበቂያ ግንብ ትምህርት ፈጽሞ ትክክል አይደለም። እንደ ድርጅቱ ትምህርት 144 ሺዎቹ በቀጥታ ተተርጉሞ እስራኤላዊ ክርስቲያኖች ናቸው ሲባል፣ ታላቁ መንጋ ደግሞ ከተለያየ ነገድ ያመኑ ክርስቲያኖች ናቸው። ነገር ግን የክፍሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት 144 ሺዎቹም ሆኑ ታላቁ መንጋ ሕዝበ ክርስቲያንን የሚወክሉ ናቸው፤ ይኸውም ቤተ ክርስቲያን ማለት ነው። 144 ሺዎቹ በምድር ላይ በሚመጣው ቍጣ በእግዚአብሔር ማኅተም የተጠበቁ (ራእ 7÷1-8) እንዲሁም ቍጣው እስከሚያልፍ ድረስ በድል የቆሙ ናቸው (ራእ 14÷1-5)። ታላቁም መንጋ የሚወክለው ቤተ ክርስቲያንን ሲሆን፣ ይኸውም ከታላቁ መከራ በኋላ ባለማቋረጥ ለእግዚአብሔር የሚሰጠውን አምልኮ በማሳየት ነው (ራእ 7÷9-17)።

አንድ መቶ አርባ አራት ሺዎቹ ያሉት በሰማይ ሳይሆን በምድር ነው (ራእ 7÷1-8) ። አራቱ መላእክት ምድርንና ባሕርን ከመጒዳታቸው በፊት በእግዚአብሔር እንዲጠበቁ የታተሙ ናቸው። በተጨማሪም 144 ሺው በጽዮን ተራራ ላይ ቆመው ሳለ (ራእ 14÷1) መዘምራን በላይ በሰማይ ይዘምሩ ነበር (ቍ2-3) ። በርግጥ የጽዮን ተራራ ሰማያዊትዋን ከተማ ሊወክል ይችላል (ዕብ 12÷22)፤ ነገር ግን ሰማያዊትዋ ከተማ ከሰማይ ወደ ምድር ወርዳለች (ራእ 21÷2)፤ በመንፈሳዊው አነጋገር ክርስቲያኖች አሁን በምድር እያሉ ወደ ጽዮን ተራራ ወጥተዋል (ዕብ 12÷22) ። 144 ሺዎቹ ሰማያዊውን ዝማሬ ለመማር ከሰው ዘር ውስጥ ብቸኞቹ ናቸው(ቍ3)። «ከምድርም ከተዋጁት» (ቍ3) የሚለው አገላለጽ የሚያመለክተው 144 ሺዎቹን ነው። ነገር ግን 144 ሺዎቹ ለዘላለም በሰማይ ይኖራሉ ማለት አይደለም። ነገር ግን በምድር ላይ ሊመጣ ካለው ቍጣ እንዲያመልጡ ወደ ሰማይ ከተወሰዱ በኋላ፣ እንደገና ወደ ምድር መመለሳቸውን ነው የሚያሳየው። አዲሲቷ ኢየሩሳሌም ብለን በምንጠራትም፣ «አዲስ» ምድር ላይ ይኖራሉ (ራእ 21÷1-2) ።

የይሖዋ ምስክሮች ምን ይላሉ፦ «ታላቁ መንጋ» የሚባሉት እንደ ፣ «ቅቡዓን» ሰማያዊውን አካላት ሳይሆን ምድርን ተስፋ የሚያደርጉት ናቸው። ታላቁ መንጋ ተስፋ የሚያደርጋት በረከት (ራእ7÷15-17) ምድርን መውረስ ነው (ራእ 21÷2-4) ። ታላቁ መንጋ፣ «በዙፋኑና በበጉ ፊት» ይቆማል (ራእ 7÷9)፤ ይህ ማለት ግን የታላቁ መንጋ ስፍራ በሰማይ ነው ማለት ሳይሆን፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነትና ሞገስ የሚያሳይ አገላለጽ ነው። ይህም አገላለጽ ኀጢአኞች በእግዚአብሔር ፊት እንደማይቆሙ ለማነጻጸር ነው (ራእ 6÷15-17)።

መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል ፦ የተባረከው ተስፋ ለታላቁ መንጋ ነው የሚለው የይሖዋ ምስክሮች አባባል ትክክል ነው (ራእ7÷15-17) ። በአዲሲቱ ምድር ለመኖር ተስፋ ከተሰጣቸውም ጋር አንድ ናቸው(ራእ 21÷2-4)። የበረከታቸውም መሠረት እግዚአብሔር በእነርሱ መካከል መኖሩ ነው። እነርሱም በእግዚአብሔርና በበጉ ዙፋን ፊት ይቆማሉ (ራእ 7÷9)። ምክንያቱም ከመጨረሻው ፍርድ በኋላ የእግዚአብሔር ዙፋን በአዲሲቱ ምድር ይሆናል (ራእ 21÷3) ።

የይሖዋ ምስክሮች ምን ይላሉ፦ ሁለት ዐይነት ክርስቲያኖች እንዳሉ የሚያሳየው ሌላው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል[9] (ራእ 1÷6፤ 5÷10፤ 20÷6) ነው። ነገሥታትና ካህናት የሚሆኑት ሰዎች ከሚመሩአቸውና በእግዚአብሔር ፊት ከሚወክሉአቸው ሰዎች የተለዩ ናቸው። ሉቃ 12÷32፤ ዮሐ 10÷16 ክርስቶስ መንግሥቱን የሚሰጠው፣ «ትንሽ መንጋ» አለው፤ ይህም መንጋ ከ «ሌሎች በጎች» የተለየ ነው[10]።

መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል፦ የይሖዋ ምስክሮች ሁለት ዐይነት ክርስቲያኖች አሉ ለሚለው ትምህርታቸው ማስደገፊያ ከላይ ካየናቸው

---

[9] ዝኒ ከማሁ ገጽ 997። ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር፤

[10] «ትንሹ መንጋ» የሚባሉት «ቅቡዓን» ናቸው። «ትልቁ መንጋ»፣ «ሌሎች በጎች» የሚባሉት ከመቶ አርባ አራት ሺው ውጪ ያሉት ናቸው።

ጥቅሶች በተጨማሪ የሚጠቅሱት (ራእ 1÷6፤ 5÷10፤ 20÷6) ነው:: ነገር ግን በክፍሎቹ መንግሥትና ካህናት የሚሉት ቃላት አሁን በከፊል ወደፊት በሙላት ቅዱሳን በእግዚአብሔር በረከት የሚደሰቱትን ደስታ የሚያሳይ አገላለጽ ነው:: እንደ «መንግሥት» ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን የልጅነት ግንኙነት ያመለክታል (ራእ21÷7):: እንዲሁም በአዲሲቱ ምድር ላይ የሚያሳዩትን ፍትሐዊ አገዛዝ ያሳያል (ዘፍ 1÷26-30፤ መዝ 8÷3-8):: «ካህናት» መሆናቸውም ከእግዚአብሔር ጋር በቀጥታ መገናኘት እንደሚችሉ የሚያመለክት ነው::

ሉቃ12÷32፤ ዮሐ10÷16 ክርስቶስ መንግሥትን እሰጣችኋለሁ ካለው፣ «ትንሹ» መንጋ፣ «ከሌሎች በጎች» ጋር ፍጹም ልዩነት የላቸውም:: ከላይ ያየናቸው የሉቃስና የዮሐንስ ወንጌላት ዐውዳቸው አብሮ የሚሄድ አይደለም:: እነዚህም ክፍሎች፣ «ታላቁ መንጋ» እና «ታናሹ መንጋ» ልዩነት አላቸው፤ ታናሹ መንጋ ታላቁን መንጋ ይመራል አይልም:: «ታናሹ መንጋ» የተባለበት ምክንያት በዚያን ጊዜ ይህ ኅብረት የክርስቶስ ትንሽ ኅብረት ስለነበር ነው:: ሁሉም ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን መንግሥት እስከፈለጉ ድርስ (ሉቃ 12÷32)፣ ለሁሉም ክርስቲያኖች ሁሉ የእግዚአብሔር መንግሥት ይሰጣቸዋል (ቊ 32):: የሚፈልግም ሁሉ ያገኛልና (ማቴ 7÷7-8) ::

ዮሐ 10÷16 ከመጠበቂያ ግንብ ትምህርት ጋር ይጣረሳል:: ይኸውም ወደፊት በጎች ሁሉ «አንድ መንጋ » ስለሚሆኑ ነው:: «ከዚህም በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ፤ » የዚህ አባባል ታሪካዊ ዳራ የሚጠቁመን ከዚህ በፊት ሌሎች አሕዛብ ማለትም ከእስራኤል ነገድ ውጪ የነበሩት በክርስቶስ፣ «አንድ መንጋ» መሆናቸውን የሚያስተምር ነው::

የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ስለ ቅቡዓን የሚያስተምረው ትምህርት ያለው ችግር ወደ ስድስት ሚሊዮን የሚደርሱትን ምድር

ናፋቂ የይሖዋ ምስክሮች ያለመሪ ሊያስቀራቸው ነው:: እንደ ድርጅቱ ትምህርት ወደ፣ «ቅቡዓን» የመቀላቀል ቊጥር (144 ሺህ) የሞላው በ1935 ዓ.ም ነው:: አሁን በምድር ላይ ያሉት የዚህ የ«ቅቡዓን» ክፍል አባላት[11] ቊጥር ከ5 ሺህ የሚያንስ ሲሆን፣ ዕድሜያቸውም ከ80 ዓመት በላይ ነው:: በቅርቡ እነዚህ፣ «የቅቡዓን» «ቅሬታዎች» ሞተው ያልቃሉ፤ ድርጅቱም ያለ መሪ ይቀራል::

የይሖዋ ምስክሮች ምን ይላሉ:- በእምነት ጸድቀናል፤ ነገር ግን ጽድቃችን ጊዜያዊ ነው፤ ዘላቂነት የለውም:: «ታላቁ መንጋ» በምድር ላይ ለዘላለም ይኖራል:: የእግዚአብሔር ጓደኛ ለመሆን ጸድቆአል (ያዕ 2÷23):: ለ«ታላቁ መንጋ» እንከን አልባ የመሆን ሥልጣን ወይም ደረጃ ተሰጥቶታል፤ ነገር ግን በሺህ ዓመቱ ጊዜ የመፈተኑ ጉዳይ በእንጥልጥል ላይ ያለ፣ ውሳኔ ያላገኘ ጉዳይ ነው:: ለአብርሃምም ሆነ ከክርስቶስ በፊት ለነበሩት ቅዱሳን በእግዚአብሔር ተስፋ የማመናቸው መሠረቱ፣ በእግዚአብሔር ፊት እንከን አልባ ናችሁ መባላችሁ መሠረቱ ነበር (ሮሜ 4÷20-22):: «ታላቁ መንጋ» ተብለው የተቈጠሩት ክርስቲያኖች በክርስቶስ ማመናቸው የክርስቶስ የማዳን ሥራው እግዚአብሔር እነርሱን እንደ፣ «ጻድቃን» እንዲመለከታቸው አድርጎታል (ማቴ 25÷34-46) :: ነገር ግን እምነታቸው ጽድቅ ሆኖ የሚቈጠርላቸው ለመልካም ሥራ ያላቸው ጥረትና ለእግዚአብሔር ፍቃድ ከመታዘዛቸው ጋር ተያይዞ ነው (ያዕ 2÷17-26):: «የታላቁ መንጋ» አባላት ጻድቃን መሆናቸው ገና አልተረጋገጠም:: የጻድቃን መሆናቸው የሚረጋገጠውም እስከ ሺሁ ዓመት መጨረሻ ድረስ በእምነት በመታዘዝ የቀጠሉ እንደሆነ ብቻ ነው::

የክርስቲያናዊ ማኅበር አባላት («ቅቡዓን») የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆን ጸድቀዋል (ዮሐ 1÷12-13)፣ ከኀጢአት ውጪ እንዲሆኑ

11. በሕይወት ያሉ « ቅቡዓን»፣ «ቅሬታ» በመባል ይታወቃሉ::

የተሰጣቸው ጊዜያዊ ሥልጣን በእምነት እስካሉ ጊዜ ድረስ ቋሚ ነው:: እንደ «ታላቁ መንጋ»፣ «ቅቡዓንም» ለደኅንነታቸው መልካም ሥራ መሥራት ይጠበቅባቸዋል:: «ቅቡዓን» የእግዚአብሔር የማደጎ ልጆች የሆኑት ለጊዜው ነው (ሮሜ 8÷15-16) :: ነገር ግን እውነተኛ ልጆች መሆናቸው የሚረጋገጠው በትንሣኤ መንፈስ ሆነው ከሙታን ሲነሡ ነው::

መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል:- ደኅንነት እምነትን ብቻ ሳይሆን ሥራንም ይጨምራል የሚለው የይሖዋ ምስክሮች ትምህርት ከቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት ጋር የሚጋጭ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ እምነት አስፈላጊ ነው ያለው፣ ያለ እምነት እግዚአብሔርን ማስደሰት ስለማይቻል ነው (ዕብ 11÷6) :: እውነተኛ እምነት ደግሞ መልካም ሥራን ፍሬው ያደረገ ነው (ያዕ 2÷14-26):: እግዚአብሔር ደኅንነትን ያዘጋጀው ለሚያምኑ ነው እንጂ፣ «እምነታቸውን በተግባር ላዋሉ» አይደለም:: «እምነትን በተግባር ማዋል» የሚለው ቃል፣ «ፒስትአ» ከሚለው የግሪክ ቃል የተተረጐመ ነው:: የቃሉም ትርጕም በአንድ ሰው ወይም ነገር መመካት ወይም ማመን ማለት ነው (ለምሳሌ:- ዮሐ 3÷16:18) :: ትክክለኛ እምነት በሥራውና በፍሬው ይታወቃል፤ ስለዚህ እምነት እንጂ፣ «እምነትን በተግባር በማዋል» አይደለም ለደኅንነት አስፈላጊው ቅድመ ሁኔታ (ለምሳሌ:- ዮሐ 3÷16:18፤ ሐሥ 16÷31፤ ሮሜ 1÷16-17፤ 3÷21-28፤ 2ተ1÷8-10) :: መቼም መልካም ሥራ እጅግ አስፈላጊ ነገር መሆኑ አያጠያይቅም:: ነገር ግን ለደኅንነት ቅድመ ሁኔታ አይደለም:: የመልካም ሥራ መጓደል ክርስቲያን ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር እንዳያሳይ ያደርገዋል፤ በመጽሐፍ ቅዱስ አጠ ራር ሥጋዊ ክርስቲያን ያስብለዋል (1ቆሮ3÷1-4):: ነገር ግን እምነት ብቻ የደኅንነትን በቂ ዋስትና ይሰጣል (ቲቶ 1÷16፤ 1ጴጥ 1÷5-10፤ ዮሐ 2÷3-4፤ 3÷9-10:14-15፤ 5÷2-3) ::

በእምነት መጽደቃችን ለጊዜው ሳይሆን ለዘለቄታው (ለዘላለም) ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ጓደኛ ለመሆን በጸደቁት፣

(ያዕ 2÷23) በ«ታላቁ መንጋ» እና የእግዚአብሔር ልጅ (ዮሐ 1÷12-13) ለመሆን በጸደቁት፣ «ቅቡዓን» መካከል ምንም ልዩነት አላደረገም:: ሁሉም በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው (ሮሜ 8÷13-14):: መጽሐፍ ቅዱስ ለሁለት ነገር መጽደቅንም ሆነ [ግማሹ፣ ለልጅነት፣ ግማሹ ጓደኛ ለመሆን] ሁለት ዐይነት ጽድቅ አለ አይልም::

እግዚአብሔር ምዕመናን ጸድቀዋል ያለው፣ ለጊዜው ወይም ወደፊት የሚጠብቃቸውን ፈተና የሚያልፉትን አይደለም:: ነገር ግን ለአንዴና ለዘላለም ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ የጸደቅነው ላሁን ጊዜ ብቻ ነው እንዲሁም ሺህ ዓመት የፈተና ጊዜ ነው አይልም (ዕብ 9÷27):: አብርሃምና ሌሎች ቅዱሳን ደኅንነታቸው የተረጋገጠው ወደፊት እምነታቸው ስለሚፈተን አይደለም፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን በማመናቸው ብቻ ነበር:: አሁንም ሰው መንግሥተ ሰማይን የሚያገኘው ልክ እንደ እነርሱ ነው (ማቴ 8÷11፤ ሉቃ13÷28፤ ገላ 3÷9):: በዚህ መልኩ የጸደቀው የአብርሃም እምነት ፍጹም ነበር (ያዕ 2÷22) :: ኖኅ «በእምነትም የሚገኘውን ጽድቅ ወራሽ ሆነ» (ዕብ 1÷17):: ሁሉም ክርስቲያኖች በክርስቶስ ኢየሱስ ሞት በማመናቸው ብቻ ጽድቃቸውን ዐውጀዋል፤ ደኅንነታቸውም የተጠበቀ ነው::

ደኅንነት የተከናወነ እውነት ነው (ሮሜ 5÷1-9):: በዚህም መሠረት ነው መጽሐፍ ቅዱስ በእርሱ ከቁጣው እንድናለን የሚለው:: እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል የሰጠን ነጻ ስጦታ ጽድቅና (ሮሜ 3÷22-24፤ 5÷15-16) የዘላለም ሕይወት (ሮሜ 6÷23) ነው:: ሁለቱም እጅ ለእጅ ተያይዘው የሚሄዱ ናቸው (ሮሜ 5÷17-18) :: የጸደቁ ጻድቃን ናቸው የሚከብሩት (ሮሜ 8÷20):: አማኞች ወደፊቱት የመከበራቸው ጉዳይ የተረጋገጠው በተከናወነው መሠረት

[ይኸውም:- በመጽደቃቸው] ላይ ነው:: የእግዚአብሔር የማደጎ ልጅ መሆናችን (ሮሜ 8÷15-16) ወደፊት በፈተና የሚገኝ ሳይሆን፣ የአሁን ጊዜ እውነታ ነው:: ሮሜ 8÷23 የማደጎ ልጅ መሆናችን የወደፊቱት ጊዜ የሚያሳይ ነው፤ ነገር ግን ይህ ማለት አሁን የእግዚአብሔር የማደጎ ልጅ አልሆንም ማለት ሳይሆን፣ የአሁኑ ልጅነታችን የሚገለጠው ወደፊት ነው ማለት ብቻ ነው (ቍ 18-19፤ 1ዮሐ 3÷1-2):: በአሁኑ ጊዜ ያለነው የማደጎ ልጅነታችንን መገለጥ እየተጠባበቅን እንጂ፣ ለማደጎ ልጅነታችን እየሠራን አይደለም (ቍ23-24) ::

የይሖዋ ምስክሮች ምን ይላሉ:-መልካም ሥራ ደኅንነትን ያመጣል:: መልካም ሥራ የሚባሉት ከዚህ የሚከተሉት አራቱ ነጥቦች ናቸው:-[12]

1. በመጠበቂያ ግንብ መሪነት መጽሐፍ ቅዱስን በማጥናት የእግዚአብሔርንና የክርስቶስን ነገር፣ «ማወቅ»(ዮሐ 17÷3)::
2. ለእግዚአብሔር ሕግጋት መታዘዝ[13]::
3. የእግዚአብሔር ድልድይ (Channel) ከሆነው የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ጋር ኅብረት ማድረግ::
4. በይሖዋ ምስክሮች የስብከት ሥራ ላይ ተካፋይ መሆን::

መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል:- መልካም ሥራ ለደኅንነታችን ማረጋገጫ ቅድመ ሁኔታ አይደለም:: መጽሐፍ ቅዱስ የእምነት ትምህርቶች የሚቀዱበት፣ ደኅንነትም ሆነ መልካም ሥራ የሚገኙበት፣ በእግዚአብሔር ሥልጣናዊ ቃል እንደ ሆነ ይናገራል (2ጢሞ 3÷15-17):: የዘላለም ሕይወት የሚገኘው፣ «ዕውቀትን በመገብየት» ሳይሆን፣ እግዚአብሔርንና ክርስቶስን በ«ማወቅ» ነው

[12] The Watchtower, February 15, 1993 ገጽ 12-13::
[13] እነዚህ ሕግጋት በመጠበቂያ ግንብ ድርጅት በኩል የተደነገጉት ናቸው:: ከእነዚህም ውስጥ ደምን መስጠትና መቀበል (blood transfusions)፣ የልደት በዓላትን፣ የዓመት በዓላትን ወዘተ ማክበርን ይጨምራሉ::

(ዮሐ 17÷3):: ከአብና ከወልድም ጋር ግንኙነት የሚመሠረተውም በእምነት ነው:: ለደኅንነት የመጠበቂያ ግንብ ጽሑፎችን ማንበብ አለብህ የሚለው የመጠበቂያ ግንብ አስተምህሮ የእግዚአብሔርን የጽድቅ ሥራ ከንቱ ያደርገዋል (ሮሜ 3÷21-26):: እውነተኛ ክርስቲያን ባሕርይውን፣ ምግባሩንም ሆነ አስተሳሰቡን በእግዚአብሔር ቃል መቅረጽ አለበት:: ነገር ግን መልካም ሥነ ምግባር የደኅንነት መሠረት ሳይሆን የደኅንነት ፍሬ ነው:: ዛሬ በመጠበቂያ ግንብ በኩል የሚተላለፉት ሕግጋት[14]፣ በመጽሐፍ ቅዱስ የተሰጠ ትምህርት አይደለም:: እነዚህም ነገሮች የደኅንነትም ሆነ የቅድስና መሠረት ሊሆኑ አይችሉም::

መጽሐፍ ቅዱስ በአንድ የሃይማኖት ድርጅት ጥላ ሥር መጠለል ወይም ከድርጅቱ ጋር መተባበር ለደኅንነት መሠረት ነው አይልም:: እውነተኛ ክርስቲያኖች መሰሎቻቸውን መውደድ፣ ከእነርሱም ጋር ኅብረት ማድረግ እንዳለባቸው ያስተምራል (1ዮሐ 3÷14፤ 4÷20፤ 5÷1)::

ደኅንነት ከእምነት በስተቀር በምንም ነገር ላይ የተመሠረተ ስላልሆነ፣ በስብከትም ሆነ በማስተማር ሥራ ላይ ተካፋይ መሆን ለደኅንነት አንገብጋቢ ጉዳይ ተደርጎ የሚሠራጨው የመጠበቂያ ግንብ ትምህርት፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚጋጭ ነው:: ክርስቶስ ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ለወንጌል ሥራ ማሠማራቱም ሆነ (ማቴ 10÷5-42፤ ሉቃ 9÷1-6) ሰባ ሁለቱን መላኩ (ሉቃ 10÷1-16)፣ ለእኛ እንደ ምሳሌ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ክርስቲያናዊ ሕግ ልናደርገው ፈጽሞ አንችልም::

[14] ዝኒ ከማሁ::

የይሖዋ ምስክሮች ምን ይላሉ፦ «ዳግም ልደት» ለ144 ሺዎች ብቻ ነው[15]:: «ቅቡዓን» ለእግዚአብሔር መንፈስ የሚሆኑ ልጆች ናቸው:: መንፈስ እንደ መሆናቸውም በሰማይ ሆነው በምድር የሚገኘውን የእግዚአብሔር መንግሥት ያስተዳድራሉ (1ቆሮ 15÷50) :: ዳግም ልደት ለእነርሱ ያስፈለገበትም ዐላማ፣ በሰማይ ስለሚጠብቃቸው ሕይወት ወደ መንፈስነት ስለሚለውጣቸው ነው (ዮሐ 3÷4-5፤ ሮሜ 8÷16-17፤ 1ጴጥ 1÷3-4):: «ቅቡዓን» ዳግም መወለዳቸው የእግዚአብሔርን መንፈስ እንዲቀበሉ ያደርጋቸዋል:: ይህም መንፈስ ሰማያዊ ጥሪያቸውን ይገልጽላቸዋል እንዲሁም፣ «ልባምና ታማኝ ባሪያ» የመሆን ኀላፊነታቸውን እንዲወጡ ያበረታታቸዋል::

ዳግም ልደት ክርስቶስን ላመኑ ሰዎች ሁሉ አይደለም:: ነገር ግን በክርስቶስ ዘመን እስራኤላዊ ሆነው ክርስቶስን የተቀበሉት ዳግም ተወልደዋል::

መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል፦ ክርስቲያኖችን የሰማይ ወራሽ እና የምድር ወራሽ ብሎ ለሁለት መክፈሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እስካልሆነ ድረስ፣ የመጠበቂያ ግንብ ስለ ዳግም ልደት የሚሰጠው ትምህርት ትክክል ሊሆን አይችልም:: ክርስቲያኖች መንፈስ ሳይሆኑ የከበሩ ሰዎች ናቸው የሚሆኑት (1ቆሮ 15÷47-57) :: የትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ዳግም ልደት አንዱን ሰው መንፈስ ወደ መሆን ሕይወት ያሸጋግረዋል አይልም (ለምሳሌ 3÷3-5፤ ሮሜ 8÷16-17፤ 1ጴጥ 1÷3-4):: ስለዚህ፣ «ዳግም ልደት» እንደ መጠበቂያ ግንብ ትምህርት ለጥቂት ሰዎች ብቻ የሚሆን፣ ጥቂት ክርስቲያኖችን ሰማያዊ ጥሪ እንዳላቸው የሚጠቁም ወይም በሌሎች ክርስቲያኖች ላይ መሪና አለቃ እንዲሆኑ ኀይል የሚሰጥ አይደለም::

[15] ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር፣ ገጽ 75-78::

ዮሐ 1÷12-13 «ለተቀበሉት» የሚለው ግስ ዐላፊ ጊዜን ቢያሳይም እንኳን፣ በአሁኑ ጊዜ ሰዎች ዳግም አይወለዱም ማለት አይደለም:: የይሖዋ ምስክሮች ራሳቸው ብዙ ሰዎች ከእኛ መካከል ዳግም ልደትን አግኝተዋል ይላሉ:: ሐዋርያው ዮሐንስ ሁለት ዐይነት ሰዎች እንዳሉ፣ እነርሱም የእግዚአብሔር ልጆችና የሰይጣን ልጆች እንደሆኑ (1ዮሐ 3÷10):: ዮሐንስ ከእግዚአብሔር የተወለዱ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው ካለ (ዮሐ 1÷13) እንዲሁም ከእግዚአብሔር ያለተወለዱ የሰይጣን ልጆች ከሆኑ፣ ምዕመናን ሁሉ ዳግም ተወልደዋል ማለት ነው::

ለ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ደኅንነት ምን ያስተምራል[1]?

ክርስቲያኖች ሁሉ አሁንም ሆነ ወደፊት እኩል የሆነ ሥልጣን አላቸው:: ሁሉም ክርስቲያኖች በአዲሲቱ ምድር ይኖራሉ (ራእ 21÷1-4) :: አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ ምድር ከወረደች፣ የቅዱሳን መኖሪያ ምድር ናት ማለት ነው:: ይህም ለእግዚአብሔር ሕዝቦች መኖሪያ ተምሳሌታዊ (ሥዕላዊ) ገለጻ ነው:: ይኸውም ሕይወት ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሚመጣ፣ ወደፊት አዲስ ሕይወት በምድር እንደሚሆን ነው:: ዮሐንስ በመቀጠል እንዲህ ይላል:- « እነሆ፤ የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው፤ ከእነርሱም ጋር ያድራል፤ እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ:: እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናል፤ እንባዎችንም ሁሉ ከዐይኖቻቸው ያብሳል» (ቊጥር 3):: ክፍሉ ጥቂት የተመረጡ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ለመኖር ወደ ሰማይ ይሄዳሉ አይልም:: ነገር ግን እግዚአብሔር ራሱ ከሰዎች ጋረ ለመኖር ይመጣል፤ ዕንባዎችንም ሁሉ ከዐይኖቻቸው ያብሳል ነው የሚለው:: አሁን ክርስቲያኖች ወደ ሰማይ የሚሄዱት የትንሣኤን ቀን ለመጠበቅ ነው:: ነገር ግን እኛ ወደ መንግሥተ ሰማይ ሳይሆን የምንሄደው መንግሥተ ሰማይ ወደ እኛ ትመጣለች::

ራእይ 5÷10 ክርስቲያኖች፣ «በምድርም ላይ ይነግሣሉ» የሚለው ሀረፍተ ነገር በአዲሲቱ ዓለም ትርጒም (NWT)፣ «ከምድርም በላይ ይነግሣሉ» (Over the earth) ይለዋል:: ነገር ግን ይህ ትርጒም በመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ዘንድ ተቀባይነት የለውም:: በአዲስ ኪዳኑ ግሪክ «ሂፒ» የሚለው የግሪክ ቃል 63 ጊዜ፣ «ምድር» ከሚለው ቃል ጋር

---

[1] ይህ ክፍል የተወሰደው ተስፋዬ ሮበሌ የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮአቸው በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን ገጽ 114-118 ላይ ነው::

ተያይዞ ተጠቅሶአል። ነገር ግን አንድም ቦታ ላይ ከምድር በላይ ተብሎ አልተተረጐመም። ቃሉ በራእ 5÷10-13 ላይ የተተረጐመው በዚህ መልኩ ነው።

ክርስቲያኖች ሁሉ ትንሣኤ አግኝተው ዘላለማዊ ሕይወትን በአዲሲቱ ምድር ላይ ለዘላለም መኖር ከመጀመራቸው በፊት፣ በሰማይ ከክርስቶስ ጋር ይቆያሉ። በራእይ 7÷19-27 ላይ ያለው፣ «ብዙ ሕዝብ» እና በሰማይ ያለው ብዙ ሕዝብ መካከል ብዙ ተነጻጻሪ እውነታዎች አሏቸው። ይኸውም በሁለቱም ክፍሎች ላይ፣ «ብዙ ሕዝብ» የሚለው ቃል አለ (ራእ 7÷9፤ 19÷1:6)። በራእይ መጽሐፍ ውስጥ «ብዙ ሕዝብ» የሚለውንም ቃል የምናገኘው በእነዚህ ክፍሎች ላይ ብቻ ነው። በሁለቱም ክፍል ላይ ያሉት፣ «ብዙ ሕዝብ በታላቅ ድምፅ» ይጮኻሉ (ራእ 7÷10፤ 19÷1) የጩኸታቸውም አጀማመር አንድ ዐይነት ነው፣ «በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ለአምላካችንና ለበጉ ማዳን ነው» (7÷10)፣ «ማዳንና ክብር፣ ኀይልም የአምላካችን ነው» (19÷1)። በእነዚህም ሁለት ክፍሎች ላይ ብቻ ነው፣ «ማዳን የአምላካችን ነው» የሚለው ዐረፍተ ነገር የሚገኘው። ከዚህም በኋላ ሽማግሌዎቹና አርባእቱ እንስሳት [አራቱ ፍጥረታት]፣ «ወድቀው» ለእግዚአብሔር ይሰግዳሉ፤ የመጀመሪያ ቃላቸውም፣ «አሜን» (7÷11-12፤ 19÷4) የሚለው ነው።

ሉቃስ 23÷43 እንደ መጠበቂያ ግንብ ድርጅት ትምህርት ንስሓ የገባው ወንበዴ ለሰማያዊ ሕይወት ብቁ አይደለም። ምክንያቱም የክርስቲያናዊ ጉባኤ ተጠማቂ አባል ስላልሆነ፤ ነገር ግን ኢየሱስ ከእርሱ ጋር አሁን በገነት እንደሚሆን ቃል ገብቶለታል። ይህ የሚያሳየን አማኝ ሁሉ በሚሞትበት ጊዜ ነፍሱ ወይም መንፈሱ ሕያው [ንቁ] ስለሆነች ከጌታ ጋር ለመሆን ወደ ሰማይ እንደምትሄድ ነው።

ሁሉም ክርስቲያኖች የዘላለምን ሕይወት እኩል ይወርሳሉ። (ማቴ 5÷3-12) የተራራው ስብከት (ማቴ 5-7) የሚናገረው ስለ አንድ ሕዝብ እንጂ፣ ስለተለያዩ ሁለት ክፍሎች አይደለም። ኤፌ 4÷4 ክርስቲያኖች ሁሉ ያላቸው ተስፋ አንድ ብቻ መሆኑን ይነግረናል።

ጳውሎስ እንደሚለው ሁሉም ክርስቲያኖች፣ «የክርስቶስ አካል» ናቸው (ኤፌ 4÷3-4)። ክርስቲያኖች ሁሉ፣ «አንድ አካል» ከሆኑ የዚህ አካል ክፍል ያልሆነ፣ ክርስቲያን አይደለም ማለት ነው። በ1ቆሮ 12÷12-27 ላይ ጳውሎስ የአንድ አካል ብልቶች፣ አንዱ ከሌላው እንደሚሻል ወይም አንዱ ከሌላው እንደሚበልጥ አድርጎ ራሱን መቍጠር እንደሌለበት ያስተምራል [እንደ መጠበቂያ ግንብ ትምህርት አብዛኛው የይሖዋ ምስክር («ታላቁ መንጋ») የዚህ አካል ክፍል አይደለም]። ሮሜ 12÷4-8 ሌሎችን የሚያገለግሉ፣ የሚያበረታቱ፣ ምሕረትን የሚያሳዩ ወዘተ ክርስቲያኖች የክርስቶስ አካል እንደሆኑ ሁሉ የሚያስተምሩ፣ የሚመሩና የሚተነብዩም የክርስቶስ አካል ናቸው።

በጸጋው አማካይነት በእምነት የተገኘው ደኅንነት መልካም ፍሬ ያፈራል። በእምነት ብቻ የዳንን ሰዎች ብንሆንም እንኳ፣ የሚያድን እምነት መልካም ሥራን ፍሬው ያደረገ ስለሆነ፣ አማኝ የመንፈስ ፍሬ የሆነው መልካም ሥራ ይታይበታል። እምነት ብቻ ነው ደኅንነት የሚያገኙትንና ደኅንነት የማያገኙትን የሚለየው። ለዚህም ነው ቃለ እግዚአብሔር የእምነትን አንገብጋቢነት በስፋት የሚያስተምረው (ለምሳሌ፦ ዘፍ 15÷6፤ ዕብ2÷4፤ ዮሐ 3÷ 14-18፤ 20÷30-31፤ ሐሥ 16÷31፤ ሮሜ 1÷16-17፤ 3÷22-28፤ 4÷3-5፤ 5÷1-2፤10÷9-11፤ ኤፌ 2÷8፤ ቲቶ 3÷8፤ ዕብ 4÷2-3፤ 1ጴጥ 1÷5፤ 1ዮሐ 3÷23-24፤ 5÷10:13)።

እውነተኛ እምነት ታዛዥነትን የሚያፈራ፣ መልካም ሥራን የሚያሠራ፣ ፍቅርን የሚያሳይ ነው (ሮሜ 1÷15፣ 16÷25-26፣ ገላ 5÷6፣ ያዕ 2÷14-26) ፡፡ ለእግዚአብሔር ትእዛዝ ተገዥ ያልሆኑ ሰዎች በትክክል ያላመኑ ናቸው፤ በትክክል ያላመኑ ደኅንነት የላቸውም (1ቆሮ 6÷9-11፣ ገላ 5÷19-21፣ ኤፌ 5÷5-6፣ 1ዮሐ 3÷16፣ 2÷3-6፡9-11፣ 3÷6-15፣ ራእ 21÷8) ፡፡

ሐዋርያት፣ ክርስቲያን ኀጢአትን መሥራት ማቆም እንደሚገባውና፣ ቅድስናን ማጐልበት እንዳለበት ማስተማራቸው፣ እውነተኛ ክርስቲያን ከኀጢአት ጋር ዕለት በዕለት እንደሚታገል፣ ታግሎም ወደ ብስለትና ወደ ሥነ ምግባራዊ ዕድገት እንደሚመጣ ያሳያል፡፡ ክርስቲያን ከኀጢአቱ ጋር በመታገሉ ምክንያት ደኅንነቱም ሆነ በእግዚአብሔር ላይ ያለው እምነት በጥያቄ ውስጥ ሊገባ አይገባውም (ገላ5÷16-26፣ ኤፌ 4÷25-32፣ 1ተሰ 4÷1፣ ዮሐ 3÷17-18)፡፡

ሰዎችን ከዘላለም ሕይወት የሚያጐድላቸው ኀጢአት ብቻ ነው፡፡ ይኸውም፡- እውነቱን የማያምኑ፣ በክርስቶስም የሚያምነውን ሰው ከክርስቶስ የሚያርቁ ናቸው(ዕብ 2÷1-3፣ 6÷4-6፣ 10÷26-29፣ 2ጴጥ 2÷20-22፣ 1ዮሐ 5÷16)፡፡

ደኅንነት የእግዚአብሔር ስጦታ ነው፤ እኛ ልናደርገው የምንችለው ነገር ቢኖር በእምነት መቀበል ብቻ ነው፡፡ በእግዚአብሔር ላይ ያለን ትክክለኛ አቋም፣ እምነታችን፣ በቅድስና ማደጋችን፣ እስከ መጨረሻው በእምነት ጸንተን መቆማችን በእግዚአብሔር ጸጋና ኀይል ነው (ዮሐ 3÷16-17፣ ሐሥ 18÷27፣ 20÷24፣ ሮሜ 3÷23-24፣ 5÷15-21፣ ኤፌ 1÷18-19፣ 2÷4-10፣ ፊል 1÷6፣ ቲቶ 3÷7፣

ዕብ 4÷16፣ 1ጴጥ 1÷5)፡፡ ጸጋን ለማግኘት የምንሠራ ከሆነ፣ ታዲያ ጸጋ ምኑን ጸጋ ሆነ? [ጸጋ ማለት ነጻ የእግዚአብሔር ስጦታ ማለት ነውና (ሮሜ 4÷2-4፣ 11÷6፣ ገላ 2÷21)]፡፡

ዳግም የተወለዱ ክርስቲያኖች ሁሉ፣ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው (ዮሐ 3÷3-5)፡፡ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት ማለት በሚመጣው አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ላይ መኖር፣ ከበረከቱም ተካፋይ መሆን ማለት ነው (ማቴ 5÷19-20፣ 7÷21፣ 18÷3፣ 19÷23-25፣ 21÷31፣ ማር 9÷47፣ 10÷23-26)፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ያልተወለደ ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት አይችልም ካለ፣ ክርስቲያኖች ሁሉ ዳግሞ ሊወለዱ ያስፈልጋቸዋል ማለት ነው (ዮሐ 3÷3-5)፡፡

ሮሜ 8÷14-16 «በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ እነዚህ፣ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና» (ቊ14)፡፡ ክርስቲያኖች ሁሉ በመንፈስ መመራት ካለባቸው፣ በመንፈስ የሚመሩም የእግዚአብሔር ልጆች ከሆኑ፣ ክርስቲያኖች ሁሉ ያለ ጥርጥር የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው እውነት ነው፡፡ የባርነትን መንፈስ ካልተቀበልን፣ የተቀበልነው የልጅነትን መንፈስ ነው ማለት ነው (ቊ 15)፡፡ የልጅነትን መንፈስ የተቀበሉና እግዚአብሔርን «አባ» የሚሉ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው፡፡ ክርስቲያኖች ሁሉ እግዚአብሔርን አባ ማለት የሚችሉ ከሆነ፣ እግዚአብሔር ለክርስቲያን ሁሉ አባት ነው ማለት ነው፡፡ የእግዚአብሔር ልጆች እንደሆንን ያ መንፈስ የሚነግረን ከሆነ (ቊ16) አንድም የሃይማኖት ድርጅት የእግዚአብሔር ልጆች አይደላችሁም ሊለን አይችልም፡፡

በገላትያ 3÷23-4÷7 መሠረት፣ አሁን ክርስቶስን የሚያምን ሁሉ፣ ከሞግዚት በታች (ቊ 23-25) አይደለም፤ በእምነት በኩል ሁላችንም የእግዚአብሔር ልጆች ነን (ቊ 26)፡፡ ከክርስቶስ ጋር

የተጠመቀ ወይም እንደ ክርስቲያንነቱ ጥምቀትን የወሰደ ሁሉ፣ ክርስቶስን ለብሶታል (ቊ 27)። ክርስቶስንም የለበሰ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅ ነው (ቊ 26-27)፤ ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት በባርነት ቀንበር ሥር ነበርን። አሁን ክርስቶስ መጥቶአል፤ የእግዚአብሔርም ልጆች እንድንሆን ተዋጅተናል (4፥1-5፥7) ። ይህ የሚያመለክተን በክርስቶስ የተዋጀ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ እግዚአብሔርን አባ እንድንለው ያስተምረናል። ስለዚህ የእግዚአብሔር ልጆች እንደ ሆንን ልናውቅ ይገባል (4፥6፤ ሮሜ 8፥15-16) ።

አንደኛ ጴጥሮስ 1፥3፡12-23 ዳግም በመወለዳችን ሕያው ተስፋ አለን (ቊ 3) ይላል። ይህ የሚያመለክተን፣ ሕያው ተስፋ ያለው ሁሉ ዳግም እንደተወለደ ነው። መንፈሳዊ ፍሬ (ፍቅር፣ ቅድስና ወዘተ) ማፍራት የምንችለው ዳግም ስለተወለድን ብቻ ነው (ቊ 22-23) ።

አንደኛ ዮሐንስ 3፥9-10፤ 5፥1-2፡18-19 ክርስቶስ ነው ብሎ በኢየሱስ የሚያምን ሁሉ፣ ከእግዚአብሔር ተወልዶአል (5፥1) ይላል። እንደ ዮሐንስ ትምህርት፣ «ከእግዚአብሔር መወለድ» ማለት፣ የእግዚአብሔር ልጅ መሆን ማለት ነው (5፥1፤ 3፥9-10፤ 5፥18-19፤ ዮሐ 1፥12-13)። ዳግም መወለድ ማለት፣ በጸጋ ከእግዚአብሔር መወለድ ማለት ነው (ዮሐ 3፥3-5)። ዳግም ልደት የክርስቲያንን ሕይወት ስለሚለውጥ፣ ክርስቲያን ኀጢአት አያደርግም (1ዮሐ 3፥9-10፤ 5፥18፤ 2ቆሮ 5፥17)፤ ይህም ነው ዳግም መወለድን ለክርስቲያን አንገብጋቢ ጉዳይ የሚያደርገው።

ክፍል ዐሥራ አንድ
አብና ወልድ --- አንድ ወይስ ሁለት አካል?

«ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያንና»[1] ትምህርተ ሥላሴ

ኢየሱስ ክርስቶስ በምድራዊ ሕይወቱ፣ ደቀ መዛሙርቱን አበክሮ ካስጠነቀቃቸው ነገሮች መካከል አንዱና ዋነኛው፣ ራሳቸውን ከመናፍቃን መጠበቅ እንደላባቸው የሚገልጸው፣ ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ፣ «ልዩ ወንጌል» ማስጠንቀቅ የጀመረው በ55 ዓ.ም የገላትያን መጽሐፍ በጻፈበት ጊዜ ነው (ገላ1፥6-8)። ይህም ከክርስቶስ ዕርገት 20 እና 25 ዓመት በኋላ ማለት ነው።

እስከ አራተኛው ምእት ዓመት ድረስ ያልተነሣ የትምህርት ነፋስ ፍጹም እንደሌለ፣ የታሪክ ድርሳናት ስፌ ቦታ ሰጥተው አትተዋል። እንዲያውም የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን መሠረተ እምነቷን ደርዝ ባለው መልኩ ይፋ እንድታደርግ ያስገደዷት፣ በየዘመናቱ የተነሡት መናፍቃን ናቸው። ዛሬ የይሖዋ ምስክሮችና የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር ለሚባለው ድርጅት መሠረታዊ አስተምህሮ ጥርጊያ መንገድ የከፈተው፣ በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሣውና በጉባኤ ኒቅያ በጽኑ የተወገዘው፣ በእስክንድርያ

---

[1] ምሳሌን አስመልክቶ በሚያስተምሩት ትምህርትና በጥምቀት ቀመራቸው በተለምዶ « ኢየሱስ ብቻ » [" Jesus Only "] ይበሉ እንጂ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ በሕግ የሚታወቁት፣ «ሐዋርያት ቤተክርስቲያን» በሚል መጠሪያ ሲሆን፣ በዓለም ዐቀፍ ደረጃ የሚታወቁበት ስም ግን፣ «Oneness Pentecostal " " United Pentecostal Church International", " Pentecostal Assemblies of the World, Incorporated" " The Church of Jesus Christ" ወዘተ በሚለው ነው።

የአንድ ቤተ ክርስቲያን አለቃ የነበረው አርዮስ ነው:: ከአርዮስ በፊት በሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሣውና ቤተ ክርስቲያን አውግዛ ሰብአልዮስ (Sabellius) ለዛሬዎቹ «ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን» አባላት መንፈሳዊ አባት ነው:: «ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን» በመባል የሚታወቀውን መናፍቃዊ ድርጅት የመሠረተው ተክለማርያም ገዛኸኝ፣ «ኢየሱስን ማን ይሉታል?» በሚል ርእስ የተጻፈውና " The Identity of Jesus Christ" በሚል ወደ እንግሊዝኛ የተተረጐመው መጽሐፍ «የእነሰብአልዮስ ትምህርት የተመሠረተው በቈላ 2÷9 'የመለኮት ሙላት ሁሉ በክርስቶስ ውስጥ ተገልጦ ይኖራል' በሚል ነበር:: ዶክትሪናቸውንም ሲያብራሩ፣' አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ የአንድ አምላክ የመገለጫ ሞዴል እንጂ፣ ሦስትነትን አያንጸባርቅም፤ እግዚአብሔርም ሦስት ሰዎች ሆኖ ተገልጦ አያውቅም' . . . በኢሳ 9÷6 መሠረትም ኢየሱስ ክርስቶስ የዘላለም አባትና ኀያል አምላክ ነው»[2] በማለት ድርጅቱና ተከታዮቹ «ዳይናሚክ ሞናርኪያሊዝም» በመባል የሚታወቀውን የሰብአልዮስን አስተምህሮ እየተከተሉ እንዳሉ ይፋ አድርጎአል::

ኢትዮጵያዊው ምሁር አባ ጐርጐርዮስ፣ «የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ» በተባለው መጽሐፋቸው «ሰብአልዮስ በ3ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረ የሊብያ ሰው ነው:: በትምህርት ምክንያት ወደ ሮም ኼደ፤ ያን ጊዜ ሮም ዓለም ዐቀፍና የንጉሠ ነገሥት መዲና ስለነበረች፣ ብዙ የፍልስፍናና የሃይማኖት ሰዎች መሰብሰቢያም ነበረች፤ በዚህም ምክንያት ብዙ ክሕደትና መፈላሰፍም ይፈልቅባት ነበር:: ሰብአልዮስ በሮም እግዚአብሔር አንድ አካል ነው፣ አንድ ገጽ ነው፣ የሚለውን ትምህርት ተማረ:: ይህን የተማረው፣ 'አብ መከራ ተቀበለ' [Patripassians] ከሚሉ መናፍቃን ነው፤ እነዚህ መናፍቃን በሮም ያስተምሩት የነበረው፣ 'ሞዲሊስቲክ ሞናርኪያኒዝም' ይባላል:: አንዱ ገጽ በተለያዩ ዘመናት ቅርጹን ለውጦ ታየ ማለት ነው:: ሰብአልዮስ ይህን ኹሉ አግበስብሶ ወደ አገሩ ተመለሰ፤ ይህንኑም ማስተማር ጀመረ:: ሰብአልዮስ እንደሚለው አንዱ አካል ራሱ ማለት አብ ብሉይ ኪዳንን ስለ ሠራ አብ ተባለ፤ በዘመነ ሥጋዌ ሰው ሁኖ ሥጋ ለብሶ ስለ ታየና ሐዲስ ኪዳንንም ስለ ሰጠን ወልድ ተባለ፤ ኋላም በበዓለ ጰንጠቈስጤ በአምሳለ እሳት ወርዶ ለሐዋርያት ምስጢር በመግለጡ፣ ቋንቋ በማናገሩ መንፈስ ቅዱስ ተባለ እንጂ፣ አንድ አካል አንድ ገጽ ነው ብሎአል:: ይህ የሰብአልዮስ ትምህርት በማቴዎስ 28÷19፣ 'ወእንዘ ታጠምቅዎሙ በሉ በስመ አብ፣ ወወልድ፣ ወመንፈስ ቅዱስ' ባለው አምላካዊ ትምህርት ምስጢረ ሥላሴን ያፋልሳል»[3] ብለዋል::

ሞናርኪያኒዝም የሚለው ቃል የመጣው፣ «ሞናርኪያ» ከሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን፣ ከሰብአልዮስ በኋላ ትምህርቱ፣ «ዳይናሚክ ሞናርኪያኒዝም» እና «ሞዳልስቲክ ሞናርኪያኒዝም» በመባል ለሁለት ተከፈለ:: እንደ «ዳይናሚክ ሞናርኪያኒዝም» እምነት፣ ኢየሱስ እንደ ማንኛውም ሰው፣ ሰው ሆኖ ከተወለደ በኋላ ቅዱስ ሆኖ ስለተገኘ በዛ ያለ መለኮትነት ተሰጠው (ተቸረው) የሚል አቋም ነው:: እንደዚህ ትምህርት ኢየሱስ አምላክ የሆነው ከቀን በኋላ ነው:: «ሞዳልስቲክ ሞናርኪያኒዝም» ደግሞ፣ በአዲስ ኪዳን ላይ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የተባለው አንዱ አምላክ ራሱን በተለያየ መንገድ የገለጸበት መገለጥ ነው ባዮች ናቸው:: ይህም ማለት አንዱ እግዚአብሔር ራሱን በተለያዩ ጊዜያት አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አድርጎ ገልጾአል የሚል ነው:: ተክለማርያም ገዛኸኝ፣ እርሱና መሰሎቹ የሚከተሉትን ትምህርት ሲያብራራ:-

- «መለኮት ከዘላለም በአካል በባሕርይ በስም በግብር አንድ እንጂ ሁለት ወይም ሦስት አልነበረም:: በሦስት መንገድ ግን ራሱን ለሕዝቡ ገልጾአል:: በሦስት መንገድ የተገለጸበትም ምስጢር በአብነት በሥጋ ዐይን ሳይታይ፣ በወልድነት በሥጋ እየታየ፣

[2] ተክለማርያም ገዛኸኝ፤ ኢየሱስን ማን ይሉታል? (1978) ገጽ 4::

[3] አባ ጐርጐርዮስ (የሸዋ ሊቀ ጳጳስ) የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ (ቅዱስ ሲኖዶስ 1978 ዓ.ም) ገጽ 72:: በቅንፍ ያለውን አይጨምርም::

በመንፈስ ቅዱስነት እስትንፋሱን በሕዝቡ ልብ ውስጥ በማሳደሩ ተገልጠአል»[4]

- «ከጥንት ከዘላለም እግዚአብሔር ወይም መለኮት አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በመባል በሦስት አካላት ተከፋፍሎ አይጠራም ነበር»[5]
- «[ኢየሱስ] የመለኮት አካል እንዲሆን የተዘጋጀ ሰው ነው»[6]
- «አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ የአንዱ አምላክ መገለጫ አጠራር እንጂ፣ የመጠሪያ ስሞች አይደሉም. . .»[7]
- «አብ ራሱ ቅዱስ መንፈስ [መንፈስ ቅዱስ] ስለሆነም የሕይወትን እስትንፋስ ይዥውም ሕያው መንፈስ ቅዱስን ከራሱ (ከውስጡ) በማፍሰስ ፍጥረታትን ሕያዋን ያደርጋል»[8]
- « ይህ ሕፃን ሆኖ የተገለጠው አብም ወልድም ነው:: ሙሉ አምላክና ሙሉ ሰውም ነው. . . አብ ሰው ሆነ ማለት ሳይሆን፣ አብ በሥጋ ተገለጠ ማለት ነው»[9]
- «ይህም ከመጀመሪያው በእግዚአብሔር ውስጥ የነበረ የሕይወት ቃል፣ በድንግል ማርያም ማሕፀን ገብቶ ሰው ሆኖ ከተወለደ በኋላ በዚህ [ፍጹም ሰው በሆነው አካል] ውስጥ አብ ተዋሕዶ ተገለጠ»[10]
- «አማኑኤል የተባለበትም ምክንያት፡- ትርጓሜው እግዚአብሔር አብ በሥጋ ተገለጠልን፣ አየነው፣ ዳሰስነው ማለት ስለሆነ ነው»[11]
- «አብ በወልድ፣ ወልድም በአብ በውሕደት አሉ የሚለው የአንድ አምላክ ምስጢር መገለጥ ነው:: ስለዚህ እግዚአብሔር አብ ኢየሱስም ነው ብለን ማመንና ማሳመን እውነተኛ ሃይማኖት ነው»[12]
- « አብ በመለኮትነቱ ከወልድ ይበልጣልና ክርስቶስ ከእግ ዚአብሔር አብ ጋር በአንድ አካል ስለተዋሐደ ፍጹም አምላክና ሰው እንደሆነ ከዚህ በታች በተጠቀሱት ማስረጃዎች እናረጋግጣለን»[13]::

«ማስረጃ» ናቸው ከተባሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ ዋና ዋና የሚባሉትን፣ አንድ በአንድ እየነቀስን በማውጣት «ትክክለኛ ማስረጃ ናቸው ወይስ አይደሉም?» የሚለውን ከመመርመራችን በፊት፣ እስከ አሁን ያየናቸውን ዐዋጆች ጠቅለል እናድርጋቸው:: እንደ «ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን» መሠረተ እምነት፣ <u>እግዚአብሔር አምላክ፣ በሥጋ ዐይን ሳይታይ መንፈስ ሆኖ ይኖር ነበር:: በኋላ ግን ቃሉን ሥጋ ማለትም ኢየሱስ በማድረግ፣ ኢየሱስ በተባለው ሰው ውስጥ ዐደረ[14]:: ኢየሱስ በተባለው ሰው ውስጥ ካደረው አምላክ የሚወጣው እስትንፋስ ደግሞ ቅዱስ መንፈስ ወይም መንፈስ ቅዱስ ይባላል:: ስለዚህ አብ ማለት፣ ኢየሱስ በተባለው ሰው ውስጥ ያደረው አምላክ ሲሆን፣ ወልድ ደግሞ እግዚአብሔር ያደረበት ሰው ነው:: የአብ እስትንፋስ ወይም ትንፋሽ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ነው::</u> ድርጅቱ ይህን መሰል አስተምህሮ እንድይዝ አድርገውኛል የሚላቸውን የቃለ እግዚአብሔር ማስረጃዎችን ደግሞ ወደ መመርመሩ እንዝለቅ::

ኢየሱስ አብ ነውን?

ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ምን ይላል፡- «በኢሳይያስ 9፥6፡- 'ሕፃን ተወልዶልናልና ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነትም

[4] ተክለማርያም ገዛኸኝ፡<u>ኢየሱስን ማን ይሉታል</u>? (19. ዓ.ም) ገጽ 8::
[5] ዝኒ ከማሁ ገጽ 10::
[6] ዝኒ ከማሁ ገጽ 12:: በቅንፍ ያለውን አይጨምርም::
[7] ዝኒ ከማሁ ገጽ 19::
[8] ዝኒ ከማሁ ገጽ 20:: የመጀመሪያውን ቅንፍ አይጨምርም::
[9] ዝኒ ከማሁ ገጽ 40::
[10] ዝኒ ከማሁ ገጽ 41:: በቅንፍ ያለውን ይጨምራል::
[11] ዝኒ ከማሁ ገጽ 42::
[12] ዝኒ ከማሁ ::
[13] ዝኒ ከማሁ ::
[14] እግዚአብሔር ሰው አልሆነም ነገር ግን፡- « አብና ወልድ መለኮትና ሰው ናቸው» (ዝኒ ከማሁ ገጽ 79) « አብ ሰው ሆነ ማለት ሳይሆን፣ አብ በሥጋ ተገለጠ ማለት ነው» (ገጽ 40)

በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር ኀያል አምላክ፣ የዘላለም አባት፣ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል' የተባለለት ያ አንዱ ኀያል አምላክና የዘላለም አባት በሥጋ መምጣቱን ያስረዳል:: ይህ ሕፃን ሆኖ የተገለጠው አብም ወልድም ነው:: ሙሉ አምላክና ሙሉ ሰውም ነው. . . አብ ሰው ሆነ ማለት ሳይሆን፣ አብ በሥጋ ተገለጠ ማለት ነው. . .ክርስቶስ ከአብ የወጣ ቃል በመሆኑ የእግዚአብሔር አብ ሥጋ ነው»[15]::

መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል፡- ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አማኞችም ሆኑ፣ በድርጅቱ እየተዘጋጁ የሚወጡ ጽሑፎች[16]፣ ኢየሱስ ክርስቶስ አብ ነው ለማለት አዘወትረው የሚጠቅሱት ጥቅስ ኢሳ 9÷6 ነው:: ክፍሉ፣ «ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር አብ ነው» የሚል ትምህርት የለውም:: «በብሉይ ኪዳንም ሆነ በዕብራውያንና በዐረቡ ባህል፣ «አባት» ወይም በዕብራይስጡ ቋንቋ፣ «አብ» የሚለው ቃል በተጸውዖ ስምነት ካገለገለ የቃሉ ባለቤት (ቃሉ የተሰጠው ሰው) የተሰጠውን ስም የሚወክል ባሕርይ አለው ማለት ነው»[17]:: ለምሳሌ:- «አቢዓልቦን» (2ሳሙ 23÷31) የሚለው ድርብ ስም፣ «አቢ» ማለትም አባት ከሚለውና «ዓልቦን» ማለት ደግሞ ጠንካራ ከሚሉት ቃላት የተዋቀረ ሲሆን፣ በተገናኝ ሲነበብ [አጫፍረን ስናነበው]፣ «የጥንካሬ አባት» ወይም «ጠንካራ» ማለት ነው:: «አቢያሳፍ» (ዘፀ 6÷24) ማለት፣ «የመሰብሰብ አባት» ወይም «ሰብሳቢ» ማለት ነው:: «አቢጋኤል» (1ዜና 2÷16) ማለት፣ «ከፍ የማለት አባት» ወይም «ከፍ ያለ» ማለት ነው[18]:: አቢጋኤል የሚለው ስም የተሰጠው ለሴት መሆኑን ልብ ይሏል (አባት ነች ማለት ሳይሆን፣ ከፍ ያለች ነች ማለት ብቻ ነው)::

[15] ዝኒ ከማሁ ገጽ 40-41:: እንዲሁም ገጽ 31 ይመለከቷል::
[16] የድርጅቱን የእምነት አቋም የሚገልጸው፣ « የኢትትዮጵያ ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን የእምነት አንቀጾች» ጨምሮ አብዛኛዎቹ የድርጅቱ መጻሕፍት የተጻፉት የቤተ ክርስቲያኒቱ መሥራች በሆነው ተክለማርያም ገዛኸኝ በተባለው ግለሰብ ነው::
[17] Albert Barnes, "Notes on the Old Testament Explanatory and Practical Isaiah, " V0l. I (Grand Rapids, MI: Baker Book House, 1950 reprint), ገጽ 193::
[18] ተጨማሪ አስረጆችን ከፈለጉ:- Benjamin Davidson "The Analytical Hebrew and Chaldee Lexicon" (Peabody, MA:Hendrickson Publishers, 1981 trprint) ገጽ 93 ይመለከቷል::

በኢሳይያስ 9÷6 ላይ «አቢአድ» የሚለው የዕብራይስጥ ቃል፣ «የዘላለም አባት» ወይም ዘላለማዊ ማለት እንጂ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ አብ ነው ማለት አይደለም:: ይህ የሚያመለክተን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘላለማዊ አምላክ መሆኑን እንጂ (ዕብ 1÷2፤ 11÷3)፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ፣ «የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት» (2ቆሮ 1÷3) ነው ማለት አይደለም::

ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ምን ይላል፡- «ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐ 10÷30 እኔና አብ አንድ ነን ብሎ በማወጁ አብ ወልድ ውስጥ በውሕደት መኖሩን መግለጡ እንደሆነ እንረዳለን»[19]:: «እግዚአብሔር አብ የላከልን ልጅ ሰማያዊ ስለሆነ የባሕርይ ልጁ ነውና በአካል ከአብ የተለየ አይደለም:: ወልድ የአብ መልክ ነው:: 'እኔና አብ አንድ ነን' ብሎ በድፍረት መናገር የሚቻለው አብና ወልድ በውሕደት በአንድ አካል ውስጥ ስላሉ ብቻ ነው (ዮሐ 10÷30)»[20]::

መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል፡- ኢየሱስ፣ « እኔና አብ አንድ ነን» (ዮሐ 10÷30) ማለቱ፣ አብ ወልድን ማደሪያው ማድረጉን ወይም አብና ወልድ በአካል አንድ መሆናቸውን የሚገልጽ አይደለም:: እንዲያ ለማለት ካስፈለገ ኢየሱስ፣ «እኔ አብ ነኝ» ወይም «አብ እና ወልድ አንድ አካል ናቸው» ማለት ነበረበት:: «እኔና አብ አንድ ነን»፣ «አንድ ነን» ተብሎ ወደ አማርኛ የተተረጐመው፣ «ሄስሜን» ከሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን፣ ይህም የብዙን ቊጥር የሚያመለክት አንደኛ መደብ [we] ነው:: ኢየሱስ አብን ቢሆን ኖሮ፣ ቃሉ «ሄስሜን» የሚለውን ሳይሆን፣ አንደኛ መደብ ነጠላ ቊጥር የሆነው የሚያመለክተውን፣ «ሔይስ» የሚለውን የግሪክ ቃል መሆን ነበረበት::

[19] ተክለማርያም ገዛኸኝ፤ ኢየሱስን ማን ይሉታል? ገጽ 43::
[20] ዝኒ ከማሁ ገጽ 68::

በተጨማሪ «እኔና አብ አንድ ነን» ሲል «አንድ» የሚለው ቃል፣ «ሒን» ከሚለው የግሪክ ቃል የተተረጐመ ሲሆን፣ ይህም ግዑዝ ጾታን የሚያመለክት ነው:: ነገሩ የአብንና የወልድን የአካል አንድነት ለማመልከት ቢፈለግ ኖሮ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ለእግዚአብሔርም ሆነ ለኢየሱስ ክርስቶስ ተባዕታይ ጾታ እንደሚጠቀም የተባዕታይ ጾታ ይጠቀም ነበር::

የክፍሉ ዐውድ የሚያስተምረን አብና ወልድ አንድ አካል መሆናቸውን ሳይሆን፣ አብና ወልድ ባሕሪያቸው አንድ መሆኑን (essence) ለመግለጽ ብቻ ነው:: ኢየሱስ፣ «እኔና አብ አንድ ነን» ሲል፣ «አይሁድ ሊወግሩት ድንጋይ» ያነሡበትም ምክንያት (ቍ.31) ሕጋቸው፣ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር ያስተካከለ እግዚአብሔርን መሳደቡ ስለሆነ፣ በድንጋይ ይወገር ስለሚል ነው [ዘሌ 24÷16፤ ማቴ 26÷66፤ ማር 14÷64፤ ዮሐ 19÷7፤ ሐሥ 7÷58] :: ኢየሱስ በዚሁ ክፍል አብን፣ «አባቴ» (ቍ32) «የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ» (ቍ36)፣ ወዘተ የሚለውን ቃል እየተናገረ መልሶ ራሱን፣ እንዴት «አባት» ያደርጋል:: አብና ወልድ አንድ አካል ከሆኑ ኢየሱስ፣ «እኛም አንድ እንደሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ » (ዮሐ 17÷22) ብሎ ለደቀ መዛሙርቱ የጸለየው ጸሎት፣ የአካል አንድነት እንዲኖራቸው ነው ማለቱ ይሆን? (ዮሐ 10÷30 ከ17÷21-23 ጋር ያነጻጽሩ) ::

ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ምን ይላል፦ በዮሐንስ ወንጌል 5÷43፦ «እኔ በአባቴ ስም መጥቻለሁ» ተብሎ በተጻፈው ቃል . . . አንድ እውነተኛ አምላክና አንድ እውነተኛ ሰው በአንድ አካል እንዳሉ ማመን ያስፈልጋል»[21]:: «በአባቴ ስም» ማለት የኢየሱስ ስም የአብ ስም ነው ማለት ነው[22]::

[21] ዝኒ ከማሁ ገጽ 51::

[22] David Campbell, "All the Fullness" (WAP, 1975) ገጽ 43, John Paterson, " The Real Truth About Baptism in Jesus' Name " (PPH, 1953) , ገጽ 16::

መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል፦ ሁሉም የአዲስ ኪዳን ሊቃውንት እንደሚያስረዱት«በ----ስም» ማለት፣ « በ----ሥልጣን» ማለት ነው::

«በራሱ ስም» የሚመጣውን ሰው መቀበል፣ እንደ ጌታ ትምህርት ሞኝነት ነው:: «በአባቴ ስም» እና «በራሱ ስም» የሚሉት ሐረጐች ያለ ጥርጥር የሚያመለክቱት፣ ጌታ የመጣው፣ «በራሱ ስም» እንዳልሆነ ነው:: ስለዚህ፣ «ኢየሱስ» የሚለው ስም የአብ ስም እንዳልሆነና ኢየሱስም አብን እንዳልሆነ የሚያመለክት ነው:: የሚያስገርመው ግን ኢየሱስ አብን እንዳልሆነ የሚያስተምረውን ክፍል ኢየሱስ አብ ነው ለማለት እንደ መረጃ መቅረቡ ነው::

የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አማኞች፣ የኢየሱስ ስም የአብ ስም መሆኑን፣ ይህም ኢየሱስ አብ መሆኑን እንደሚያሳይ ከሚጠቅሷቸው ጥቅሶች መኻል ዮሐ 7÷6፡11-12 አንዱ ነው:: የድርጅቱ መምህራን ክፍሉ ኢየሱስ አብ መሆኑን እንደሚያስተምር ያስረዳሉ:: ይህ ትንታኔ ወላጅ አባት ስሙን ለልጁ እንደሰጠውና አባትና ልጅ አንድ አካል (ሕላዌ) ሆኑ እንደ ማለት ነው::

ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ምን ይላል፦ «በዮሐ 14÷6-11 ያለውን ቃል ስንመለከት የአብና የወልድ አካል በአንድ ሰውነት እንዳለ ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማይዋሽ ቃሉ ያረጋግጥልናል:: ኢየሱስም፦ «እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም:: እኔንስ ብታውቁኝ አባቴን ደግሞ ባወቃችሁ ነበር:: ከአሁንም ጀምራችሁ ታውቁታላችሁ፣ አይታችሁትማል አላቸው:: ፊልጽስም፦ 'ጌታ ሆይ አብን አሳየንና ይበቃናል አለው':: ሁለቱም በአንድ አካል እንዳሉ አላወቀም ነበር:: ኢየሱስም አለ፦ 'አንተ ፊልጶስ ይህን ያህል ዘመን ከእናንተ ጋር ስኖር አታውቀኝምን? እኔን ያየ አብን አይቶአል' እንዴትስ አንተ አብን አሳየን ትላለህ? እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ አታምንምን? እኔ የምነግራችሁ ቃል

ከራሴ አልናገረውም:: ነገር ግን በእኔ የሚኖረው አብ እርሱ ሥራውን ይሠራል እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ እመኑኝ» ይላል:: ከዚህ በላይ የተመለከትነው ምስክርነት እውነት ስለሆነ አብና ወልድ በአካል አንድ መሆናቸውን ልናምን ይገባል:: ውሕደቱም ከአንድያ ልጁ መሆኑን ብቻ አረጋግጠን ማመን ይኖርብናል::»[23]

መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል፦ በየትኛውም ዘመን ያሉ የሰብአልዮስ ደቀ መዛሙርት አብዝተው የሚጠቅሱት ጥቅስ በዮሐ 14÷6-11 ያለውን ክፍል ነው:: ክፍሉ ኢየሱስና እግዚአብሔር አንድ አካል ናቸው:: ወይም ኢየሱስ እግዚአብሔር አብ ነው አይልም:: ነገር ግን ኢየሱስ በሰዎችና በእግዚአብሔር መካከል ያለ መካከለኛ መሆኑን የሚገልጽ ነው:: ለዚህም ነው፣ «እኔን ብታውቁኝ ኖሮ አባቴንም ባወቃችሁት ነበር» (ቍ7ሀ) ያለው:: ይህ የሆነው ኢየሱስ አብ ስለሆነ ሳይሆን፣ ኢየሱስን በትክክል የሚያውቁት ሰዎች በእርሱ መካከለኛነት አብን በደንብ ያውቃሉና ነው:: ኢየሱስ የእግዚአብሔር አብ ገላጭ (ተራኪ) ነውና:: «ከአሁን ጀምሮ ግን ታውቁታላችሁ፤ አይታችሁታልም::» (7ለ):: ኢየሱስ፣ «እኔን ያየ አብን አይቶአል» (ቍ9) ወይም «እኔ በአብ እንዳለሁ፣ አብም በእኔ እንዳለ» የሚለው ሐረግ፣ መለኮት («አብ») በኢየሱስ ሰብአዊነት («ወልድ») ውስጥ እንዳለ የሚያሳይ ነው ይላሉ:: ነገር ግን ይህ ትንተና ከእርሱ በፊት ያለውን ማለትም፣ «እኔ በአብ እንዳለሁ» የሚለውን ሐረግ የመመለስ ዐቅም አይኖረውም:: በእነርሱ መንገድ ከፈታነው በአብ ውስጥ ሰባዊነት ይኖራል ማለት ነው:: አስገራሚው ጉዳይ በዚሁ ዐውድ ውስጥ እንዲሁም በሌላ ስፍራ ኢየሱስ ይህንኑ ዐይነት ገለጻ በመጠቀም ከአማኞች ጋር ያለውን አንድነት ገልጾአል «እኔ በአባቴ እንዳለሁ፣ እናንተም በእኔ እንዳላችሁ፣ እኔም በእናንተ እንዳለሁ በዚያን ቀን

[23] ተክለማርያም ገዛኸኝ፤ ኢየሱስን_ማን ይሉታል?(1978 ዓ.ም) ገጽ 68-69:: መስመሮቹን ይጨምራል::

ታውቃላችሁ» (ቍጥር 20 እንዲሁም 17÷21-23 ያለውን ክፍል ይመለከቷል)::

ኢየሱስ እግዚአብሔር (አምላክ) ነው

የሥላሴ አማኞች ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ መሆኑን ያምናሉ:: ነገር ግን አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው አይሉም:: ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ነው ማለት፣ እግዚአብሔር አብ ነው ማለት አይደለም:: የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር አብ ነው ለማለት የሚጠቅሱአቸውን ጥቅሶች ከዐውደ ምንባቡ አላቀው በመተርጐም፣ ለዐረፍተ ነገሩ አሰካክ፣ ለክፍሉ ሰዋስውና ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጽ ቦታ ሳይሰጡ ነው::

የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ምን ይላል፦ ጎርደን ማጂ በተባለው ሰው የተጻፈውና በስፋት የተሠራጨው በራሪ ጽሑፍ ቈላ 2÷9 በመጥቀስ ግጻዌ መለኮት [Godhead] በኢየሱስ ውስጥ ነው ያለው ይላል[24]::

ጎርደን ማጂ፣ « በእርሱ የመለኮት ሙላት ሁሉ በሰውነት ተገልጦ ይኖራልና» (ቆላ 2÷9) የሚለው ጥቅስ ኢየሱስ በግጻዌ መለኮት ውስጥ ሳይሆን (ግጻዌ መለኮት ሳይሆን) ግጻዌ መለኮት በኢየሱስ ውስጥ እንዳለ ያስተምረናል ይላል:: ይህንኑ ጥቅስ አስመልክቶ ተክለማርያም ገዛኸኝ እንዲህ ይላል፣ « በቈላ 2÷9-10 የተጻፈው ቃል የውሕደት ምስጢር ነው. . . ይህም ቃል መለኮት በክርስቶስ ውስጥ ተጠቃሎ በአንድ አካል ውስጥ እንዳለና ለዘላለም እንደሚኖር እንጂ፣ ከእርሱ ውጪ እንደማይታይ ያረጋግጥልናል . . . ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ ውጪ ብቻውን ሌላ አምላክ ነው የሚሉም ሁለት አምላክ የለምና

[24] Gordom Magee. Is Jesus in the Godhead or is the Godhead Jesus? (Pasadena, TX: Gordon Magee, n.d)

ከመጽሐፍ ቅዱስ ምንም ማስረጃ የላቸውም:: ትምህርት ባልነበረበት ዘመን የተፈላሰፉትን አዋልድ በመጥቀስ ለማሳመን ቢሞክሩም መጽሐፍ ቅዱስ ያወግዛቸዋል»[25]::

መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል:- የድርጅቱ መምህራን ቈላ 2÷9 በመጥቀስ ግጻዌ መለኮት በኢየሱስ ውስጥ ያለ እንጂ፣ ኢየሱስ በግጻዌ መለኮት ውስጥ አይደለም የሚለው ትንተና ዮሐ 10÷38 ላይ፣ «. . . አብ በእኔ እንደሆነ እኔም በአብ እንደ ሆንሁ ታውቁና ታስተውሉ ዘንድ» ከሚለው ትምህርት ጋር በቀጥታ ይቃረናል:: ግጻዌ መለኮት በኢየሱስ ውስጥ ነው ኢየሱስም በግጻዌ መለኮት ውስጥ ነው:: የድርጅቱ መምህራን፣ « ግጻዌ መለኮት በኢየሱስ ውስጥ ነው» ማለታቸው፣ ኢየሱስ ከሥላሴ አካላት አንዱ አይደለም ማለታቸው ነው:: ነገር ግን ቈላ 2÷9 እንዲህ ዐይነት ትምህርት የለውም:: ክፍሉ የክርስቶስን ፍጹም አምላክነት የሚያስረዳ እንጂ፣ ኢየሱስ አብ መሆኑን ወይም የሥላሴ አካላት ሁሉ በኢየሱስ ውስጥ መኖራቸውን አያስተምርም::

የኢየሱስ ስም

ድርጅቱ፣ «ኢየሱስ» በሚለው ስም ላይ ትልቅ ትኵረት ይሰጣል[26]:: የድርጅቱም እንቅስቃሴ የተጀመረው በማቴ 28÷19 ላይ ያለው የአብ፣ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ስም በሐሥ 2÷38 መሠረት የኢየሱስ ስም ነው በሚለው ትምህርት ላይ ነው:: ለዚህም ነው ድርጅቱ ተከታዮቹን በኢየሱስ ስም የሚያጠምቀው::

የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ምን ይላል፡- « በማቴ 28÷19 የተነገረው ቃል በነጠላ ቍጥር የተነገረ ስም ስለሆነ አንድን አምላክ

[25] ተክለማርያም ገዛኸኝ ኢየሱስን ማን ይሉታል? ገጽ 47::
[26] ተክለማርያም ገዛኸኝ፣ አዲስ ልደት (1987ዓ.ም) ገጽ 62-73::

ያመለክታል እንጂ፣ ስለ ሦስት አይናገርም. . . እግዚአበሔር በሥጋ ከመገለጡ ወይም ከድንግል ማርያም ከመወለዱ በፊት ሰዎችን ሊያድንበት ዐቅዶ በሰማያት ሰውሮ ያስቀመጠው የመለኮት (የአብ) ስም ኢየሱስ ነው:: መንፈስ ቅዱስም ከእግዚአብሔር ወይም ከኢየሱስ የሚፈስ የእግዚአበሔር ኀይል ነው:: ከቅዱስ አምላክ ስለሚወጣ መንፈስ ቅዱስ ይባላል፤ የመጠሪያ ስሙ ግን ኢየሱስ እንደሆነ በማቴ 1÷20-21 እና በ2ቆሮ 3÷17 ተገልጽአል. . .አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ እነዚህ ሦስቱ የእግዚአብሔር የክብር ስሞች የመጠሪያ ስሞቹ ቢሆኑ ኑሮ፣ ስም ተብሎ በነጠላ ቍጥር ከመጻፍ ይልቅ ስሞች ተብለው ሊጻፉ ይገባ ነበር:: ስም ተብሎ ስለተጻፈ ነጠላነትን ስለሚያሳይ ሐዋርያት ሳይሳሳቱ በዚህ በሦስት የክብር ስም የተጠራ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ በመንፈስ ቅዱስ ተረድተው፣ ኀጢአትን በሚያስተሰርይ በአምላካችንና በመድኀኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አጥምቀዋል:: እኛም በዚህ ስም እንድንጠመቅና እንድናጠምቅም በጥብቅ አዘዋል»[27]::

መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል፡- በማቴ 28÷19 ላይ የምንመለከተው የሰዋስው አወቃቀር አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የተለያዩ አካላት [Persons] መሆናቸውን ነው:: አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ በሚለው ስም ፊት የተጠቀሱት ሦስት የተወሰኑ መስተአምሮች (Definite Articles) አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የተለያዩ [distinct] መሆናቸውን ያመለክታል:: እንደ እንግሊዝኛው ሁሉ የግሪኩ ሰዋስው በስሞች ፊት የተወሰነ መስተአምር ኖሮ፣ ስሞቹ ተመሳሳይ ሙያ [case] ካላቸው፣ ስሞቹ የተለያየን አካል ይወክላሉ [ነገሩን ግልጽ ለማድረግ በእንግሊዝኛ ዐረፍተ ነገር እንጠቀም:- The black and the white dogs ስንል ጥቁርና ነጭ ቀለም ያላቸው ሁለት የተለያዩ ውሾች ማለታችን ነው:: ነገር ግን The black and white dog ካልን ግን ጥቁርና ነጭ ቀለም ያለው አንድ ውሻ ማለታችን ነው:: ልዩነቱን ያመጣው በመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር

[27] ዝኒ ከማሁ ገጽ 116-118::

ላይ፣ ነጭ ከሚለው ቅጽል በፊት የነበረው የተወሰነ መስተኣምር [The] ፣በሁለተኛው ዐረፍተ ነገር ውስጥ ያለመገኘቱ ነው።] በግሪክኛውም አብ (ፖትሮስ)፣ ወልድ (ሁዮስ) እና መንፈስ ቅዱስ (አግዮ ኑማቶስ) ከሚሉት ስሞች ፊት የተወሰነ መስተኣምር (ቶ [ዘርፍ ሙያ፣ የተወሰነ መስተኣምር]) አለ። ይህም አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የተለያዩ አካላት እንዳላቸው ፍንትው አድርጎ ያሳያል [ይህ አወቃቀር በእንግሊዝኛቹ ቅጆች ላይ በግልጽ ይታያል፡- In the name of The Father and of The Son and of The Holy Spirit] ::

ተክለማርያም ገዛኸኝ፣ « አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ እነዚህ ሦስቱ የእግዚአብሔር ስሞች የመጠሪያ ስሞቹ ቢሆኑ ኑሮ፣ ስም ተብሎ በነጠላ ቊጥር ከመጻፍ ይልቅ፣ ስሞች ተብለው ሊጻፉ ይገባ ነበር[28] ይላል። ነገር ግን፣ «ስም» ሳይሆን «ስሞች» መባል አለበት የሚለው የየትኛው ቋንቋ ሰዋሰው ነው? የአማርኛ፣ የእንግሊዝኛና የግሪክ ቋንቋዎች « ስም » የሚለው ነጠላ ቃል የብዙ ሰዎችን ስም ሊወክል ይችላል።

ከቃለ እግዚአብሔር አንዳንድ አስረጆችን እናቅርብ። « ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው፤ ባረካቸውም ። ስማቸውንም [Name] በፈጠረበት ቀን አዳም ብሎ ጠራቸው» (ዘፍ 5÷2)። ወንድና ሴት ሆነው የተፈጠሩት አዳምና ሔዋን ሁለት የተለያዩ አካላት ሆነው ሳለ «ስም» የሚለው ነጠላ ቃል ወክሎአቸው እናገኛለን [የዕብራይስጡን መጽሐፍ ይመለከቷል]። «. . . በምድርም ላይ ሳንበተንም ስማችንን እናስጠራው አሉ» (ዘፍ 11÷4)። የባቢሎንን ግንብ የሠሩት ሰዎች ብዙ ሆነው ሳለ፣ «ስማችንን» እንጂ «ስሞቻችንን» የሚለውን ቃል አልተጠቀሙም። «ከእነርሱም በኋላ የምትወልዳቸው ልጆች ለአንተ ይሁኑ፤ በርስታቸውም በወንድሞቻቸው ስም ይጠሩ» (ዘፍ 48÷6) ይላል እንጂ፣

[28] ተክለማርያም ገዛኸኝ፤ አዲስ ልደት (1987 ዓ.ም) ገጽ 63።

በወንድሞቻቸው «ስሞች» አይልም። «ከክፉ ነገር ሁሉ ያዳነኝ መልአክ እርሱ እነዚህን ብላቴኖች ይባርክ፤ ስሜም የአባቶቼ የአብርሃምና የይስሐቅም ስም በእነርሱ ይጠራ. . .» (ዘፍ 48÷6) ይላል ። አብርሃምና ይስሐቅ አባትና ልጅ ሆነው ሳለ «ስሞች» ሳይሆን «ስም» ነው የሚለው። ከቋንቋ ሕግጋት የምንማረው ነገር «ስም» የሚለው ነጠላ ቃል ብዙ ስምን ሊወክል እንደሚችል ነው። «. . . በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም. . .» መባሉ አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የኢየሱስ መጠሪያ («የማዕረግ ስም») መሆኑን አያመለክትም።

የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ምን ይላል፡- «የሐዋርያት ሥራ 2÷38 አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ እየተባለ የሚጠራው ያው ራሱ አንድ አምላክ ሲሆን፣ ለሰው ልጆች በሦስት አገላለጽ መገለጹን ያሳያል»[29]። ማቴ 28÷19 አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የሚለው በሐሥ 2÷38 መሠረት ኢየሱስ ክርስቶስን ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል፡- ማቴ 28÷19 አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ለየራሳቸው አካል ያላቸው መሆኑን (የተለያዩ አካላት መሆናቸውን) የዐረፍተ ነገሩ ሰዋስዋዊ አወቃቀር እንደሚያስረዳ ካላይ ለማየት ሞክረናል። ትክክለኛው የጥምቀት ቀመር «በአብ፤ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ» ስም ነው ወይስ፣ «በኢየሱስ ስም» (በማቴ 28÷19፤ ሐሥ 2÷38)? የሚለው ጥያቄ ነው።

በሐዋርያት ሥራ «በኢየሱስ ስም» የተጠመቁት በሥጋም ሆነ በሃይማኖት አይሁዳዊ የሆኑትን ሰዎች ብቻ ነው፡-
1. ዕብራውያን ሐሥ 2÷5፡ 38፤ 22÷16፤ 18÷1-8

[29] ዝኒ ከማሁ ገጽ 122።

2. ሳምራውያን ሐሥ 8÷5:12:16 (ሳምራውያን በአሶራውያን ዘመነ መንግሥት በምርኮ ሄደው ከአሕዛብ ጋር የተቀላቀሉ አይሁዶች መሆናቸውን ልብ ይሏል ዮሐ 4) ::
3. በትውልድ አሕዛብ ሆነው በኋላ ግን ወደ ይሁዲነት የገቡ ሐሥ 10÷12:22:48
4. የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ሐሥ 19÷1-5 [የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት አይሁድ መሆናቸው ይታወቃል፤ ምክንያቱም መጥምቁ ዮሐንስ የንስሓን ወንጌል የሰበከው፣ «አብርሃም አባት አለን» ላሉ አይሁዶች ነበርና ማቴ 3÷5:7:8:9] ::

በማቴ 28÷19 ላይ ያለው የጥምቀት ቀመር የተሰጠው ሐዋርያት ወንጌልን ይዘው ወደ አሕዛብ [Nations] እንዲሄዱ ትእዛዝ በተሰጠበት ጊዜ ነው:: በአዲስ ኪዳን ንባባት «አሕዛብ» የሚለው ቃል ከቤተ እስራኤል [ከእስራኤል ነገድ] ውጪ ያሉትን ነገዶች ሁሉ የሚያመለክት ነው፤ ስለዚህ አይሁድ «በኢየሱስ ስም» ሲጠመቁ አሕዛብ ደግሞ፣ « በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ይጠመቃሉ» :: አይሁድ በኢየሱስ ስም የሚጠመቁበት ምክንያት፣ በብሉይ ኪዳን የተገለጠውን እግዚአብሔርን በማምለክ ላይ ስለነበሩ ነው:: አሁን የሚያስፈልጋቸው ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ ማመን ነው:: አሕዛብ ግን ጣዖትን የሚያመልኩ ስለሆነና ወደ ክርስቶስ የሚመራውን የእስራኤልን አምላክ ስለማያውቁ፣ ኢየሱስ ጌታ መሆኑን ብቻ ሳይሆን በአብና በመንፈስ ቅዱስም ማመን ይገባቸዋል::

አብና ወልድ

እንደ ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ፣ አብ አምላክ ወልድ ደግሞ ሰው በመሆን አንድ አካል አላቸው የሚል ነው:: የድርጅቱ መምህራን፣ «አካል» የሚለውን ቃል የሚታይና የሚዳሰስ

ቁስ አድርገው ይመለከቱታል:: አካል የሚለውን ቃል መዳሰስና መታየት በሚለው መልኩ ከፈታነው፣ አካል ያለው ኢየሱስ ብቻ ነው ማለት እንችላለን:: የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አብ አካል አለው [Person]፣ እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ አካል አለው ስትል አብ በዐይን ይታያል፣ በእጅ ይዳሰሳል፣ መንፈስ ቅዱስ በዐይን ይታያል፣ በእጅ ይዳሰሳል ማለቷ ሳይሆን፣ ወልድ የራሱ የሆነ ማንነት ወይም ስሜት ፈቃድና ዕውቀት እንዳለው አብና መንፈስ ቅዱስም እንደዚሁ አላቸው ማለቷ ነው [እባክዎን «ህላዌ» ወይም «አካል» የሚለውን ቃል የአማርኛና የትምህርተ መለኮት መዝገበ ቃላት እንዴት እንደሚፈቱት ይመልከቱ] ::

መጽሐፍ ቅዱስ አብና ወልድ የተለያዩ አካላት መሆናቸውን በግልጽ ያስተምራል:: ኢየሱስ አገልግሎቱ ተአማኒነት ያለው ለመሆኑ አብን ምስክር ሲያደርግ እንመለከታለን (ዮሐ 5÷31-32፤ 8÷16-18) :: ኢየሱስ፣ «ስለ እኔ የሚመሰክር ሌላ ነው» (5÷32) ማለት እርሱ አብ እንዳልሆነ ያሳያል:: በግሪክ፣ «አሎሎስ» የሚለው ቃል ነው በአማርኛው «ሌላ» ተብሎ የተተረጐመው:: ይህም .«ከሚናገረው ሰው የተለየ»[30] ማለት ነው::

ኢየሱስ በዮሐ 8÷16-18 ላይ ብሉይ ኪዳን የአንድን ነገር ወይም ትክክለኛነት ለማወቅ ሁለት ምስክሮች በፍርድ ፊት መቅረብ አለባቸው የሚለውን ቃል በመጥቀስ (ዘዳ 17÷6፤ 19-15 እንዲሁም ዘኍ 35÷30 ይመለከቷል) የአገልግሎቱን ተኣማኒነት ያረጋግጣል:: የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን መምህራን የኢየሱስ አምላክነትና ሰብአዊነቱ ናቸው የሚመሰክሩት ይላሉ:: ነገር ግን ቃለ እግዚአብሔር ሁለት ምስክር ሲል ሁለት የተለያዩ አካላት መሆናቸውን ልብ ልናደርግ ይገባል:: አንድ ሰው በሸንጎ ፊት ቆሞ ምስክሮችህ የታሉ

[30] William F. Arrdt and F. Wilbur Gingrich, A Greek-English Lexicon of the New Testament and Other Early Christian Literature (Chicago University of Chicago Press, 1957) ገጽ 39::

ሲባል፣ አካሌና ነፍሴ ይመሰክሩልኛል ቢል ወይም አምላክነቴና ሰውነቴ ይመሰክሩልኛል ቢል የግለሰቡ ንግግር ምን ያህል እንደሚያስደንቀን መገመት ይቻላል:: የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በሸንጎ የሚቀርቡ ሰዎች ቢያንስ ሁለት ምስክር ያቅርቡ ሲል፣ ዛሬ በእኛ ዘመን ከሚደረገው የተለየ እንዳልሆነ ግልጽ ነው:: ኢየሱስ፣ «ስለ እኔ የምመሰክር እኔ ነኝ፤ የላከኝም አብ ስለ እኔ ይመሰክራል» (ዮሐ 8÷18) ሲል እርሱ አብ እንዳልሆነ በግልጽ ያመለክታል::

መጽሐፍ ቅዱስ አብ ላኪ ወልድ ደግሞ ተላኪ መሆኑን በግልጽ ያስተምራል (ዮሐ 3÷17፤ ገላ 4÷4፤ 1ዮሐ 4÷10):: ላኪና ተላኪ አንድ አካል ናቸው ካልን፣ ዮሐ 1÷6 ላይ « ከእግዚአብሔር የተላከ ስሙ ዮሐንስ የሚባል አንድ ሰው ነበረ» ከሚለው ቃል ተነሥተን፣ መጥምቁ ዮሐንስና እግዚአብሔር አንድ አካል ናቸው ልንል ነው ማለት ነው:: ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እርሱን አብ እንደላከው፣ እርሱ ደግሞ እነርሱን እንደሚልካቸው ገልጾአል (ዮሐ 17÷18፤ 20÷21):: ከእነዚህ ክፍሎች ተነሥተን በኢየሱስ የተላኩትን ሰዎች ኢየሱስ ናቸው እንደማንል ሁሉ፣ በአብ የተላከውንም ኢየሱስ አብ ነው ማለት በፍጹም አንችልም::

መጽሐፍ ቅዱስ አብና ወልድ እንደሚዋደዱ ያስተምረናል (ዮሐ 3÷35፤ 17÷23-26፤ 14÷31):: ይህም አብና ወልድ የተለያዩ አካላት መሆናቸውን የሚገልጽ ነው:: የኢየሱስ አምላክነት የኢየሱስን ሰውነት መውደዱ ነው ካልን፣ የአምላካዊነት ባሕርይ (nature) የሰብአዊነት ባሕርይ (nature) እንዴት ሊወድ ቻለ? የሚለውን ጥያቄ ያስከትላል:: መውደድ የአካል (Person) ነው ወይስ የባሕርይ [nature] ?

መጽሐፍ ቅዱስ አብ ለወልድ እንደሚናገር፣ ወልድም ለአብ እንደሚናገር ይገልጻል (ዮሐ 11÷41-42፤ 12÷28፤ 17÷1-26):: ቃለ እግዚአብሔር አብ ለወልድ እንደተናገረ ወልድም ለአብ እንደተናገረ፣

ሰዎችም እንደሰሙአቸው [ዮሐ 12÷28] እየገለጸ፣ የለም አንድ አካል ናቸው ማለት አግባብ አይደለም::

መጽሐፍ ቅዱስ አብ ወልድን እንደሚያውቀው፣ ወልድም አብን እንደሚያውቀው ይገልጻል (ማቴ 11÷27፤ ሉቃ 10÷22፤ ዮሐ 7÷29፤ 8÷55፤ 10÷15):: ወልድን፣ ወልድም አብን እንደሚያውቀው በግልጽ ተቀምጦ ሳለ የለም የሁለቱም አካል አንድ ነው ማለት እንዴት ይቻላል?::

ኢየሱስ በድኅረ ሥጋዌ ሕይወቱ

በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ወደዚች ምድር ከመምጣቱ በፊት እንደ ነበር ይገልጻሉ:: ዓለማትን የፈጠረ ኢየሱስ (ቃል) ነው (ዮሐ 1÷3፤ ቆላ 1÷16-17፤ ዕብ 1÷2፤ ራእ 3÷14):: ዕብ 1÷2 ላይ እግዚአብሔር ዓለማትን የፈጠረው «በልጁ» ነው ይላል::

ኢየሱስ ሰው ሆኖ ወደዚች ምድር ከመምጣቱ በፊት በእግዚአብሔር «ዘንድ» ነበር (ዮሐ 1-1፤ 17÷5፤ 1ዮሐ 2÷1):: ግሪኩ «ፕሮስ» ወይም «ፓራ» የሚለውን ቃል፣ አማርኛው «ዘንድ» (የ1954 ዓ.ም ትርጉም) ብሎ ተርጉሞታል:: በግሪኩ ሰዋስው «ፕሮስ» ወይም «ፓራ» የሚለውን ቃል ተሳቢ ሙያ (Objective case) ከቀደመው፣ የሚያመለክተው ግንኙነትን ነው::

ኢየሱስ ከመጥምቁ ዮሐንስ በፊት ነበር [ዮሐንስ ከኢየሱስ በፊት ቢወለድም እንኳ] (ዮሐ 1÷15፤ 1÷14-18፤ 29-34) ::

ኢየሱስ ከሰማይ የመጣ፣ ከአብ «ዘንድ» የተላከ፣ ወደ ሰማይ የወጣ፣ በክብር ወደ አባቱ የተመለሰ ነው (ዮሐ 3÷13:31፤ 6÷33:38:41:46:51:56-58:62፤ 8÷23:42፤ 13÷3፤ 16÷27-28፤ ዮሐ 1÷10-11)::

ኢየሱስ ከአብርሃም በፊት ነበር (ዮሐ 8÷58):: ኢየሱስ ፍጥረታት ሁሉ ከመፈጠራቸው በፊት ነበር (ቆላ 1÷17፤ 1÷12-20):: ይህም ወልድ በብሉይ ኪዳን ዘመን ከአብ ጋር እንደ ነበር በግልጽ የሚያሳይ ነው::

አብና መንፈስ ቅዱስ

እግዚብሔር አብና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የተለያዩ አካላት ናቸው:: እግዚአብሔር አብ መንፈስ ቅዱስን ልኮታል (ዮሐ 14÷15፤ 15÷26):: ታዲያ ላኪና ተላኪ አንድ አካል ናቸው ማለት እንዴት ይቻላል?

መንፈስ ቅዱስ ስለ ምዕመናን ወደ አብ ይጸልያል (ሮሜ 8÷26-27) ስለዚህ አብ ጸሎት ሰሚ፣ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ጸሎት አድራሽ ነው::

አብ የተለየ አካል፣ መንፈስ ቅዱስም እንደዚሁ የተለየ አካል እንዳላቸው በማቴ 28÷19 ሰዋስዋዊ አወቃወር ቃኝተናል::

ተቃውሞዎች

የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን መምህራን የሥላሴን አስተምህሮ ላለመቀበል የሚያቀርቡአቸው «ማስረጃዎች» ከቃለ እግዚአብሔር የሚጠቀሱ ብቻ አይደሉም:: ከአመክኒዮና [Logic] ከታሪክ የሚጠቅሱአቸውም «ማስረጃዎች» አሉአቸው:: ከድርጅቱ

አባላት ተዘውትሮ የሚደመጠው አነጋገር ሥላሴ የሚለው ቃል መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አይገኝም የሚለው ዋነኛው አመክንዮአዊ «ማስረጃቸው» ነው:: ሥላሴ የሚለው ጥሬ ቃል መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አለመገኘቱ እሙን ነው:: ነገር ግን ሥላሴ የሚለው ቃል የወከለው ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው:: የቤተ ክርስቲያን አበው ነገረ መለኮትን ሲያጠኑ፣ ለትምህርቶቹ ይስማማሉ የሚሉአቸውን ርእሶች ሰጥተዋል:: ለምሳሌ ቀኖና (Canon)፣ የእግዚአብሔር ቃል ሕጸጽ አልባ ስለመሆኑ [Inerrant]፣ ነገረ ክርስቶስ [Christology] ወዘተ. . . እነዚህ ጥሬ ንባቦች ቃላት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አይኑሩ እንጂ፣ በእነዚህ ነገሮች ቃለ እግዚአብሔር ሰፊ ትምህርት አለው:: ቃሎቹም እነዚህን አስተምህሮዎች ይወክላሉ:: «የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን» ደቀ መዛሙርት ችግራቸው ሥላሴ የሚለው ቃል ከሆነ፣ ቃሉን አለመቀበል ይችላሉ፤ ነገር ግን ቃሉ የሚወክለውን ተአማኒ ትምህርት ክዶ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ ማሰብ በፍጹም አይቻልም:: እንዲያው ለነገሩ «ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን» የሚለው ቃል መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገኛል?

የሥላሴን አስተምህሮ ላለመቀበል ከታሪክ የሚጠቅሱት፣ «የሥላሴ ትምህርት ከአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፊት አልነበረም» የሚል ነው:: ትምህርቱን ያስፋፋችው የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ነች ባዮችም ናቸው:: እንደ ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ትምህርት፣ የሥላሴ አስተምህሮ የተዋቀረው በ325 ዓ.ም በተጠራው በጉባኤ ኒቂያ ላይ ነው::

ይህ ዐዋጅ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን መምህራን ለትምህርተ መለኮትና ለአመክኒዮ ብቻ ሳይሆን፣ ለታሪክም ባዕዳን መሆናቸውን ያሳያል:: በዚያን ወቅት አሁን ያለው ዐይነት መዋቅር ያላት የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያናት አልነበረችም:: በወቅቱ የሮማ ፓፓ የበላይ ሆኖ የሚያስተዳድራቸው ቤተ ክርስቲያናት ብቅ ያሉት፣ በስድስተኛው

መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ ነው:: እንዲያውም የሮማ ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳት በኒቂያ ጉባኤ አልተሳተፉም:: የኒቂያው ጉባኤ የተጠራው በምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ነበርና::

ሥላሴ የሚለውም ቃል ሆነ፣ ከሥላሴ አስተምህሮ ጋር አብረው የሚጠቀሱት ቃላት [ለምሳሌ :- አካላት (Persons)፣ እንደ ባሕርይ (Substance)] ይሠራባቸው የነበሩት ከጉባኤ ኒቂያ በፊት ነው:: ቃላቱንም በስፋት ሲጠቀምባቸው የነበረው ጠርጡሊያኖስ የኖረው ከኒቂያ ጉባኤ በፊት ነበር::

እንዲያውም ከታሪክ የምንማረው ነገር፣ በመጀመሪያ ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ የአትናቴዎስ ደጋፊ ቢሆንም፣ ከ332 ዓ.ም በኋላ ባሉት 50 ተከታታይ ዓመታት የደገፈው፣ ኢየሱስ አምላክ አይደለም የሚለውን የአርዮስን ኑፋቄ ነው::

የሥላሴ አስተምህሮ ቀዳማይ አመንጪው መጽሐፍ ቅዱስ ቢሆንም፣ ፈርጅ ባለው መልኩ የቀረበው፣ እንደ ሌሎቹ ክርስቲያናዊ አስተምህሮዎች ሁሉ ቤተ ክርስቲያን በየዘመናቱ የሚነሣባትን መናፍቃዊ ትምህርት በቃለ እግዚአብሔር ለመግታት ትችል ዘንድ፣ በምትጠራቸው ጉባኤዎች ነበር:: ለዚህም ነው፣ «የነገረ መለኮት ታሪክ፣ የመናፍቃን ታሪክ ነው» የሚባለው:: ነገረ መለኮት አሁን ባለው መልኩ አምሮና ደምቆ የቀረበው፣ መናፍቃን ለሚያነሡአቸው ጥያቄዎች ቤተ ክርስቲያን መልስ ለመስጠት ባደረገችው ዝግጅት ነው:: የትኞቹ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ቀኖናዊ ናቸው፣ የትኞቹስ አይደሉም የሚለው ነገር የተወሰነው፣ መናፍቃን በቃለ እግዚአብሔር ላይ ሐሳባቸውን የሚደግፉ ሌሎች የድርሳነ ፈጠራ መጻሕፍት ለመጨመርና ካሉትም ላይ ለመቀነስ ያደርጉ የነበረውን ሙከራ መና ለማስቀረት ነበር:: መጽሐፍት ለመጨመርና ካሉትም ላይ ለመቀነስ ያደርጉ የነበረውን ሙከራ መና ለማስቀረት ነበር:: ይህም የሆነው በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ ነው::

የሥላሴ አስተምህሮ አሁን ባለው መልኩ ተቀናጅቶ የቀረበው፣ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ተነሥተውባት ለነበሩት የሰብአልዮስና የአርዮስ ደቀ መዛሙርት መልስ ለመስጠት በተነሣችበት ጊዜ ነው:: ቃለ እግዚአብሔር አብን፣ ወልድንና መንፈስ ቅዱስን አስመልክቶ ላለው ትምህርት፣ ሥላሴ የሚለው ስም ተገቢ ቃል ነው፤ የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት ለመግለጽ ከዚህ ቃል የተሻለ የለምና::

የዛሬዎቹ ሰብአልዮሳውያንም ሆኑ አርዮሳውያን፣ ከታሪክም ሆነ ከቃለ እግዚአብሔር የሚግሩ አይደሉም::

ማጠቃለያ

የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ሰዎች በአስተምህሮተ እግዚአብሔር ላይ ያላቸው ትምህርት፣ ቃለ እግዚአብሔር ስለ አብ፣ ስለወልድና ስለ መንፈስ ቅዱስ ከሚያስተምረው ትምህርት እጅግ የራቀ ነው:: ስለዚህም ድርጅቱ፣ አምላካዊው መገለጥ ፍንትው አድርጎ የሚያስተምረውን የሥላሴን አስተምህሮ ያለመቀበሉ ፍጹም ስሕተት ነው::

ዐበይት የሆኑትን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች መካድ ንዑስ የሆኑትን ትምህርቶች ከመካድ የበለጠ ጥፋት ያስከትላል:: አብያተ ክርስቲያናት ክርስቲያናዊ ትምህርቶችን ርቱዕና መናፍቅ ብለው እንዲፈርጁአቸው ከሚያደርጉት መሠረታዊ አስተምህሮዎች መኻል፣ የኢየሱስ ክርስቶስን ፍጽም ሰብአዊነትና ፍጽም አምላካዊነት መቀበል ወይም መካድ ዋነኛው ነጥብ ነው:: በርካታ መናፍቃን የኢየሱስ ክርስቶስን ፍጽም ሰብአዊነትና አምላካዊነት ይክዳሉ::

ለሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ኢየሱስ ፍጹም አምላክ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር አብ የለበሰው /የተገለጠበት/ ሥጋ ነው:: የድርጅቱ ተከታዮች ኢየሱስ እግዚአብሔር ነው ሲሉ፣ ኢየሱስ እግዚአብሔር አብ ነው ማለታቸው ነው፤ ነገር ግን ቃለ እግዚአብሔር እንደዚያ አያስተምረንም:: መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ እግዚአብሔር ነው ሲል፣ ከዘላለም ዓለም ጀምሮ መቅደም መቀዳደም፣ በብለጥ መበላለጥ

ሳይኖር፣ ከእግዚአብሔር አብ ጋር እኩል የሆነ አምላክ ነው ማለቱ ነው:: ቤተ ክርስቲያን አዘወትራ በምትጠቀምበት አጭር አገላለጽ፣ እግዚአብሔር ወልድ /በግጻዌ መለኮት ውስጥ/ ሁለተኛው አካል ነው::

ሐዋርያው ዮሐንስ፣ «ወልድን የሚክድ ሁሉ አብ እንኳ የለውም፤ በወልድ የሚታመን አብ ደግሞ አለው» /1ዮሐ 2÷23/ ይላል:: የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ሰዎች፣ ኢየሱስን ክደናል የሚል እምነት የላቸውም:: በመሠረቱ በሐዋርያው ዮሐንስ ዘመን የነበሩትም መናፍቃን ኢየሱስን እንደካዱ አያስቡም:: ሁሉም መናፍቃን «ወልድ» ለሚለው የተለየ ትርጒሜ ይሰጣሉ:: የይሖዋ ምስክሮች፣ «ኢየሱስ» በእግዚአብሔር አብ የተፈጠረ የመጀመሪያ ፍጥረት ነው ሲሉ፣ ሞርሞኖች ደግሞ፣ «ወልድ» በእግዚአብሔር አብና በማርያም መካከል በተካሄደ የግብረ ሥጋ ግንኙነት የተወለደ ሰው ነው ይላሉ:: የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አማኞች ደግሞ «ወልድ» የእግዚአብሔር አብ ሰብአዊ ተፈጥሮ (/አብ የለበሰው ሰብአዊ / አካል) ነው ባዮች ናቸው:: ይህ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ዐዋጅ የሞርሞኖችን ያህል አስደንጋጭ እንዲሁም የይሖዋ ምስክሮችን ያህል ያፈጠጠ ባይሆንም፣ ከቃለ እግዚአብሔር ትምህርት ጋር በቀጥታ የሚቃረን ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ አብ ራሱን የቻለ ህላዌ /personality/ ያለውና ከአብ ጋር ትክንል ዕሪና ያለው [በሁሉ እኩል የሆነ] ፍጹም አምላክ መሆኑን መካድ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ፣ «ወልድ» የሚያስተምረውን ትምህርት መካድ ነው:: ስለዚህ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ተከታዮች የሚሰብኩት፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት ያልሰበኩትን «ሌላ ኢየሱስ»፣ «ልዩ ወንጌልና» «ልዩ መንፈስ» ነው /2ቆሮ 11÷4/::

የቃለ እግዚአብሔርን እውነት መሠረት ያደረገችው የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን፣ የጥንት ሰብአልዩሳውያንንም ሆነ የዛሬዎቹን «የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን» ሰዎች፣ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊው እውነት የራቁ መናፍቃን ናቸው የሚል ጠንካራ እምነት አላት:: ክርስቲያኖች የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አባላትን በታላቅ ፍቅርና ትሕትና የሥላሴን ትምህርት በማስረዳት፣ ወደ ደኅንነት ሊያመጡአቸው ይገባል::

ክፍል ዐሥራ ሁለት
የክርስቲና እምነት ከባሃኢ ሃይማኖት ጋር ማበር ይችላልን?

ሀ. የባሃኢ እምነት ታሪካዊ ዳራ

የባሃኢ እምነት ወደ ኢትዮጵያም ሆነ ወደ ሌሎች የዓለማችን አገሮች የተሠራጨው ከፋርስ (ከኢራን) ተነሥቶ ነው:: የባሃኢን እምነት የመሠረተው ሚርዛ ሁሴን ዓሊ በቅጽል ስሙ ባሃኡላ (በፋርስ ቋንቋ፣ «የእግዚአብሔር ክብር» ማለት ነው) የተባለው የፋርስ ተወላጅ ነው»:: የሰውን ልጆችን አንድ ለማድረግና የሰላምን ዘመን የሰበከውን» የዚህን ነቢይ ነኝ ባይ ምጽአት በ1844 ዓ.ም ያወጀው የእርሱ አገልጋይ የነበረው ዓሊ ሙሐመድ፣ በቅጽል ስሙ ባብ (በፋርስ ቋንቋ፣ «መግቢያ» ማለት ነው) የተባለው ወጣት ነው[23]::

በእምነቱ መስፋፋት የተቈጡት ሙስሊሞችና የአገሪቱ መንግሥት፣ አዲሱን እንቅስቃሴ ለመግታት ዕቅድ አወጡ:: በ1850ዓ.ም ባብ ታስሮ በእሳት ተቃጠለ:: ከእርሱ ሞት በኋላ የእርሱ ተከታዮች ተሰደዱ:: ከ20ሺህ የሚበልጡ ተገደሉ፤ የተቀሩትም ወደ ወህኒ ተወረወሩ::

በ1863ዓ.ም ሚርዛ ሁሴን ዓሊ ባግዳድ ውስጥ ተያዘ:: በሃኢ የሚለው ስም የመጣው ባሃኡላ ከሚለው ከዚህ ሰው የቅጽል ስም ነው:: ባሃኡላ ከ1892ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሞተበት ጊዜ ድረስ የኖረው በእስር ቤት ነው:: የእርሱ ታላቅ ወንድም የነበረው አጳስ አፈንዲን በእርሱ እግር የተተካ ሰው መሆኑን በማወጅ ራሱን አብዱል ባሃ (በፋርስ ቋንቋ፣ «የባሃ አገልጋይ» ማለት ነው) ብሎ ሰየመ:: አብዱል ባሃ በ1908ዓ.ም ከእስር ከተፈታ በኋላ፣ በርካታ ሚስዮናዊ ጕዞዎችን

[23] The Bahai Faith in Ethiopia (ያልታተመ) ገጽ 1::

አድርጎአል:: በ1912ዓ.ም ወደ አሜሪካን አገር በመሄድ ለስምንት ወር በዚያ ተቀመጠ:: በዚህን ጊዜ ነው በዊልሚት ኢሊኖይ የሚገኘውን ቤተ መቅደስ ለማነጽ የመሠረት ድንጋይ የተቀመጠው::

አብዱል ባሃ በ1921ዓ.ም ሲሞት የልጅ ልጁ ሾጊ አፈንዲ በቦታው ተተካ:: ሾጊ አፈንዲም በ1957ዓ.ም የሞተው በቦታው ሰው ሳይተካ ነው:: አሁን ድርጅቱ የሚመራው ዘጠኝ በሚሆኑ የአመራር አካላት ሲሆን፣ ዋና መሥሪያ ቤቱም የሚገኘው በእስራኤል አገር አይፋ በተባለው ስፍራ ነው[24]::

በ1982ዓ.ም በወጣው ስታቲስቲክ መሠረት በኢራን 300,000 የእምነቱ ተከታዮች የሚገኙ ሲሆን፣ በኢራን ውስጥ እምነቱ ከእስልምና እንዳፈነገጠ ሃይማኖት ይቈጠራል::

ለ. የባሃኢ እምነት በኢትዮጵያ

ዓሊ ሙሐመድ (ባብ)፣ ሙባራክ የተባለ ኢትዮጵያዊ አገልጋይ ነበረው:: የባብን ዐዋጅ የተቀበለ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊም ሙባረክ መሆኑ ተዘግቦአል[25]::

እምነቱን የተቀበለች የመጀመሪያዋ አፍሪካዊት አገር ግብፅ ናት:: ይህም በባሃሁላ የአገልግሎት ዘመን ነው:: እምነቱ ከግብፅ ወደ ሌሎች የአፍሪካ አገሮች መስፋፋት የጀመረው በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አካባቢ ነው:: እምነቱ ወደ ኢትዮጵያ የገባውም በዚሁ ወቅት ነው:: እምነቱ በከፍተኛ ፍጥነት እየተስፋፋባቸው ካሉ የዓለማችን አገሮች ውስጥ፣ የአፍሪካ አገሮች ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛሉ::

24 Edmond C.Gruss. Cults and the Occult ገጽ 146-147::
25 The Bahai Faith in Ethiopia (ያልታተመ) ገጽ 1::

እምነቱን ከግብፅ ወደ ኢትዮጵያ ያመጣው የመጀመሪያው ሚስዮናዊ ሳብሪ ኤልያስ የሚባለው የ27ዓመት ወጣት ነው:: ከአንድ ዓመት «ጠንካራ» ሚስዮናዊ ሥራ በኋላ፣ በአዲስ አበባ የመጀመሪያው፣ «አጥቢያ መንፈሳዊ ጉባኤ» በወርኀ ኀዳር 1933ዓ.ም ተመሠረተ:: ይህን ድል አስመልክቶ በየአገሮቹ ለሚገኙ የባሃኢ ማኅበረ ሰብ አባሎች የተላከው ደብዳቤ የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች አካቶ ነበር:- «የባሃሁላ እምነት በኢትዮጵያ- የአፍሪካ ብቸኛዋ ነጻ አገር...ያለውን ዕድገት አስመልክቶ በዓለም ዙሪያ ለሚገኙ ወንድሞቻችን ይህንን መልእክት ስናስተላልፍ ደስታ ይሰማናል...የባሃኢ እምነት በዚህ ታሪካዊ ምድር ላይ እየተስፋፋ ነው[26]»::

እምነቱን በመጀመሪያው የተቀበሉት ኢትዮጵያዊ (ከሙባራክ ቀጥሎ ማለት ነው) አዝማች ስዩም ገብርኤል ይባላሉ:: በኋላ እኚህ ሰው ኑሮአቸውን ወደ አሥመራ በማድረግ በ1955ዓ.ም ላይ የተቈረቈረው፣ «አጥቢያ መንፈሳዊ ጉባኤ» አባል ሆኑ:: በአሥመራ እምነቱን በመጀመሪያ የተቀበለው ሰው የአዝማች ስዩም ልጅ፣ ታምራት ስዩም ነው::

ሳብሪ ኤልያስ ካከናወናቸው ሥራዎች መኻል የባሃይን መሠረተ እምነት የሚገልጸው፣ «ባሃሁላና አዲሱ ዘመን» [«Baha'u'llah and the New Era »] የተባለውን መጽሐፍ በ1934ዓ.ም ወደ አማርኛ መተርጐሙ ነው:: ሳብሪ ኤልያስ የአማርኛ ቋንቋ ስለማያውቅ የትርጐሙን ሥራ ያከናወኑት ሁለት ኢትዮጵያውያን ናቸው[27]:: የመጽሐፉ ቅጅ በዓለም ዙሪያ ለሚገኙት የእምነቱ አባላት ብቻ ሳይሆን፣ ለቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴም በ1936ዓ.ም ተበርክቶላቸው ነበር[28]::

26 ዝኒ ከማሁ::
27 ዝኒ ከማሁ::
28 ዝኒ ከማሁ::

በጣሊያን ወረራ ምክንያት በ1935ዓ.ም ሳብሪ ኤልያስ ወደ አገሩ ወደ ግብፅ ተመለሰ:: ጦርነቱ እንዳበቃም ሳብሪ ኤልያስ በወርኀ የካቲት 1944ዓ.ም ከሦስት ዓመት በፊት ካገባት ሚስቱ ፋይማ ካኩት እንዲሁም ሁሴንና ሳፋ ከሚባሉት ልጆቹ ጋር ወደ ኢትዮጵያ ተመለሰ[29]::

በጦርነቱ ወቅት ብዙ የእምነቱ ተከታዮች እምነቱን ትተው ስለ ነበር፣ ሳብሪ ኤልያስ ያገኛቸው ባሃኢዎች ከየመን የመጣው ሰይድ መንሱርና አርአያ የሚባሉት ግለሰቦች ብቻ ነበሩ:: ሰይድ መንሱር እምነቱን ወዲያው ተወ፤ አቶ አርአያም ሞቱ:: በዚህን ወቅት ነው ቀኛዝማች ጊላ ሚካኤል ባሕታ ይህን እምነት የተቀበሉት:: እኚህ ሰው የሕግ አማካሪ የነበሩ ሲሆን፣ ለእምነቱም መስፋፋት ታላቅ ድርሻ ነበራቸው:: የባሃዮችም ቁጥር የጨመረው በዚህ ጊዜ ነው[30]::

ከ1953-63 ዓ.ም ባሉት ጊዜያት ውስጥ ድርጅቱ ትልቅ የመስፋፋት ፓሊሲ ስለነደፈ፣ በርካታ የኢራንና ጥቂት የአሜሪካን ሚስዮናውያን ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል:: ለሚስዮናዊ ሥራቸውም ማእከል ያደረጉት አዲስ አበባን፣ አሥመራን፣ ዐድዋን፣ ጐንደርን የመሳሰሉ ቦታዎችን ነው[31]::

በ1963ዓ.ም 25 የሚሆኑ የአውሮፕላን በረራ ተማሪዎች የባሃኢን እምነት ተቀበሉ:: እምነቱ በዮኒቨርስቲ ተማሪዎችም መካከል ተሰበከ:: የመጀመሪያው ብሔራዊ የባሃኢ ማእከል የተመሠረተው 1972ዓ.ም ነው:: የባሃኢ እምነት በ1960ዓ.ም በግብፅ ውስጥ እንዳይንቀሳቀስ ሲታገድ፣ «ብሔራዊ መንፈሳዊ ጉባኤው መቀመጫውን በኢትዮጵያ አደረገ:: ሰኔ 10ቀን 1961ዓ.ም ኢትዮጵያ፣ «የብሔራዊ መንፈሳዊ ጉባኤ ሰሜን ምሥራቅ አፍሪካ» ዋና መቀመጫ ሆነች[32]::

[29] ዝኒ ከማሁ::
[30] ዝኒ ከማሁ::
[31] ዝኒ ከማሁ::
[32] ዝኒ ከማሁ::

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ባሃኢ ብሔራዊ መንፈሳዊ ጉባኤ ሥር 51 «አጥቢያ መንፈሳዊ ጉባኤዎች» ይገኛሉ[33]::

ሐ. የባሃኢ እምነት አስተምህሮ

የባሃኢ እምነት በሦስት መሠረታዊ ነጥቦች ላይ መሠረት ያደረገ ነው:: ይኸውም:- የእግዚአብሔር አንድነት፣ የሃይማኖት አንድነትና የሰዎች አንድነት ናቸው:: እግዚአብሔር በባሕርይው ሊታወቅ የማይቻል ነው:: የእግዚአብሔር ቃል ሊታወቅ የሚችለው እርሱ በመረጣቸው መልእክተኞች አማካይነት ብቻ ነው:: የበሃሁላን አስተምህሮ በሚከተለው መልክ አሳጥሮ ማቅረብ ይቻላል[34]:-

- የሃይማኖቶች ሁሉ መሠረታዊ አንድነት::
- የሃይማኖት፣ የጐሣና የቀለም ልዩነቶችን ማስወገድ::
- በሳይንስና በሃይማኖት መካከል ኅብረት መፍጠር::
- የወንድና የሴት እኩልነት::
- ሰዎች ሁሉ የሚግባቡት አንድ ዓለም ዐቀፋዊ ቋንቋ::
- ሥር የሰደደ ድኽነትንና ቅጥ ያጣ ብልጽግናን ማስወገድ::
- በሕዝቦች መካከል ያለውን አለመግባባት ሁሉ ማስወገድ::
- ሥራን እንደ አምልኮ በማየት ለሥራ ትልቅ ትኩረት መስጠት::
- የሰው ልጆች ሁሉ ዋነኛ ግብ የሆነውን ቋሚና ዓለም ዐቀፋዊ ሰላም መመሥረት::

የባሃኢ እምነት ማእከል ያደረገው «አንድነት» እና «ኅብረት»ን ነው:: ይኸውም «አንድነትና» «ኅብረት» በሃይማኖት፣ በማኅበራዊ ኑሮ

[33] ዝኒ ከማሁ::
[34] One God, One Religion One Mankind

እንዲሁም በፓለቲካ ላይ ነው:: የባሃኢ እምነት ያለው ቀዳማይ ዐላማ የማኅበረ ሰብ ጥናት፣ የፓለቲካ ወዘተ ምሁራን ካላቸው ዐላማ ጋር አንድ ዐይነት ነው::

የባሃኢ እምነት ኢየሱስንም ሆነ መሐመድን ነቢይ ናቸው፣ ነገር ግን ከእነርሱ በኋላ የመጣው ባሃሁላ ከእነርሱ ይበልጣል የሚል ሃይማኖት ነው::

መ. የባሃኢ ሃይማኖትና ክርስትና

የባሃኢ እምነት መሠረታዊ ከሆኑት የክርስትና አስተምህሮዎች ጋር በቀጥታ ስለሚጋጭ፣ የባሃኢ እምነት ከክርስትና ጋር ፈጽሞ ሊስማማ አይችልም:: ታላቁ ዐቃቤ ክርስትና ዋልተር ማርቲን፣ «የባሃኢ ሃይማኖት መምህራን የክርስትና አስተምሮ ከበሃኢ መሠረታዊ ትምህርት ጋር የመቃረኑን እውነት ችላ ይሉታል፤ እንዲያውም ቅራኔዎቹን ለማስታረቅ ይሞክራሉ:: ነገር ግን ከእነርሱ ጋር የተካሄደው ቃለ መጠይቅ የባሃኢ እምነት መሠረታዊ ናቸው ከሚባሉት ታሪካዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ከሆኑት የክርስትና ትምህርቶች ጋር ይቃረናል[35]::

ጆርጅ ታዎንሸንድ የተባለው የባሃኢ ጸሐፊ ክርስቲያኖችን፣ «ሐሰተኞች ነቢያት» ብሎ ይጠራቸዋል:: ይህንን ያለበትም ምክንያት ክርስቲያኖች «ክርስቶስ ያስተማረውን የወንጌል ትምህርት ስለለወጡ» ነው[36] የሚል እምነት አለው:: እነዚህን ክርስቲያኖች «ሐሰተኞች ነቢያት» ያሰኘው ትምህርቶች የትኞቹ እንደሆኑ ሲገልጽ:- እነዚህ

[35] Walter R. Martin, The Kingdom of the Cults,rev. ed.(Minneapolis: Bethany, 1985) ገጽ 278 ማርቲን ከባሃኢ መምህራን ጋር ያደረገውን ቃለ መጠይቅ በራሱ መጽሐፍ በገጽ 273-276 ላይ ይመለከቷል::

[36] Edmond C. Gruss. 153 George Townshend,Christ and Baha'U'llah, rev.ed. (Oxford: George Ronald,1966) ገጽ 25 ጠቅሶ እንደ ጻፈው::

ነቢያት «ኢየሱስ ክርስቶስ ልዩ የሆነና ሰው የሆነ አምላክ ነው፤ በሃይማኖት ታሪክ ውስጥ ፍጹም ያልታየ፣ ወደፊትም የማይታይ ነው ይላሉ»[1]:: ከዚህም የተነሣ «የክርስቶስ ትምህርት ፍጹምና የመጨረሻ ነው ይላሉ»[2]:: ኢሳ 9÷6-7 መሠረት በማድረግ፣ «ክርስቶስ የብሉይ ኪዳኑ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው ይላሉ»[3]:: «የክርስቶስ ወንጌል» ነው ብለው የሚያስተምሩት ትምህርት፣ «መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው ክርስቶስ በገሊላ ካስተማረው ትምህርት፣ ፍጹም የተለየ ነው»[4]:: «ቤተ ክርስቲያን የእርሱን [የክርስቶስን] መገለጥ [ትምህርት] የመጨረሻና የእውነተኛ እምነት ብቸኛ መሠረት ነው ይላሉ»[5]:: «የክርስቶስ መንፈሳዊ አገልግሎት...እንደ ተኣምራት...ቁሳዊ ነው ይላሉ:: ዐላማውን ሙሉ በሙሉ በመሳት ትንሣኤውን እንኳ ቁሳዊ ነው ይላሉ»[6]::

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስን የሚያምኑ ክርስቲያኖች ታዎንሸንድ፣ «ሐሰተኛ ነቢያት» ናችሁ የሚለውን ክስ እንዲሁም በሃኢዮች የሚያቀርቡላቸውን አብሮ የመሆን ግብዣ አይቀበሉም:: ክርስቲያኖች፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በባሃሁላ የሚተካ ነቢይ ነው የሚል እምነት የላቸውም:: ቃለ እግዚአብሔር እንደሚያስተምረን ኢየሱስ ክርስቶስ እጅግ ልዩና ከማንም ጋር የማይተካከል ፍጹም ሰውና ፍጹም አምላክ፣ የእግዚአብሔር አብ ብቸኛ እንደራሴ፣ ለማንኛውም ሰው፣ በየትኛውም ጊዜና ሁኔታ የኀጢአት ብቸኛ መድኀኒት ነው:: እንደ ባሃሁላ ትምህርት፣ መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስን በተመለከተ የሚያስተምረው ትምህርት በአሁኑ ዘመን እውነተኛ አይደለም:: ትክክል አይደሉም ከሚባሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው:-

[1] ዝኒ ከማሁ::

[2] ዝኒ ከማሁ ከገጽ 26 ጠቅሶ እንደ ጻፈው::

[3] ዝኒ ከማሁ ከገጽ 27 ጠቅሶ እንደ ጻፈው::

[4] ዝኒ ከማሁ ከገጽ 28 ጠቅሶ እንደ ጻፈው::

[5] ዝኒ ከማሁ በቅንፍ ያለውን አይጨምርም::

[6] ዝኒ ከማሁ ከገጽ 29 ጠቅሶ እንደ ጻፈው::

«ኢየሱስም:- እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም» (ዮሐ 14÷6)

«መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና» (ሐሥ 4÷12)

«ከተመሠረተው በቀረ ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልምና፤ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው» (1 ቆሮ 3÷11)

«አንድ እግዚአብሔር አለና፤ በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፤ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ ራሱንም ለሁሉ ቤዛ ሰጠ» (1ጢሞ 2÷5-6)

«ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ፣ እስከ ለዘላለምም ያው ነው»:: (ዕብ 13÷8)

ባሃኢዎች፣ «የተባረከ ተስፋችን» የሚለውን ክርስቲያናዊ ቃል በመውሰድ:- «ክርስቲያን ከሆንህ...በእግዚአብሔር ክብር የሚመጣው የክርስቶስ ትንቢት ተፈጽሞአል:: በዚህ ጊዜም የእርሱ [የክርስቶስ] አዲስ ስም ባሃኡላ ነው:: ይህም ማለት፣ «የእግዚአብሔር ክብር ማለት ነው»[7]:: ይህ «የትንቢት ፍጻሜ» ቃለ እግዚአብሔር ከሚያስተምረን የትንቢት ፍጻሜ ጋር የሚስማማ አይደለም:: መጽሐፍ ቅዱስ:-«...የተባረ ከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኅኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን...»

[7] ዝኒ ከማሁ ገጽ 154 "The Bahai Faith Unites All Races, All Religions" Los Angeles Times, ጥቅምት 22 ቀን 1971ዓ.ም ጠቅሶ እንደ ጻፈው:: በቅንፋ ያለውን አይጨምርም::

እየጠበቅን...» (ቲቶ 2÷12-13) ይለናል:: እንዲሁም የኢየሱስ ክርስቶስን ዕርገት ቆመው በመመልከት ላይ ለነበሩ ሐዋርያት፣ መላእክት:- «ደግሞም የገሊላ ሰዎች ሆይ፤ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለምን ቆማችኋል? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት፣ እንዲሁ ይመጣል አሉአቸው» (ሐሥ 1÷11)::

የባሃኢ ሃይማኖት፣ «የሃይማኖት አንድነት» የሚለው ትምህርቱ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ አይደለም:: አብዛኞቹ ሃይማኖቶች ተመሳሳይ የሆኑ ባሕርያት ቢኖሩአቸውም እንኳ፣ ክርስትና ከሌሎች የሚለየውን መሠረታዊ አስተምህሮ በመተው፣ ከሂንዱይዝም፣ ከቡዲሂዝም፣ ከእስልምና ወይም ከሌሎች ሃይማኖቶች ጋር አያብርም:: የባሃኢን እምነት ጨምሮ የትኛውም የሃይማኖት ክፍል ስለ ሰዎች ኀጢአተኛነትና በክርስቶስ ስለሚገኘው ደኅንነት (ሮሜ 3÷23፤ ኢሳ 64÷6፤ ዮሐ1÷29፤ 3÷14-17) ምንም ዐይነት ትምህርት የለውም::

ማጠቃለያ

የባሃኢ እምነት እንዴት ኀጢአት ይቅር ሊባል እንደሚችልና ስለ እግዚአብሔር ፍርድ የሚያስተምረው ትምህርት የለውም:: እንዲያውም በባሃኢ እምነት ስለ ኀጢአት ዋጋና ስለ ደኅንነት መንገድ ማውራት ጸያፍ ነው:: ነገር ግን ቃለ እግዚአብሔር ከዚህ የተለየ አቋም አለው፣«እግዚአብሔርም የዘላለምን ሕይወት እንደ ሰጠን ይህም ሕይወት በልጁ እንዳለ ምስክሩ ይህ ነው:: ልጁ ያለው ሕይወት አለው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም:: የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ»:: (1ዮሐ 5÷11-13)

ክፍል ዐሥራ ሦስት

የሞርሞን ሃይማኖት ክርስትና ነውን?

ሀ. የሞርሞን እምነት ታሪካዊ ዳራ

«ሞርሞን» ወይም «የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የመጨረሻው ዘመን ቅዱሳን»፣ የተባለውን ሃይማኖታዊ ድርጅት የመሠረተው ጆሴፍ ስሚዝ ጁ. አር ይባላል። ጆሴፍ ስሚዝ ታኅሣሥ 23 ቀን 1805 ዓ.ም በአሜሪካን አገር ቫረን ቬርሞት በተባለው ስፍራ ተወለደ። ጆሴፍና ሉሲ ማክ የተባሉት ወላጆቹ ዐሥር ልጆች የነበሩአቸው ሲሆን፣ ጆሴፍ ስሚዝ አራተኛው ልጅ ነው።

አብዛኞቹ የስሚዝ ቤተ ሰብ አባላት የፕሪስባቴሪያን ቤተ ክርስቲያን አባል ሲሆኑ፣ ወጣቱ ጆሴፍ ግን የቤተ ክርስቲያኒቱ አባል ሳይሆን ቆየ። ስሚዝ የቤተ ክርስቲያኒቱ አባል እንዳልሆን ምክንያት የሆነኝ፣ በአብያተ ክርስቲያናት መካከል ያለው ልዩነት ነው[44] ይላል።

በ1820ዓ.ም ጆሴፍ ስሚዝ ለሞርሞን ቤተ ክርስቲያን መሠረት የሆነውን ራእይ አየሁ አለ። በራእይ አየሁት ያለው በብርሃን የተሞላ ሰው፣ ከየትኛውም የሃይማኖት ድርጅት ጋር እንዳይቀላቀል እንዳስጠ ነቀቀው እንዲያውም የእነዚህ ሃይማኖት ሊቃውንት የተበላሹ፣

---

[44] Josh MC Dowell . A Ready Defense (Nashville, Tennessee: Thomas Nelson 1993) ገጽ 341

የሃይማኖት መግለጫቸውም ጻያፍና የሃይማኖት መልክ ቢኖራቸውም ኀይሉን ግን እንደካዱ ገለጸልኝ ይላል[45]::

ጆሴፍ ስሚዝ በመስከረም 21ቀን 1823ዓ.ም ሁለተኛውን ራእይ እንዳየ ገለጸ:: ጆሴፍ ስሚዝ በሁለተኛው ራእዩ ያየው ሰው ሊገለጽ ከሚቻለው በላይ የከበረ፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ እንዲሁም ስሙ ሞርሞንይ የሚባል ነበረ:: ስሚዝ፣ ሞርሞናይ የሚባለው ሰው ገለጸልኝ የሚለውም ነገር፣ በወርቅማ ሳሕኖች ላይ የተጻፈና መሲሑ ለአሜሪካ ነዋሪዎች የሰጠው ድርሳን (ጽሑፍ) ነበር:: በተጨማሪም በብር ጋኖች ውስጥ የተቀመጠና ከጥሩር ጋር የተጣበቁ ሁለት የሁሪምና የቱሚም ድንጋዮች ከሳሕኖቹ ጋር እንዳሉ፣ የድንጋዮቹም ዐላማ መጽሐፉን ለመተርጐም እንደሚረዳ «ገለጸለት»[46]::

ሰማያዊው መልእክተኛ በዚያው ሌሊት ለሁለተኛ ጊዜ ተገልጦለት መጀመሪያ የገለጸለትን ነገር ዳግም ተናገረው:: ሳሕኖቹ ያሉበትንም ቦታ አሳየው:: በማግስቱ ከሚኖርበት ከተማ ውጪ ወደ ሚገኘው ኩረብታማ ስፍራ ሲሄድ በድንጋይ ሣጥን ውስጥ ሁሪምና ቱሚሙን እንዲሁም ጥሩሩን አገኘ:: ነገር ግን መልአኩ እንዲወስዳቸው አልፈቀደለትም፤ ሆኖም ለተከታታይ አራት ዓመት በየዓመቱ፣ ልክ በዚሁ ወቅት መምጣት እንዳለበት ገለጸለት:: በመጨረሻም መስከረም 22ቀን 1827ዓ.ም ሳሕኖቹ በሰማያዊው መልእክተኛ እጅ ተሰጠው[47]:: የጽሑፎቹም የትርጉም ሥራ መጋቢት 26 ቀን 1830 ዓ.ም ተጠናቀቀ:: የትርጉሙ ሥራ ከተጠናቀቀ ከዐሥራ አንደኛው ቀን በኋላ የሞርሞን ቤተ ክርስቲያን («የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን») በስድስት

[45] ዝኒ ከማሁ ገጽ 342
[46] ዝኒ ከማሁ::
[47] ዝኒ ከማሁ::

ሰዎች አባልነት ተመሠረተ:: የመጠሪያ ስሙም፣ «የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን፣ የመጨረሻው ዘመን ቅዱሳን» ተባለ[48]::

በወቅቱ ብዙ ሰዎች በሞርሞኖች ላይ የተለያዩ ጽሑፎችን ጽፈዋል:: ስሚዝም እነዚህ ጽሑፎችና የታተመባቸው ማተሚያ ቤት እንዲቃጠል አዘዘ፤ በዚህም ምክንያት ስሚዝ ከወንድሙ ከሃይሩም ጋር ታስሮ ዘብጥያ ተወረወረ:: ሰኔ 27ቀን 1844ዓ.ም ተቃውሞ ሰልፍ ያደረጉ 200 ሰዎች እስር ቤቱን ሰብረው በመግባት ሃይሩምንና ጆሴፍን ተኩሰው ገደሉአቸው:: እንደ ቤተ ክርስቲያኒቱ አስተምህሮ ጆሴፍ ሳይዋጋ እጁን አጣምሮ የሞተ ሰማዕት አልነበረም:: ነገር ግን ብዙዎችን ተኩሶ ያቈሰለ እንጂ[49]::

ጆሴፍ ስሚዝ ሰኔ 27ቀን 1944ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ፣ የዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ፕሬዝዳንት የነበረው ብሪግሃም ያንግ የአመራር ቦታውን ያዘ::

[48] ዝኒ ከማሁ 342::
[49] ዝኒ ከማሁ::

ለ. የሞርሞን ቤተ ክርስቲያን ዐዋጆች

ሞርሞኖች፣ በኢየሱስ ክርስቶስ የተመሠረተችውን እውነተኛዪቱን ቤተ ክርስቲያን እንደሚያድሱ ይገልጻሉ:: ይህቺም ቤተ ክርስቲያን የኦርቶዶክስ፣ የካቶሊክ ወይም የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናትን አይደለችም፤ ነገር ግን ይህቺ ቤተ ክርስቲያን «ብቸኛዋና እውነተኛዋ» የሞርሞን ቤተ ክርስቲያን ነች:: የቤተ ክርስቲያኗም አባል ካልሆኑ ደኅንነት የሚታሰብ ጉዳይ አይደለም:: ጆሴፍ ስሚዝንም እንደ ነቢይ ያልተቀበሉ ሰዎች ደኅንነት የላቸውም[50]::

የሥልጣን ምንጮች

የሞርሞን ቤተ ክርስቲያን አራት የተቀደሱ መጻሕፍት አሉት:: እነርሱም መጽሐፍ ቅዱስ፣ የሞርሞን መጽሐፍ፣ አስተምህሮና ቃል ኪዳን («ዶክትሪን ኤንድ ኮቬናንትስ») እንዲሁም «ዘ ፐርል ኦፍ ግሬት ፕራይስ» ናቸው:: የዛሬዎቹም የድርጅቱ ነቢያት ቃል የሥልጣን ምንጭ ተደርጐ ይታያል::

1. መጽሐፍ ቅዱስ

ሞርሞኖች፣ «መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል ከተተረጐመ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን እናምናለን» ይላሉ:: የሞርሞን መጽሐፍ «የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን ስላጣመመችው፣ መጽሐፍ ቅዱስን አንብቦ ትክክለኛውን መንገድ ማወቅ አይቻልም» ይላል (1 ኔፊ 13÷26-27)::

[50] ዝኒ. ከማሁ:: 343-344::

ስለዚህ ሞርሞኖች ከመጽሐፍ ቅዱስ ይልቅ፣ በድርጅቱ ዘንድ እንደ ሥልጣናዊ ቃል የሚታዩትን ሌሎቹን ሦስት መጻሕፍት የበለጠ ተአማኒነት ይሰጡአቸዋል:: ይህም ሞርሞኖች ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ የራሳቸውን አዲስ ሐሳብ እንዲጨምሩ በር ከፍቶላቸዋል:: እነዚህም አዳዲስ ሐሳቦች የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያወጣችው አስተምህሮዎች ናቸው ብለው ያምናሉ::

2. የሞርሞን መጽሐፍ

የሞርሞኖች የእምነት አንቀጽ፣ «የሞርሞን መጽሐፍ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ እናምናለን» ይላል:: የሞርሞን መጽሐፍ በስፋት የሚተርከው ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሣኤው በኋላ ለአሜሪካን አገር ቀደምት ነዋሪዎች የመገለጡን ጉዳይ ነው::

3. አስተምህሮና ቃል ኪዳኖች

አስተምህሮና ቃል ኪዳኖች («ዶክትሪን ኤንድ ኮቬናንትስ») የተባለው መጽሐፋቸው የሞርሞን አስተምህሮ ልዩ ባሕርያት ስለ ሆኑት ስለ ሙታን መጠመቅና ስለ ሰማያዊ ጋብቻ የሚያወራ ነው::

4. ዘ ፔርል ኦፍ ግሬት ፕራይስ

ይህ መጽሐፍ « የሙሴን መጽሐፍ» የያዘ ነው:: በሌላ አነጋገር የዘፍጥረት የመጀመሪያዎቹን ስድስት ምዕራፎች የሚተካ መጽሐፍ ነው:: «የአብርሃም መጽሐፍ» የሚባለው ደግሞ፣ «የግብፃውያንን ጳጺራ [ፓፒረስ]» የሚተረጉም ነው:: «የግብፃውያን የጳጺራ» ትርጉም የሚባለው፣ ሆን ተብሎ ለማታለል የተጻፈ ነገር ነው::

ይህ መጽሐፍ ጆሴፍ ስሚስ መጽሐፍ ቅዱስን በተመለከተ የሰጠውን ማብራሪያ፣ በጆሴፍ ስሚዝ የተጻፈ የራሱ የሕይወት ታሪክ እንዲሁም የእምነት አንቀጻቸውን የያዘ መጽሐፍ ነው።

ሐ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሞርሞን እምነት ምን ይላል?

መጽሐፍ ቅዱስ የሞርሞኖችን አስተምህሮ በጽኑ ይቃወማል። የሞርሞን መጻሕፍት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ብቻ ሳይሆን እርስ በርሳቸውም ይቃረናሉ። መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በርሱ አይጋጭም። የመጽሐፍ ቅዱሱ እግዚአብሔር ራሱን አይቃረንምና። ዕብራውያን 1÷1-3 ስለ እግዚአብሔር ያለን ዕውቀት ከየት እንደሚመነጭ ሲናገር፦

«ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዐይነትና በብዙ ጐዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ፣ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ፣ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን፤ እርሱም የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ ሆኖ ሁሉን በሥልጣኑ ቃል እየደገፈ፣ ኀጢአታችንን በራሱ ካነጻ በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ» ይላል።

ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ ነው የሚባል ማንኛውም ዐይነት መልእክት፣ የብሉይ ኪዳን ፍጻሜ ከሆነው ከኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ጋር መጣጣም አለበት (ሉቃ 24÷27)። የዘላለም ሕይወት የሚገኘው በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራና ስጦታ ብቻ ነው እንጂ ከጆሴፍ ስሚዝ፣ ከብሪግሃም የንግ ወይም ከሌሎች የሞርሞን ሐሰተኛ ነቢያት አይደለም (ዮሐ 20÷31)። በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የራሳቸውን ትምህርት የሚጨምሩትን ሰዎች በተመለከተ ቃለ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል።

«የእግዚአብሔር ቃል ሁሉ ተፈትናለች፤

እርሱ ለሚታመኑት ጋሻ ነው።

እንዳይዘልፍህ፣ ሐሰተኛም እንዳትሆን

በቃሉ አንዳች አትጨምር» (ምሳ 30÷5-6)

መ. የሞርሞን አስተምህሮ

እግዚአብሔር

የሞርሞኖች እግዚአብሔር፣ መጽሐፍ ቅዱስ ከሚያስተምረው እግዚአብሔር የተለየ ነው። ሞርሞኖች በብዙ አማልክት ያምናሉ። እንዲያውም እግዚአብሔር ራሱ በአንድ ወቅት ሰው ነበር የሚል እምነት አላቸው። የሞርሞን ወንዶች እግዚአብሔር የመሆን ዕድል አላቸው[51]። ሞርሞኖች ስለ እግዚአብሔር ያላቸው አስተምህሮ ከቃለ እግዚአብሔር ጋር ብቻ ሳይሆን ከራሳቸውም መጽሐፍ ጋር ይቃረናል። ለምሳሌ እነዚህን ክፍሎች «ከሞርሞን መጽሐፍ ላይ» ይመልከቱ አልማ11÷21-22፤ 1ኔፊ11÷7፤31÷21፤ 3ኔፊ11÷27፡36፤ ሞሳያ 15÷1-5፤ 16÷15።

መጽሐፍ ቅዱስ አንድነት ሦስትነት የባሕርይ ገንዘቡ የሆነ አንድ እግዚአብሔር ብቻ እንዳለ በአጽንዖት ያስተምራል። ለምሳሌ ኢሳ 43÷10፤ «ታውቁና ታምኑብኝ ዘንድ እኔም እንደ ሆንሁ ታስተውሉ ዘንድ፣ እናንተ የመረጥሁትም ባሪያዬ ምስክሮቼ ናችሁ ይላል እግዚአብሔር፤ ከእኔ በፊት አምላክ አልተሠራም ከእኔም በኋላ አይሆንም» ይላል።

---

[51] ዝኒ ከማሁ ከ The King follett Discourse ገጽ 8-10 ጠቅስ እንደ ጻፈው።

አዲስ ኪዳን፣ ሰዎች የሚያመልኩአቸው ሐሰተኞች አማልክትና ጣዖታት ከንቱ እንደሆኑ ያስረዳል፣ «…ጣዖት ሁሉ በዓለም ከንቱ እንደ ሆኑ ከአንዱም በቀር ማንም አምላክ እንደሌለ እናውቃለን» (1ቆሮ 8÷4)::

ኢየሱስ ክርስቶስ

የሞርሞን ቤተ ክርስቲያን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ማንኛውም ሰው በቅድመ ህልውናው ("pre-existent spirit") መንፈስ ነበር ይላል:: ሁላችንም የኢየሱስ ክርስቶስ ወንድሞችና እኅቶች ብንሆንም እንኳ፣ የእግዚአብሔር በኵር የሆነ የመንፈስ ልጅ በመሆኑ ይበልጠናል::

ቃለ እግዚአብሔር ከሞርሞን አስተምህሮ ጋር በሚጋጭ ሁኔታ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጁ መሆኑን ይገልጻል፣ «ቃልም ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ ዐደረ፤ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን» (ዮሐ 1÷14):: ኢየሱስ ክርስቶስ በምድራዊ ሕይወቱ ማንም ሰው ማድረግ በማይችለው ሁኔታ፣ የእግዚአብሔርን ኀይል ገልጦአል፣ «እርሱም የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው፤ የሚታዩትና የማይታዩትም ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት፣ በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና» (ቈላ1÷15)::

ሰው

እንደ ሞርሞን አስተምህሮ ሰው ቈሳዊ አካል አግኝቶ ወደዚህ ምድር ከመምጣቱ በፊት መንፈስ ነበር:: «ሰው በመገናኛ ድንኳን የተሸፈነ መንፈስ ነው፤ የሰው አእምሮአዊ ክፍሉ አልተሠራም ወይም

አልተፈጠረም፤ ነገር ግን ዘላለማዊ ሰውም ከመጀመሪያው ጀምሮ ከእግዚአብሔር ጋር ነበር»[52]::

«አንድ ቀን እንደ እግዚአብሔር ወይም እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እሆናለሁ ብሎ ማሰብ እግዚአብሔርን መጻረፍ (መሳደብ) ነው::»

ሠ. የሞርሞን መጽሐፍና የሥነ ቅርስ ጥናት

በሥነ ቅርስ ላይ ሰፊ ጥናት ያካሄዱ የሞርሞን ምሁራንም ሆኑ ሌሎች የደረሱባቸው እውነታዎች የሞርሞንን እምነት የሚደግፉ አይደሉም:-

1. በሞርሞን መጽሐፍ[53] ውስጥ የተጠቀሱት ከተሞች የት እንደሚገኙ እንኳ በትክክል አይታወቅም::
2. በአዲሲቱ ምድር (አሜሪካ) ላይ የተካሄዱ ጥናቶች በሞርሞን መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱት ዐይነት ስሞች አልተገኙም::
3. በአሜሪካን አገር በዕብራይስጥ ቋንቋ የተጻፉ የዕቃ ላይ ጽሑፎች አልተገኙም::
4. የግብፃውያንም ሆኑ ከግብፃውያን ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ማናቸውም ዐይነት ጽሑፎች በአሜሪካን አገር አልተገኙም::
5. እስከ ዛሬ ጥንታዊ የሆነ የሞርሞን መጽሐፍ አልተገኘም::
6. የጥንት የአሜሪካን አገር ነዋሪዎች የዕብራውያንም ሆነ ክርስትና እምነት አማኒያን ለመሆናቸው ምንም ዐይነት መረጃ የለም::

[52] ዝኒ አማሁ ከ Joseph Fielding Smith. Doctrines of Salvation ጠቅሶ እንደጻፈው::
[53] የሞርሞን መጽሐፍ የሚባለው፣«Book of Mormon»ነው:: ይህ መጽሐፍ በአሁኑ ወቅት በአማርኛ ተተርጕሞ ለንባብ ቀርቦአል::

7. በሞርሞን መጽሐፍ ላይ የሚገኙት ሰዎች፣ ሕዝቦችና ቦታዎች ለታሪክና ለሥነ ቅርስ ጥናት ባዕዳን ናቸው::
8. የሞርሞን መጽሐፍ ትክክለኛ መጽሐፍ ለመሆኑ፣ ምንም ዐይነት ውጫዊ ማስረጃ የለም::

ማጠቃለያ

የሞርሞን ቤተ ክርስቲያን፣ ቀዳማይ ዐላማዬ ለክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ማምጣት ነው ቢልም እውነቱ ግን ከዚህ እጅግ የራቀ ነው::

«ነገር ግን ይናገር ዘንድ ያላዘዝሁትን በስሜ በድፍረት የሚናገር ወይም በሌላ አማልክት ስም የሚናገር ነቢይ፣ እርሱ ይገደል:: በልብህም:- እግዚአብሔር ያልተናገረውን ቃል እናውቅ ዘንድ እንዴት ይቻለናል? ብትል፣ ነቢዩ በእግዚአብሔር ስም በተናገረ ጊዜ የተናገረው ነገር ባይሆን ባይመጣም፣ ያ ነገር እግዚአብሔር ያልተናገረው ነው፤ ነቢዩ በድፍረቱ ተናግሮታል፤ እርሱን አትፍራው»

(ዘዳ 18÷20-22)

ዋቢ መጻሕፍት

በመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር የተጻፉ መጻሕፍት መካከል ዋኞቹ

- <u>በምድር ላይ በገነት ለዘላለም መኖር ትችላለህ</u>
  - እምነቱን የተቀበሉ አዳዲስ ሰዎች የሚማሩበት መጽሐፍ ነው::
- <u>በሥላሴ ማመን ይገባሃልን?</u>
  - ትምህርተ ሥላሴን ለመቃወም ተብሎ የተዘጋጀ መለስተኛ መጽሐፍ ነው::
- <u>ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር</u>
  - የይሖዋ ምስክሮች አስተምህሮአቸውን በተመለከተ የሚጠየቁትን ጥያቄ ለመመለስ ያስችላቸው ዘንድ የተዘጋጀ ነው::
- <u>Insight on the Scritures,</u> ቅጽ 2

  -የይሖዋ ምስክሮች ሥልጣናዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ (encyclopedia) ነው::
- <u>Jehovah's Witnesses: Proclaimers of God's Name</u>

  -ከራስል ዘመን ጀምሮ እስካሁን ያሉትን የድርጅቱን ፕሬዝዴንቶች ታሪክ ይተርካል::

- The Kingdom Inter Linear Translation of the Greek Scriptures

  -የአዲስ ኪዳን ግሪክ መጻሕፍትን ቃል በቃል በእንግሊዝኛ የተረጐሙበት መጽሐፍ ነው:: በገጹ በስተ ግራ ጎዳግ ላይ በአዲሲቱ ዓለም ትርጕም (NWT) እንዴት እንደተረጐመው ተገልጾአል:: የአዲስቱ ዓለም ትርጕም ለድርጅቱ አስተምህሮ ያደረ መሆኑን የግሪኩን ትርጕምና በስተ ቀኝ ባለው ጎዳግ ላይ የሰፈረውን የአዲሲቱ ዓለም ትርጕም በማነጻጸር የይሖዋ ምስክሮችን መርዳት ይቻላል::

- New World Translation of the Holy Scriptures: With References, ev.ed.

  -ይህ ድርጅቱ ከዕብራይስጥና ከግሪክ ተርጕሜዋለሁ የሚለው መጽሐፍ ቅዱስ ነው:: ይህ መጽሐፍ፣ «የአዲሲቱ ዓለም ትርጕም» በሚል ርእስ በ1993ዓ.ም ወደ አማርኛ ተተርጕሞአል፤ በቅርቡም እንደሚሠራጭ ይገመታል::

በ «ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን» የተጻፉ መጻሕፍት

- ተክለማርያም ገዛኸኝ፤ ኢየሱስን ማን ይሉታል?

  -ድርጅቱ የሰብአልዮስን ትምህርት እንደሚከተል ይፋ ያደረገ መጽሐፍ ነው::

- ተክለማርያም ገዛኸኝ፤ አዲስ ልደት

  -«በኢየሱስ ስም» መጠመቅ ለደኅንነት አስፈላጊ መሆኑን በስፋት ያትታል::

- ተክለማርያም ገዛኸኝ፤ የኢትዮጵያ ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን የእምነት አንቀጾች

  -የድርጅቱ የእምነት አንቀጽ ነው:: የዚህን መጽሐፍ አስተምህሮ « የማይቀበል በስሕተት መንፈስ የተሞላ ነው» በሚል ዐረፍተ ነገር ነው የተቋጨው::

- ተክለማርያም ገዛኸኝ፤ በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፊልጉ

  -የድርጅቱን አስተምህሮ አዳዲስ ለሆኑ የእምነቱ ተከታዮች ያቀርባል::

- ተክለማርያም ገዛኸኝ፤ አንድ መንጋ

  -ሰዎች ድርጅቱን እንዲቀላቀሉ የቀረበ ጥሪ ነው::

- ከተክለማርያም ገዛኸኝ፤ መለኮታዊ ኀይል

  ግለሰቡ ድርጅቱን ከመቀላቀሉ በፊት የጻፈው መጽሐፍ ነው::

- አማረ ዋቅቶላ ሐዋርያትና ነቢያት ምን አስተማሩ (ተርጓሚ)

  -ድርጅቱ ለአገልጋዮች በአዋሳ ባዘጋጀው ዐውደ ጥናት ላይ እንዲያስተምሩ ከአሜሪካ «ዓለም ዐቀፍ ሐዋርያት ቤተ ክርስተያን» የመጡትን የዴቪድ በርናርድን ትምህርት ወደ አማርኛ የተተረጐመበት ነው::

በይሖዋ ምስክሮች ላይ ከተሠሩ ሥራዎች መካከል ዋነኞቹ

Bowman, Robert M., Jr. Understanding Jehovah's Witnesses: Why They Read the Bible the Way They Do (Grand Rapids: Baker,1991).

Bowman, Robert M., Jr. Why You Should Believe in the Trinity :An Answer to Jehovah's Witnesses (Grand Rapids: Baker, 1989).

Bowman, Robert M., Jehovah's Witnesses (Grand Rapids: Zondervan, 1995)

Finnerty, Robert U., Jehovah' Witnesses On Trial: The Testimony of the Early Church Fathers (Phillipsburg, N.J.: Presbyterian & Reformed, 1993)

Gruss, Edmond C. The Jehovah's Witnesses and Prophetic Speculation, zd ed (Nutley, N.J.: Presbyterian & Reformed, 1975).

Gruss, Edmond C. Cults And The Occult (Nutley, N.J.: Presbyterian &Reformed, 1982).

Hoekema, Anthony A. The Four Major Cults. (Grand Rapids: Eerdmans, 1978).

Jonsson, Carl Olof. The Gentile Times Reconsidered, ed. M. James Penton (Lajolla, Calif.: Good News Defenders, 1983).

Magnani, Duane, and Arthur Barrett. The Watchtower Files: Dialogue With a Jehovah's Witness (Minneapolis: Bethany House, 1985).

Reed, David A. How to Rescue your Loved Ones from the Watch tower (Grand Rapids: Baker, 1989).

Rhodes, Ron. Reasoning from the Scriptures with Jehovah's Witnesses (Eugene,: Harvest House, 1993).

ነገረ መለኮት መጻሕፍት

Basic Christian Doctrines, ed. Carl F. Henry. (Grand Rapids: Baker, 1983).

Berkhof, Louis. Manual of Christian Doctrine (Grand Rapids: Eerdmans, 1983).

Erickson, Millard J. Christian Theology. (Grand Rapids: Baker, 1987)

Ryrie, Charles C. Basic Theology (Wheaton IL.: Victor Books, 1986).

አንድምታዎች

Bible Knowledge Commentary, Old Testament Eds. John F. Walvoord and Roy B. Zuck (Wheaton, IL: Victor Books, 1985).

Bible Knowledge Commentary, New Testament Eds. John F. Walvoord and Roy B. Zuck (Wheaton, IL : Victor Books, 1985).

Bruce, F.F. The Book of Acts. (Grand Rapids: Eerdmans, 1986).

Bruce, F.F The Epistle to the Hebrews. (Grand Rapids: Eerdmans, 1984).

መናፍቃንን አስመልክት በጸሓፊው እየተዘጋጁ ያሉ መጻሕፍት

- «የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን» አስተምህሮ በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን
- «በሥላሴ ማመን አይገባህምን?» ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉን ቻይ አምላክ አይደለምን?
- ያልተከፈለ የቤተ ክርስቲያን ዕዳ፣ የእምነት ወይስ የክሕደት እንቅስቃሴ?

«ወንድሞች ሆይ፤ መጠራታችሁን ተመልከቱ፤ እንደ ሰው ጥበብ ጥበበኞች የሆኑ ብዙዎች፤ ኀያላን የሆኑ ብዙዎች፣ ባላባቶች የሆኑ ብዙዎች አልተጠሩም። ነገር ግን እግዚአብሔር ጥበበኞችን እንዲያሳፍር፣ የዓለምን ሞኝ ነገር መረጠ፤ ብርቱንም ነገር እንድያሳፍር፣ የዓለምን ደካማ ነገር መረጠ፤ እግዚአብሔር የሆነውን ነገር እንድያጠፋ የዓለምን ምናምንቴ ነገር፣ የተናቀውን፣ ያልሆነውን ነገር መረጠ። ሥጋን የለበሰ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት እንዳይመካ። ነገር ግን የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ።» (1ቆሮ 1÷26-30)

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ዘአፈጸመኒ በዳኅና

ተስፋዬ ሮበሌ
አዲስ አበባ፤ ወርኀ መስከረም 1994 ዓ.ም